አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀውን መርሀ ትምህርት ትግበራ ግምገማ

(በኦሮሚያ ክልል 8ኛ ክፍል ናሙናነት)

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በሽመልስ በጅጋ

1993 ዓ /ም
አዲስ አበባ

# አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ (በኦሮሚያ ክልል 8ኛ ክፍል ናሙናነት)

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን የማስተማር ሥነ ዘዴ የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስችሉት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በሽመልስ በጅጋ

ግንቦት 1993
አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት


# አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ (በኦሮሚያ ክልል 8ኛ ክፍል ናሙናነት)


በሽመልስ በጅጋ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም


## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

[illegible] (ዶ/ር) ______ ______

አማካሪ ፊርማ

[illegible] (ዶ/ር) ______ ______

ፈታኝ ፊርማ

[illegible] (ዶ/ር) ______ ______

ፈታኝ ፊርማ

## ምስጋና

ይህ የጥናት ፅሁፍ በዚህ መልክ ተጠናቆ እንዲዘጋጅ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሳይቆጥቡ ረቂቁን ከማንባብ ጀምሮ ገንቢ አስተያየት በመስጠትና ልምዳቸውን በማካፈል ለረዱኝ አማካሪዬ ዶ/ር መኮንን ዲሣሣ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ለጥናቱ ማካሄጃ መጠነኛ ወጪ በማድረግ ድጋፍ ያደረገልኝን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት አመሰግናለሁ።

በሞራልና በገንዘብ በመደገፍ ከጎኔ ላልተለየችው ባለቤቴ ወ/ሮ ካሣነሽ፥ የልጅነት ፍላጎታቸውን ገድበው በትዕግስት ለጠበቁኝ ልጆቼ ፍሬህይወት፥ አብርሃም፥ ርሆቦትና ሄርሞን ውለታቸውን ከፍዬ አልጨርሰውም።

ገና ከጅምሩ ከርዕስ መምረጥ ጀምሮ በምክር የረዱኝ የዩኒቨርሲቲ ጓደኞቼ ታደሰ፥ ዘላለም፥ ስንቅነሽ፥ ሰለሞን እንዲሁም በማቴሪያል ድጋፋቸው ያልተለዩኝ በድሩ፥ ዘንባባና ጌትነት ምስጋና ይገባቸዋል።

የጥናቱን መጠይቆችና ፈተና በኮምፒዩተር በመተየብ ለተባበረችኝ ወ/ሮ ንግስት እንዲሁም ዋናውን ፅሁፍ በመፃፍ ለተባበረችኝ ወ/ሪት ወገኔ ከልብ የሆነ ምስጋና ይድረሳቸው።

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**


ምስጋና.....................................................................................I

ማውጫ.....................................................................................II

የቻርት ማውጫ.....................................................................................IV

የሠንጠረዥ ማውጫ.....................................................................................V

አጠቃሎ.....................................................................................VI

ምዕራፍ አንድ፥ መግቢያ.....................................................................................1

1.1. የጥናቱ ዳራ.....................................................................................1

1.2. የጥናቱ ዓላማ.....................................................................................4

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት.....................................................................................4

1.4. የጥናቱ ወሰን.....................................................................................5

ምዕራፍ ሁለት፥ ክለሣ ድርሳናት.....................................................................................6

2.1. ስርዓተ ትምህርትና መርሃ ትምህርት.....................................................................................6

2.2. የመርሃ ትምህርት ትግበራ.....................................................................................7

2.3. የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ.....................................................................................9

2.4. የመርሃ ትምህርት ትግበራን የሚወስኑ ተላውጦዎች.....................................................................................12

2.4.1. የለውጥ ባህሪ.....................................................................................13

2.4.2. የለውጥ ተሳታፊዎች ሚና.....................................................................................14

2.4.2.1. ርዕሳነ መምህራን.....................................................................................14

2.4.2.2. መምህር.....................................................................................15

2.4.3. ለመርሃ ትምህርት ትግበራ የአስተዳደራዊ አወቃቀር ድርሻ.....................................................................................16

2.4.4. የማስተማሪያ መሣሪያዎች ቅንጅት.....................................................................................17

ምዕራፍ ሦስት፥ የአጠናኑ ዘዴና ቅደም ተከተል.....................................................................................20

3.1. ለጥናቱ የተመረጠው ሞዴል.....................................................................................20

3.2. የናሙና አመራረጥ ሂደት.....................................................................................22

3.2.1. የወረዳዎችና የትምህርት ቤቶች አመራረጥ.....................................................................................22

3.2.2. የተማሪዎች አመራረጥ.....................................................................................22

3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች........23

3.3.1. የፅሁፍ መጠይቅ........23

3.3.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ........24

3.3.3. የብቃት መለኪያ ፈተና........24

3.4. ጥናቱ የተከተለው የመረጃ ትንተና ዘዴ........26

ምዕራፍ አራት፥ የመረጃ ትንተና ትርጓሜ........29

4.1. መምህራን ለመርሃ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት........29

4.2. የመምህራን የክፍል ውስጥ ማስተማር ብቃት........29

4.3. የመማር ማስተማሩን ሁኔታ ለማራመድ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊ ሁኔታዎች........35

4.4. የመርሃ ትምህርት ትግበራን የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች........44

4.5. የተማሪዎች የብቃት መለኪያ ፈተና........46

ምዕራፍ አምስት፥ ማጠቃለያ፥ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳቦች........50

5.1. ማጠቃለያ........50

5.2. መደምደሚያ........51

5.3. የመፍትሄ ሃሳቦች........52

ዋቢ የመረጃ ምንጮች........54

አባሪዎች........58

አንድ፥ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተጣጥሞሽ........58

ሁለት፥ ለመምህራን የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ........59

ሦስት፥ ለርዕሰ መምህራን የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ........66

አራት፥ የምልከታ ቅፅ 'ሀ' ና 'ለ'........69

አምስት፥ የፈተና ተዋፅኦ ዝርዝር........71

ስድስት፥ የብቃት መለኪያ ፈተና........72

ሰባት፥ መልስ የሰጡ መምህራን ዳራዊ ሁኔታ........77

ስምንት፥ ሀ. የ CHI SQUARE ስሌቶች........78

ለ. የብቃት መለኪያ የገጠርና የከተማ $X^2$ ስሌት........79

ሐ. የብቃት መለኪያ የወረዳዎች የ$X^2$ ስሌት........80

ዘጠኝ፥ ጥናቱ የተካሄደበት ዞን ካርታ........81

# የቻርት ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

1. የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ተከታታይና ተዛናቂ ሂደት.............................7
2. በታቀደ የለውጥ ሂደት ውስጥ የትግበራ እይታ.......................................9
3. የቀዳሚ ነገር፥ የመስተጋብርና የውጤት ግንኙነት....................................12
4. ውስብስብነትና የትግበራ ተዛምዶ..........................................................13
5. የ'ስቴክ' የዓላማ የሂደትና የውጤት ተጣጥሞሽ ሞዴል..............................21

# የሠንጠረዥ ማውጫ


ርዕስ ገፅ

1. የማለፊያ ወሰን ማሳያ.....27
2. የመምህራኑ ለመርሃ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት አማካይ.....29
3. በእርከናዊ ልኬት የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤት.....31
4. በቼክ ሊስት የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤት.....32
5. የቁሳቁስ አቅርቦት መግለጫ.....36
6. ለመምህራን የተሰጠ የፅህፈት መሣሪያዎች መግለጫ.....37
7. የማስተማሪያ መሣሪያዎች በበቂ ሁኔታ መገኘት ወይም አለመገኘትን የሚያሳይ..39
8. የርዕሰ መምህራኑ ግንኙነትና ድጋፍ ከመምህራን ምላሽ የተገኘ.....40
9. የተመደበውን ክፍለ ጊዜ፣ የመምህራንን ጫናና የተማሪዎች ብዛት ያለውን ተፅዕኖ የሚገልፅ.....41
10. የመምህር መምሪያው ይዘት ከመማሪያ መፃህፍ አንፃር.....43
11. በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች ደረጃ.....44
12. ከማለፊያ ወሰን በላይና በታች ውጤት.....46
13. የብቃት መለኪያ ፈተና ውጤት በገጠርና በከተማ ንፅፅር.....47
14. በወረዳዎች መሀከል ከማለፊያ ወሰን በላይና በታች ያስመዘገቡ.....47

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በ1990 ዓ.ም ሥራ ላይ የዋለውንና አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀውን የ8ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት የገመገመ ነው። በዋናነት ለመርሃ ትምህርቱና ለትግበራው የመምህራኑ አመለካከት ምን እንደሚመስል፥ የስልጠና ብቃታቸው ምን ያህል እንደሆነ፥ በተማሪው ላይ የታየው የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ፥ መርሃ ትምህርቱን ሙሉ ለሙሉም ሆነ በከፊል ተግባራዊ እንዳይሆን የሚያደናቅፉ ነገሮች ምን እንደሆኑ ተመልክቷል።

የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ አስፈላጊና በየጊዜው መካሄድ ያለበት መሆኑን በርካታ ምሁራን ይናገራሉ። (Shiundu እና Omulando 1992:61) የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ዑደታዊ መሆኑንና ግምገማም የዑደቱ አንድ አካል እንደሆነ ገልፀዋል። ግምገማውን ለማካሄድ ደግሞ መረጃዎች በተለያየ መንገድ ይሰበሰባሉ።

በዚህ ጥናት ርዕሳነ መምህራን፥ መምህራንና ተማሪዎች በመረጃ ሰጪነት አገልግለዋል። የፅሁፍ መጠይቆች፥ የምልከታ ቅፆችና የብቃት መለኪያ ፈተና በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ከመረጃ ሰጪዎቹ ወካይ ናሙና ለማግኘት ባለብዙ ደረጃ ቡድናዊ ናሙና አወሳሰድ ስልት ተግባራዊ ሆኗል።

በናሙናነት ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን፥ መምህራንና ተማሪዎች በተገኘው መረጃ መሠረት መምህራን ስለአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን፥ መምህራኑ መርሃ ትምህርቱን ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ ስልጠና የሚያስፈልጋቸው መሆኑን፥ በአንድ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር በርካታ መሆን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን፥ ለዓመቱ የቀረበውን ትምህርት በወቅቱ ለማጠናቀቅ የተመደበው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ መሆኑን ከቀረቡት ሦስት የትምህርት ዓላማዎች የሥነ ልሳን ትምህርት በዝቅተኛ ደረጃ ተግባራዊ መሆኑን ይህም ከከተማ ይልቅ በገጠር ዝቅተኛ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል።

በመሆኑም ስለ ፖሊሲው ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ የተለያዩ መድረኮችን ማዘጋጀት፥ ሙያቸውን ለማሻሻል አሁን የተጀመረውን የተልኮ ትምህርት በተጠናከረ ሁኔታ መቀጠል፥ የክፍል ጥበትን ለማስወገድ ግንባታ ማካሄድ፥ በሳምንት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ ከሁለት ወደ ሦስት ከፍ ማድረግ፥ የታዩትን ጠንካራ ጎኖች ይበልጥ በማጎልበት የተሳካ የመርሃ ትምህርት ትግበራ ማካሄድ አስፈላጊ ይሆናል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የትምህርት ስርዓት ሲዘረጋ የማህበረሰቡን ጥቅምና ፍላጎት መሠረት ያደርጋል። ስርዓቱም ሆን ተብሎ የታቀደና በአግባቡ የተደራጀ የዕውቀት (Knowledge)፥ የአስተሳሰብ (Concept)፥ የአመለካከት ወይም የልማድ (Attitude or habit) እንዲሁም የክሒሎች (Skills) ለውጥ ለማስገኘት የሚዘጋጅ ነው። ለውጡን ለማስገኘት የሚነደፈው ስርዓተ ትምህርት ለምን መማር እንዳስፈለገ፥ ምን መማር እንደሚገባ፥ በምን ያህል ጊዜ መማር እንደሚገባና እንዴት መማር እንደሚያስፈልግ በቂ መልስ የሚሰጥ ይሆናል።

በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካትተው ከሚቀርቡት ትምህርቶች አንዱ የቋንቋ ትምህርት ነው። ፍላጎትን ባገናዘበ መልኩ የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ (Behavioral change) ለማስገኘት የቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ይዘጋጃል። በዕቅድ ደረጃ የቀረበው ንድፍ ውጤታማ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመመዘን በትግበራ ሂደት መፈተሹ የግድ ነው። (Beauchamp 1968:132) አንድን የትምህርት ንድፍ ደካማ ሊያሰኘው የሚችለው ስልታዊ የሆነና የተቀናጀ የአተገባበር ሂደት ስለማይኖረው እንደሆነ ሲገልፁ (Fullan 1991:65) ደግሞ በዕቅድ አወጣጥ ጊዜ ስለትግበራው ሁኔታ ትኩረት ካልተሰጠው ሂደቱም ሆነ ውጤቱ ከንቱ ሊሆን እንደሚችል ያስረዳሉ። በርካታ የትምህርት ፕሮግራሞች ለትግበራ በቂ ትኩረት ባለመስጠታቸው ውጤታቸው መክኖ እንደቀረ (Giroux 1981:45-46, Sounders 1993:361, Gene 1995:104, Pratt 1995:409) ይጠቅሳሉ። (Gene 1995:174-175) የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ለትምህርት ከሚመደበው አብዛኛውን ገንዘብ የሚጠይቅና የሚወስድ እንደሆነ ገልፀው ይህ አካሄድ መለወጥ እንዳለበትና ለትግበራውም ሂደት የዚያኑ ያህል መዋለ ንዋይ ሊመደብለት እንደሚገባ አጠንክረው ይናገራሉ።

የትምህርት ፕሮግራም ትግበራ ውጤታማነት ሊታይ የሚችለው በጥንቃቄ በማቀድ ሲሆን ይህም ህዝብን፥ የማስተማሩን ፕሮግራምና የትምህርት አደረጃጀቱን ባገናዘበ መልኩ መሆን እንደሚገባው (Ornstein እና Hunkins 1998:283) ሲገልፁ አክለውም ትግበራ የማህበረሰቡ፥ የቁሳቁሱና የፕሮግራም ቅንጅቱ ውጤት እንደሆነ ይናገራሉ።

ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሃሳቦች በጥሩ ሁኔታ የታቀደ የባህሪ ማስገኛ ፕሮግራም፥ በጥሩ ሁኔታ የተመረጡ የትምህርት ልምዶችና ይዘቶች አደረጃጀቶች ብቻቸውን ወደ ተፈለገው ግብ የሚያደርሱ አለመሆናቸውንና የትግበራ ሂደት ተገቢ የሆነ ሥፍራ የሚያሻው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

የስርዓተ ትምህርት ትግበራ በተለያዩ ሁኔታዎች (Factors) ላይ ጥገኛ የሆነ ነው።

በዋናነት የሚታዩት ሦስት ተላውጦዎች ናቸው። አንደኛው ማህበረሰቡ ማለትም መምህሩ፥ ተማሪውና አስተዳደሩ፥ ተከታዩ መርሃ ግብሩ ሲሆን ሦስተኛው የትምህርት አደረጃጀቱ ናቸው። ከዚህ ጠበብ ባለ መልኩ ሲታይ ደግሞ መምህራን ርዕሣነ-መምህራንና አስተዳደሩ በትግበራ ላይ በአቢይነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ከዕቅድ አውጭዎችና ከመርሃ ትምህርት አዘጋጆች ይልቅ የትግበራ ጉዳይ ይበልጥ የሚመለከተው መምህሩን ነው። መምህሩ በአዘጋጆቹ የቀረበውን ለመተግበር ከተነሣሣ መልካም ግብ ላይ ሊደረስ እንደሚችል (Fullan እና Pomfret 1977:335-336) ይገልፃሉ። መምህሩ ለሚያከናውነው ተግባር የርዕሣነ መምህራንና የአስተዳደሩ ድጋፍ የጎላ ድርሻ ይኖረዋል። እነዚህ አካላት እርስ በርስ የተያያዙና የሚደጋገፉ ናቸው።

ከነዚህ ከሦስት አካላት የትግበራ ኃላፊነት ጫና የሚያርፈው መምህሩ ላይ ነው። ምክንያቱም መምህሩ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን በመያዝ ከተማሪው ጋር ተራክቦ የሚያደርግ በመሆኑ ነው። የተዋጣለትና እንከን የለውም የተባለ መርሃ ትምህርት ቢዘጋጅ እንኳ የትግበ ራው የመሳካት ደረጃ የሚወሰነው በመምህሩ ብቃት ነው። መምህሩ ለመርሃ ትምህርቱ ያለ ው አመለካከትና ዝግጅት እንዲሁም መረዳት (Understanding) በተጨማሪም ፈቃደኝነት የትግበራውን ሂደትና ውጤት ሊያሳምረው ወይም ሊያደበዝዘው ይችላል። በመሆኑም የመምህ ሩን አመለካከት በመለወጥ ሂደትና ስለ መርሃ ግብሩ ግንዛቤ እንዲኖረው በትምህርት አስተ ዳደሩ በኩል የተለያዩ የሙያ ላይ ስልጠና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

ትግበራ በአንድ የትምህርት ፕሮግራም ላይ ሰፊ ድርሻ እንዳለው ከቀረቡት መግለ ጫዎች መረዳት ይቻላል። የትግበራ ሂደት ውጤታማ መሆኑ ወይም አለመሆኑ የሚረጋገጠ ው በግምገማ ነው። ትግበራና ግምገማ ተያይዘው የሚሄዱ የስርዓተ ትምህርት አካላት ናቸው።

ግምገማ አንድ የማስተማሪያ መሣሪያ ወይም የማስተማሪያ ዘዴ ያለውን ብቃት በማሣየት ተገቢነቱን ወይም ኢ-ተገቢነቱን ሊያመለክት ይችላል። እንዲሁም እያንዳንዱ መምህር ለትግበራው ያለውን ብቃትና ተነሳሽነት በግምገማ መመዘን እንደሚቻል (Stenhouse 1975:98) ይጠቅሳሉ። ግምገማ ከዚህ አልፎ የመርሃ ትምህርትን ሁኔታ ይገልፃል ይላሉ። እንደ (Yeoman እና Beck 1987:10) ግምገማ በሂደት ላይ ያለ የትምህርት ፕሮግራምን በመፈተሽ መረጃ ለመስጠት፥ መርሃ ትምህርቱ አስቀድሞ ወደ ታለመለት ግብ የሚያደርስ መሆኑና አለመሆኑን ለማሣየት እንደሚረዳ ገልፀዋል። በተጨማሪም (Lewy 1977:156) አዲስ መርሃ ትምህርት ከተነደፈ በኋላ ወይም የማስተማሪያ ዘዴ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ መደበኛና ስልታዊ የሆነ ፍተሻ በመንፈቅ ጊዜ ውስጥ ወይም በዓመት አንድ ጊዜ በማካሄድ ውጤቱን መገምገም ተገቢ እንደሆነ ይጠቁማሉ።

በብዙዎቹ የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ማዕከሎች ግምገማ እንደ ጥራት መቆጣጠሪያ (Quality control) መለኪያ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህም የስርዓተ ትምህርትም ሆነ የመርሃ ትምህርት ዝግጅት በተደረገ ቁጥር ግምገማ የሚዘነጋ አለመሆኑን ያመለክታል። ግምገማ

አንድ ጊዜ ብቻ ተከናውኖ የሚያቆም ሳይሆን ዑደታዊ በሆነ መልኩ የሚከናወን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። (Fullan በLewy እና David 1981:335) እንደገለፁት በመጀመሪያ አካባቢ (በዓመትና በሁለት ዓመት) የሚደረግ ግምገማ የሥራውን ሂደት ለማመቻቸትና ለማከናወን የሚካሄድ እንጂ ውጤታማ መሆን ወይም አለመሆንን በማሳየት ውሳኔ የሚሰጥበት መሆን እንደሌለበት ያመለክታሉ።

ከላይ የቀረቡት ሃሳቦች ስለትግበራና የትግበራን ግምገማ አስፈላጊነት የሚያመለክቱ ናቸው። ይህ ጥናት በትግበራ ግምገማ ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ የትግበራ ግምገማ መርህን በመከተል አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት በመገምገም ላይ ያነጣጥራል። በኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ (1986:12-13) ላይ ትምህርትና ተመጣጣኝ ስልጠና በብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋ እንዲሰጥና አማርኛ ደግሞ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ግንኙነት በቋንቋ ትምህርትነት እንዲሰጥ ተደንግጓል። በዚህም መሠረት ባልተማከለ መልኩ በክልሎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ እንዲያስተምሩ ተደርጓል። በየክልሎቹም መርሃ ትምህርት ተዘጋጅቶለት ቀርቧል።

ይህ ጥናትም የሚካሄድበት የኦሮሚያ ክልል አማርኛ ቋንቋ እንደ አፍ መፍቻና እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚሰጥበት ነው። አማርኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚማሩት በክልሉ የሚኖሩ በኦሮምኛ አፋቸውን ያልፈቱ ሲሆኑ እነዚህ ተማሪዎች የአንደኛ ደረጃ (1-8) ትምህርቶችን የሚከታተሉት በአማርኛ ቋንቋ ነው። ጥናቱ ትኩረት የሚያደርግበት ደግሞ በኦሮምኛ አፋቸውን ለፈቱ እንደ አንድ ቋንቋ የሚቀርበውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ነው። አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ ለፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መቅረብ የሚጀምረው ከአምስተኛ ክፍል ነው። ተማሪዎቹ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ከአንደኛ መፅሃፍ እስከ አራተኛ መፅሃፍ ድረስ ያለውን ያጠናቅቃሉ። መፃህፍ ቱን በሚመለከት በትግበራ ላይ ስለታየው ሁኔታ ከዚህ ቀደም ጥናቶች እንዳልተካሄዱ መረጃዎች ያስረዳሉ።

የዚህ መርሃ ትምህርት ዝግጅት ከሌሎች ትምህርቶች የሚለየው በክልል ደረጃ መዘጋ ጀቱ ነው። የሌሎች ትምህርቶች መርሃ ትምህርት የሚዘጋጁት በአገር አቀፍ ደረጃ በስርዓተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም (ICDR) ሲሆን የክልሎች ድርሻ መርሃ ትምህርቱን መሠረት በማድረግ የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መፅሃፍ ያዘጋጃሉ።

በክልል ደረጃ የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት (በተለይ በስምንተኛ ክፍል መነሻነት) ትግበራን በሚመለከት ቀደም ሲል የተካሄደ ጥናት ባለመኖሩ በዚህ ረገድ በዚህ ወቅት ጥናት ማካሄዱ ተገቢ ሆኖ ይታያል።ይህም መርሃ ትምህርቱ ምን ያህል ተግባ ራዊ እንደሆነ ሊያሳይ ከመቻሉም በላይ በትግበራው ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በመጠቆም አማራጭ ሊሆን የሚችል መፍትሄ ሊቀርብበት ይችላል።

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

በ1990 ዓ.ም ሥራ ላይ የዋለውንና አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋ ጀውን የ8ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ትግበራ መገምገም የዚህ ጥናት ዓላማ ነው። በጥናቱ መርሃ ትምህርቱ ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነ፥ ለ8ኛ ክፍል የተመደቡት መምህራን በመር ሃ ትምህርቱና በመምሪያ መፅሃፍ የቀረበውን ተግባራዊ ለማድረግ ያላቸው ብቃት ምን ያህ ል እንደሆነ፥ በመርሃ ትምህርቱ አተገባበር ላይ ዋና ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉ መሰናክሎች ካሉም ምን እንደሆኑ ማሳየትና የበኩሉን መፍትሄ መጠቆም ሲሆን ለሚከተሉት አምስት የምርምር ጥያቄዎች መልስ ይሻል፤

### የምርምሩ ጥያቄዎች

1. የተመደቡት መምህራን በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተገለፀውን በተገቢው መንገድ ለተማሪው ለማስተላለፍ ያላቸው አመለካከትና ፍላጎት ምን ይመስላል?
2. መምህራኑ በመርሃ ትምህርቱ የተገለፀውን ለማስተላለፍ የስልጠና ብቃት አላቸው? በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት ተግባር መርሃ ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር እንዴት ይታያል?
3. ከመርሃ ትምህርቱ ትግበራ በኋላ በተማሪው ላይ የታየው የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ምን ያህል ነው?
4. የመማር ማስተማሩ ሁኔታ መርሃ ትምህርቱን ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ነው?
5. ትግበራውን በሙሉም ሆነ በከፊል ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች አሉ?

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ መካሄድ አስፈላጊ ነው። ትግበራና ግምገማ የአንድ ወቅት ክንዋኔዎች ሳይሆኑ በሂደት ላይ በየጊዜው የሚከናወ ኑ ናቸው። ግምገማ መረጃ የሚገኝበት፥ ለውሳኔ አሰጣጥ መነሻ የሚሆን የማያቋርጥ ሂደት መሆኑን ምሁራን (Stufflbeam 1971, Mc Donald 1973, Aspinwall 1992) የሚስማሙበት ነው። የመርሃ ትምህርቱን ብቃት ለማመልከት፥ በትግበራ ወቅት ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ለመፈለግ የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ ቸል የሚባል ጉዳይ እንዳልሆነ የመስኩ ምሁራን (Pratt 1980:343, Fullan 1992:37, Ornstein 1998:316) ይገልፃሉ። በመሆኑም ይህ ጥናት ከዚህ በታች ለተጠቀሱት አስፈላጊ ይሆናል፤

1. ከዚህ ጥናት ውጤት የኦሮሚያ ክልል የመርሃ ትምህርት አዘጋጆች (የአማርኛው ቡድን) የትኛው የመርሃ ትምህርት ክፍል በተገቢው ሁኔታ እንደተተገበረና የትኛው ክፍል እንዳልተተገበረ በመረዳት ወደፊት ለሚያደርጉት ማሻሻያ መነሻ ሊሆናቸው ይችላል፤

2. ውጤታማ የሆነ የትግበራ ሂደት በክልሉ እንዲኖር ሁኔታዎችን ለማመቻቸት መነሻ ይሆናል፤
3. በደረጃው ያሉ የቋንቋ መምህራን የታየባቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን ተገንዝበው ለመርሃ ትምህርቱ ትግበራ የበለጠ እንዲነሳሱ መረጃ ይሰጣል፤
4. በዚህ መስክ በኦሮሚያ ዞኖች እንዲሁም ተመሳሳይ የትምህርት ፕሮግራም በሚያካሂዱ ክልሎች ወደፊት ለሚደረጉ ጥናቶች በመነሻነት ያገለግላል።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞን በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ኢ-አፈ-ፈት ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ትግበራ በመገምገም ላይ ያተኩራል። በጥናቱ የሚካተቱት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ብቻ ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት በተገኘው መረጃ መሠረት የህዝብ፥ የኮምዩኒቲ፥ የሚሲዮንና የግል ትምህርት ቤቶች አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ እንጂ እንደሁለተኛ ቋንቋ የማያስተምሩ መሆኑ ስለታወቀ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሣ ድርሳናት

### 2.1. ስርዓተ ትምህርትና መርሃ ትምህርት፥

ስርዓተ ትምህርትና መርሃ ትምህርት በሁሉም የትምህርት ባለሙያዎች ዘንድ ተመሳሳይ ግንዛቤ ያላቸው አይደሉም። ገሚሶቹ ስርዓተ ትምህርትን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቀረፅ ፍልስፍናዊ፥ ማህበራዊና አስተዳደራዊ የትምህርት ጉዳዮችን አጠቃሎ የያዘ አገራዊ ሰነድ ነው ሲሉ አንዳንዶች ደግሞ ስርዓተ ትምህርት ዝርዝር የትምህርት ፕሮግራም እንደሆነ አድርገው ይገልፁታል። መርሃ ትምህርትን ደግሞ አንድ የትምህርት ዓይነትን ብቻ የሚያካትት ሰነድ እንደሆነና ዝርዝር የትምህርት ፕሮግራም የያዘ እንደሆነ ይገልፃሉ (UNESCO 1978:12)።

በሥነ ትምህርት ባለሙያዎች በአብዛኛዎቹ ተቀባይነት ያለው አንድምታ ስርዓተ ትምህርት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚነደፍ የአንድን አገር ፍልስፍና፥ የወቅቱን ምሁራን አመለካከት የያዘ፥ የተማሪውንና የማህበረሰቡን ፍላጎት ያገናዘበ የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ማስገኛ የትምህርት ፕሮግራም ነው።

ስርዓተ ትምህርት በጣም አጠቃላይ የሆነ እሳቤ (Concept) እንደሆነና ለማዘጋጀትም ፍልስፍናዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ሁኔታዎችን መሠረት እንደሚያደርግ (Allen 1984:6) ይጠቅሳሉ።


መርሃ ትምህርት በስርዓተ ትምህርት ላይ የሚመሠረት የመማር ማስተማር ክንውኖችን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በየደረጃው የሚታቀዱበትና የትምህርት ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ መንገድ የሚከፍትና የሚያመቻች እንደሆነ (Dubin እና Olshtain 1986:37) ይገልፃሉ። (Stern 1984:10) በበኩላቸው መርሃ ትምህርት ዝርዝር ዕቅድ መሆኑን፥ በስርዓተ ትምህርቱ የተነደፈው ዓላማ በማንና እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል የሚቀርብበት ዝርዝር የአፈፃፀም ዕቅድ እንደሆነ ያመለክታሉ። (Nunan 1988:7) ደግሞ (Van EK 1975) በመጥቀስ መርሃ ትምህርት በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን ርዕስ ጭምር ያካተተ፥ የቋንቋ ትምህርትን የያዘ፥ ተማሪው የሚሳተፍበትን የቋንቋ ተግባር የያዘ፥ በቋንቋ ረገድ ከተማሪው የሚጠበቀውን ተግባር የያዘ፥ በእያንዳንዱ ርዕስ ሥር ምን መከናወን እንዳለበት የሚገልፅ መሆኑን አስፍረዋል። የመርሃ ትምህርትና የስርዓተ ትምህርት ልዩነት ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት የሚወሰን ይሆናል።

## 2.2. የመርሃ ትምህርት ትግበራ

የመርሃ ትምህርትን ትግበራ በተመለከተ በርካታ ምሁራን ብያኔ ለመስጠት ተነሳስተዋል። አብዛኛዎቹ ማብራሪያዎች ተቀራራቢነት ያላቸው ናቸው። ለምሳሌ (Beauchamp 1968:132) "የመርሃ ትምህርት ትግበራ የታቀደውን ወደ ተግባር የመለወጥ ሂደት ነው።" ሲሉ (Giroux 1981:45-46) ደግሞ የመርሃ ትምህርት ትግበራ ሂደት ውስብስብነት ያለው፥ ችሎታና ፈቃደኝነት ያላቸው ተሳታፊዎች የሚገኙበት የትምህርት ፕሮግራም እንደሆነ ይገልፃሉ። የመርሃ ትምህርት ትግበራ አንድ ለውጥ የተካሄደበትን የትምህርት ፕሮግራም በተግባር ላይ ማዋል እንደሆነ የሚገልፁት (Fullan እናPomfret 1977:336) ናቸው። (Fullan 1991:65) አክለው ሲገልፁ ትግበራ አንድን አስተሳሰብ፥ ፕሮግራም ወይም ክንዋኔ በመለወጥ ሂደት ውስጥ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚታይበት ሂደት እንደሆነ ይገልፃሉ። (Ornstein እና Hunkins 1988:224) በበኩላቸው ጠቅለል ባለ መልክ ትግበራ በጊዜ ሂደት ውስጥ በግለሰቦች፥ በተወሰኑ ቡድኖች፥ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ውጤት ለማስገኘት የሚደረግ እንቅስቃሴ እንደሆነ ይጠቁማሉ።

ብያኔዎቹ ትግበራ በዕቅድ የተያዘ ጉዳይን ወደ ተግባር ማሸጋገር እንደሆነ የሚገልፁ ሆነው ይታያሉ። ስለዚህ ትግበራ በዕቅድ ላይ ያለ የትምህርት ፕሮግራም ወይም መርሃ ትምህርት በተግባር የሚታይበት ደረጃ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

የትምህርት ፕሮግራም ሲነደፍ ቀዳሚ ትኩረት የሚያገኘው አዘጋጆቹ በቂ ነው እስከ ሚሉ ድረስ ማቀድ ⟶ መሞከር ⟶ ማስተካከል ⟶ መሞከር ⟶ ማካሄድ ነው። በዕቅድ ደረጃ የት ድረስ መሄድ በቂ እንደሆነ ለመወሰን ቁርጥ ያለ ቀመር የለውም። አዘጋጆቹ እስካመኑበት ድረስ ብቻ ተዘጋጅቶ ለተግባር ሥራ ይቀርባል። (Shiundu እና Omulando 1992:61) የዝግጅቱን ሂደት በሚከተለው የዙር አካሄድ አስቀምጠውታል።




ቻርት 1. የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት፤ ተከታታይና ተዛናቂ ሂደት

(A continuous and integrated process)

የመርሃ ትምህርት ትግበራ በዕቅድ አውጭዎችና በተግባሪዎች መሀል የሚደረግ ተራክቦ እንደሆነ የሚገልፁት (Ornstein እና Hunkins 1988:292) ናቸው። ውጤት ሊያስገኝ የሚችል የመርሃ ትምህርት ትግበራ የሚመሠረተው በተጠቃሚው አካል፥ በመርሃ ግብሩና በአደረጃጀቱ ላይ ጥናት አካሂዶ በማቀድ ከዚያም ወደ ተግባር ለመለወጥ በመቻል ላይ መሆኑን ጨምረው ይገልፃሉ።


አንድ የትምህርት ፕሮግራም በአዲስ መልክ ሲዋቀር ተማሪው፥ መርሃ ግብሩ ያስፈለገበት ሁኔታና የማህበራዊ እርከን አደረጃጀቱ በለውጡ ሂደት ትኩረት ማግኘት ይኖርባቸዋል። ይህ ደግሞ በማስተማሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት፥ በመምህራን ስልጠና፥ በመዋቅር አደረጃጀት (Organizational structure)፥ በመርሃ ትምህርቱ ላይ ያለ መረዳትና አመለካከት (Understanding and attitude) እንዲሁም የተስተምህሮ ልምምድ (Learning practice) ላይ ለውጥ እንዲታይ ያደርጋል።

አዲስ የተነደፈ ወይም ተሻሽሎ የቀረበ መርሃ ትምህርት ትግበራ ላይ ዋለ ሊባል የሚችለው በመርሃ ትምህርቱ ተመስርተው በተዘጋጁ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ድጋፍ ዕቅዱ በመምህሩና በተማሪው መሀከል በሚደረግ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ሲታይ እንደሆነ (Brown 1994:159) ይገልፃሉ።

ትግበራ የሰመረ እንዲሆን በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካላት (አዘጋጆች፥ ኃላፊዎች፥ ርዕሣነ መምህራን፥ መምህራን) በትምህርት ለውጡና አሰጣጡ ዓላማ፥ ባህሪና ከለውጡ የሚገኘውን ጥቅም በሚመለከት የጋራ የሆነ ግንዛቤና አዎንታዊ (Positive) የሆነ አመለካከት ሊኖራቸው ያስፈልጋል። በየጊዜው የማያቋርጥ የሁለትዮሽ (Two-way) ግንኙነት በመርሃ ትምህርት አዘጋጆችና በመርሃ ትምህርት ተግባሪዎች መሀከል መዳበር ይኖርበታል። የትግበራን ውስብስብነት የጠቀሱት (Lewy 1977, Fullan 1981, Fullan 1991) በትግበራ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑት በርካታ አካላት በመሆናቸው ቅንጅቱ ጥንቃቄ የሚሻ እንደሆነ ያመለክታሉ።

ትግበራ ራሱን የቻለ ሂደት በመሆኑ ለብቻው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ እንጂ የዕቅድ ቀላል ተቀፅላ (Simple extension) ተደርጎ መታየት እንደሌለበት (Fullan እና Pomfret 1977:336) ይገልፃሉ። (Ornstein እና Hunkins 1998:297) ይህንኑ ሃሳብ ያጎለብታሉ። በመሆኑም የትምህርት ፕሮግራም በለውጥ ሂደት ውስጥ ያለ እንደመሆኑ የትግበራም ጉዳይ ራሱን ችሎ መታየት ያለበት እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

ትግበራ በታቀደ የለውጥ ሂደት ውስጥ ያለውን ድርሻ (Fullan 1981:310-311, Gene 1995:109-110) እንደሚከተለው በቻርት ገልፀውታል።




ቻርት 2 በታቀደ የለውጥ ሂደት ውስጥ የትግበራ ዕይታ

በቻርት ሁለት እንደተቀመጠው የተሻለ የትምህርት ውጤት ለማስገኘት በለውጡና በውጤቱ መሀከል ትግበራ እንደድልድይ ሆኖ ያገለግላል። ለውጤቱ ማግር ወይም አለማግር የትግበራ ጉዳይ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል። በትግበራ ላይ ትኩረት እንዲደረግ የሚያስገድዱ በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ። (Fullan እና Pomfret 1977:336-339) በዋናነት የሚጠቀሱ አራት ምክንያቶችን ይዘረዝራሉ። የመጀመሪያው በአንድ የትምህርት ሂደት ምን ለውጥ እየታየ እንደሆነ ለማወቅ በሥራ ላይ እያለ መገምገም ወይም መለካት ያለበት በመሆኑ፤ ሁለተኛው በርካታ የትምህርት ፕሮግራሞች ከታቀዱ በኋላ የተፈለገውን ግብ ለምን ማስገኘት እንዳልቻሉ በመረዳት ለለውጥ መነሳሳት፤ ሦስተኛው በትግበራ ሂደት የታየውን ጠንካራ ጎን ለማራመድና፥ የመጨረሻው፤ የተገኘውን የትምህርት ውጤት (Learning outcome) ለመተርጎምና የውጤቱ ማግር ወይም አለማግር ከየትኛው አካል ጋር (ከመምህሩና ከተማሪው፥ ከመምህሩና ከርዕሰ መምህሩ፥ ከመምህሩና ከዕቅዱ) እንደሚያያዝ ለመመዘን ትግበራን ለብቻው ማየት እንደሚገባ ይገልፃሉ።

## 2.3. የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ

ለረጅም ዘመናት ግምገማ በአንድ መምህር የሚሰጥና የተማሪዎችን ማለፍና መውደቅ ብቻ ለመወሰን የሚካሄድ እንደሆነ ተደርጎ ይታሰብ እንደነበር ድርሳናት ያስረዳሉ። በርካታ መምህራን ግምገማን ከፈተና መስጠት ያለፈ አድርገው አያስቡም ነበር። ሆኖም ግምገማ በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም። በርግጥ ፈተና የግምገማ ማካሄጃ አንድ ፈርጅ ሊሆን

ይችላል። በግምገማ የሚታየው የተማሪው ፈተና ውጤት ብቻ ሳይሆን የትምህርት ፕሮግራሙ ጭምር ነው። (Tyler 1949:105-106) እንደሚሉት፤ "ግምገማ የትምህርት ዓላማው በመርሃ ትምህርቱና በትግበራው ሂደት ምን ያህል እውናዊ ሆኖ እንደታየ የሚለካበት ነው።" ይህ የ'Tyler' ሃሳብ በዘመኑ በርካታ ምሁራንን ያነቃና ግምገማ ለተማሪው ፈተና በመስጠት ብቻ የሚወሰን እንዳልሆነ እንዲረዱ አስችሏል።

የመርሃ ትምህርት ግምገማን በሚመለከት ምሁራን አስተያየቶቻቸውን ሰንዝረዋል። እንደ (Taba 1963:311-315) የአንድ ትምህርት ፕሮግራም ግምገማ መረጃን ለመስጠት የሚያስችል ከመሆኑም በላይ የተማሪዎቹን ብቃት በመለካት ድክመቱንና ጥንካሬውን ለማሳየት የሚያስችል መሆኑን ይገልፃሉ። (Stenhouse 1975:112) የጠቀሷቸው (Mc Donald 1973) ደግሞ መረጃዎችን ለትምህርት ሰጪ አካላት በማቅረብ መርሃ ግብሩ ምን ያህል ግቡን እንደመታ የሚታይበት ነው ይላሉ። (Mc Cormic 1983:172) ደግሞ ግምገማ የመረጃዎች ስብስብ ሲሆን ስለ አንድ የትምህርት ፕሮግራም ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃሉ። (Nixon 1989:119) ግምገማ መረጃ የሚገኝበት ሂደት መሆኑን ጠቅሰው ውሳኔ ለመስጠት መነሻ እንደሚሆን ገልፀዋል።

የመርሃ ትምህርት ግምገማ ዕቅዱ በክፍል ውስጥ እንዴት ተግባራዊ ሆኗል? መምህራኑ የተዘጋጁትን የማስተማሪያ መሣሪያዎች በተገቢው መንገድ ይጠቀማሉ? መምህራኑ ከታቀደው በላይ ለመስራት ያሳዩት ጥረት ምን ያህል ነው? የትኛው የመርሃ ትምህርቱ ክፍል ተከናውኗል? ያልተከናወነው የትኛው ክፍል ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንደሚያስችል (Brandt 1981:42-43) ይናገራሉ።

የመርሃ ትምህርት ግምገማ ጠቃሚ ጎኑ የጎላ መሆኑን (Stern 1992:41) ከመግለፃቸውም በላይ የትምህርት ሂደት ዑደታዊ በመሆኑ በየጊዜው ማሻሻያ ሊደረግበትና እ የተለወጠ መሄድ ያለበት መሆኑን ለዚህ ደግሞ ግምገማ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ያስገነዝ ባሉ። የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ዑደታው መሆኑን (Shiundu እና Omulando 1992:61) ሲያቀርቡ ግምገማም የዑደቱ አንድ አካል እንደሆነ ገልፀዋል።

በአንዳንድ የግምገማ ምርምሮች ላይ የመርሃ ትምህርት ግምገማና የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ አደናጋሪ ሆነው ይገኛሉ። የሁለቱ ግምገማዎች ልዩነት ተለይቶ ሊታወቅና ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ሊያዝበት ያስፈልጋል። (Ornstein እና Hunkins 1998:320-322) ላይ እንደተጠቀሰው በመርሃ ትምህርት ግምገማና በመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ ያለው ልዩነት መታወቅ ይኖርበታል። ልዩነቱም የመርሃ ትምህርት ግምገማ የትምህርት ፕሮግራምን በተናጠል መገምገም ነው። በውጤቱ ላይ ሳይሆን የመርሃ ትምህርቱን ገፅታ በማጥናት ላይ ያተኩራል። በግምገማው የዓላማዎች አነዳደፍ ብቃት ሊታይ ይችላል፤ ግልፅነቱ፥ ተተግባሪነቱ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ይዘትና ጥራት፥ የይዘቱ ተገቢነትና የሚሸፍነው ጊዜ ሊካተት

ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ የቀረበው ዕቅድ የታለመለት ግብ ላይ ሊያደርስ በሚችል መልኩ (Intended plan) ምን ያህል ወደ ተግባር እንደተለወጠ የሚታይበት ነው። የትግበራ ግምገማ የመርሃ ትምህርቱ ተግባራዊ ክንውን የሚገለፅበት ሲሆን የመርሃ ትምህርት ግምገማ በቀረበው ሰነድ ላይ ያለው አወቃቀር የሚገለፀበት ነው። በትግበራ ሂደት የሚደረግ ግምገማና የሚገኘው ውጤት ቀደም ሲል ታቅዶ በነበረው ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊታሰብ የሚችል ነው። አንድ ዕቅድ ተግባራዊ ሆኗል ወይም አልሆነም ለማለት በሰነድ ላይ የተመሰረተ ጥናት ብቻውን በቂ አይሆንም ስለዚህ የትግበራ ግምገማ ማካሄድ የግድ ሆኖ ይገኛል።

በመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ ሰፋ ያለ የትግበራ ግምገማ ለማካሄድ በርካታ መረጃዎችን ከተለያዩ አቅጣጫዎችና በሂደቱም ተሳታፊ ከሆኑ አካላት መሰብሰብ ተገቢ ነው። ግምገማውም እንደ ግምገማው አካሄድ የተለያዩ ሞዴሎችን ሊከተል ይችላል። (Ornstein እና Hunkins 1998:327) የጠቀሱት "Provus's Discrepancy Evaluation Model" አንድ ስልት ነው። ይህ ሞዴል በአራት ደረጃዎች የተዋቀረ ነው። አንደኛው የፕሮግራሙን ደረጃ መወሰን (Determining program standard) ነው። ሁለተኛው የፕሮግራሙን ብቃት መወሰን (Determining program performance) ሲሆን ሦስተኛው በፕሮግራሙ ደረጃና ብቃት መሀከል ንፅፅር ማካሄድ (Comparing performance with standard) ነው የመጨረሻው ደግሞ ልዩነት እንዳለና እንደሌለ መወሰን (Determining whether a discrepancy exist between performance and standard) ነው። በዚህ ሂደት በእያንዳንዱ ደረጃ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ሁኔታ ይታያል። ይህም ወደሚቀጥለው ደረጃ ለማለፍ አስፈላጊ ነጥብ ነው። (Popham 1993:28) የተጠቀሰው ስልት "Judicial approach to evaluation" ሲሆን ስለቀረበው የትምህርት መርሃ ግብር ተቃዋሚና ደጋፊ የሆኑ ቡድኖች በሚያካሂዱት ክርክር በመሀል የሚሰየሙት ሁኔታውን በመገምገም ስለትምህርት ፕሮግራሙ ብያኔ የሚሰጡበት የግምገማ ስልት ነው። "CIPP" በመባል የሚታወቅ ሞዴል ያቀረቡት (Stufflbeam 1983) ናቸው። ሞዴሉ አራት ጉዳዮችን አጣምሮ በመያዝ ለመፈተሽ የሚያስችል ነው። የመጀመሪያው የአውድ ግምገማ (Context evaluation) ሲሆን ከፍላጎት አሰሳ (Needs assessment) ጀምሮ እስከ ትምህርት አውድ ድረስ ያለው የሚገመገምበት ነው። የቀረበው ግብአት ለተፈለገው ግብ በቂ መሆኑ የሚመዘንበት የግብዓት ግምገማ (Input evaluation) ሁለተኛው ነው። ሶስተኛው ደግሞ ሂደታዊ ግምገማ (Process evaluation) ሲሆን ግብዓቱ እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ የሚታይበት ነው። የመጨረሻው በሂደቱ የተገኘው ውጤት የሚመዘንበት የውጤት ግምገማ (Product evaluation) ነው። ይህ ሞዴል አዲስ ስርዓተ ትምህርት ሲዘጋጅ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ነው።

ሌላው የግምገማ ሞዴል (Stake 1967) የቀመሩት ሲሆን ሦስት ዓበይት ተላውጠዎችን ይይዛል። ሞዴሉ ቀዳሚ ነገር (Antecedent) መስተጋብር (Transaction) እና ውጤት (out come) ላይ የተመሰረተ ነው። በቀዳሚ ነገር ውስጥ የተማሪውና

የመምህሩ ሁኔታ፣ ማህበር ፖለቲካዊ ሁኔታ የሚታይበት ነው። በተለይ በተነደፈው መርሀ ግብር የመምህሩ መረዳት (Understanding)፣ እምነት (beliefs)፣ ችሎታ (ability)፣ መርሀ ትምህርቱን ለመተግበር ከመቻል አቅም ጋር የሚታይበት ነው።

በተራክቧዊ ግኑኝነት ጊዜ ትኩረት የሚሰጠው በክፍል ውስጥ የሚኖረው ክንውን ነው። የቀዳሚው ነገርና የተራክቦ ተጣጥሞሽ መገለጫው ውጤት ነው። (Posner 1992:229) የ(Stake 1967) የግምገማ ሞዴልን እንደሚከተለው ገልፀውታል።

ቀዳሚ ነገር → ተራክቦ /መስተጋብር/ → ውጤት

ቻርት 3 የቀዳሚ ነገር የተራክቦና የውጤት ግንኙነት

የStake 1967 የግምገማ ሞዴል በታቀደውና (intended) በታየው (observed) መካከል ያለውን ተጣጥሞሽ ለማነፃፀር አመቺ እንደሆነ (Omstein and Hunkins 1998:329) ያስገነዝባሉ።

ሞዴሎቹ ያላቸውን የየራሳቸውን ልዩነት ጠብቆ በሁለት ትልልቅ ጎራ መክፈል ይቻላል፤ የቀደሙት ሁለት ሞዴሎች ዓላማ መራሽ (Objective oriented) ሊባሉ ሲችሉ የኋለኞቹ ሁለቱ ደግሞ ሂደት ተኮር (Process oriented) ሊባሉ ይችላሉ። ሂደት ተኮር የግምገማ ሞዴሎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ከማሳየታቸውም በላይ ተማሪው በሂደቱ ያስመዘገበውን ውጤት ሊያሳዩ የሚችሉ መሆናቸው የሚጋሩት ባህሪ ይሆናል።

## 2.4 የመርሀ ትምህርትን ትግበራ የሚወስኑ ተላውጦዎች /Variables/

የትምህርት ፕሮግራምም ሆነ የመርሀ ትምህርት ዝግጅት ካለው የውስብስብነት ባህሪ የተነሳ በርካታ ጉዳዮች ይነሳሉ። እነዚህም ጉዳዮች ክንውኑን የሚያመቻቹና የሚያራምዱ ያለዚያም የሚያደናቅፉና የሚገቱ ይሆናሉ። የአብዛኞዎቹ የትምህርት ፕሮግራሞች ችግር የሚከሰተው ለማቀድ የሚሰጠውን ትኩረት ያህል ለትግበራው ባለመስጠታቸው እንደሆነ ይታወቃል። እንደ (Fullan 1991:19) ለትግበራ ሊደረግ የሚገባውን ስልጠናና ድጋፍ ወደ ጎን መተው፣ በሂደቱ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት ቸል ማለትና ፕሮግራም ማውጣት ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ ከትግበራው የሚገኘውን ውጤት ደካማ እንደሚያደርገው ይገልጻሉ።


የትግበራ ሂደት የለውጥ ሂደት ነው። በዚህ ሂደት በርካታ እንቅፋቶች ሊከሰቱ ይችላሉ። (Fullan 1991:66-80) የትግበራን ሂደት በዋናነት ሊወስኑ የሚችሉ ሶስት ዋና ዋና ነጥቦች አስቀምጠዋል። እነሱም የለውጥ ባህሪ፣ የለውጥ ተሣታፊዎች ሚና እንዲሁም ለውጡን ተግባራዊ ለማድረግ ያለው አደረጃጀት ናቸው። /ቻርት 2 ያነጻጽራል/

### 2.4.1 የለውጥ ባህሪ

የለውጥ ባህሪ በግልጽነት (Clarity) እና በውስብስብነት (complexity) ላይ የተመሰረተ ነው። ግልጽ መሆን የሚያስፈልገው ስለትምህርቱ ግብና ወደ ግቡ ስለሚያደርሰው መንገድ (Goals and means) የሚኖረው የጠራ አስተሳሰብ ነው። ይህም በዕቅድ አውጭዎችና በተግባር ተሳታፊዎች መሀል የሚኖር የመግባባት ሁኔታ ነው። ለምሣሌ በማዕከል ደረጃ የተነደፈ የትምህርት ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረገው በት/ቤት ደረጃ ነው። ት/ቤት ያለው ደግሞ መምህሩ ነው። ስለዚህ መምህሩ ስለግቡና ወደ ግቡ ለመሄድ የታቀደውን መንገድ ሊረዳ (Understand) ይገባል። ይህ ካልሆነ የትግበራው ሂደት በሙሉም ሆነ በከፊል ሊደናቀፍ ይችላል። ስለዚህ ለትግበራ ሂደት የለውጡ ባህሪ ግልጽ ሆኖ መቀመጥ አለበት። አዲስ የትምህርት ስርዓት በተዘረጋ ቁጥር የለውጡ ሁኔታ በተሣታፊዎቹ ዘንድ ግንዛቤ እንዲያገኝ አስፈላጊው ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

የለውጡ አስፈላጊነትና ባህሪ ግልጽ በሆነ መጠን ትግበራውም ይበልጥ ሊሳካ ይችላል። የትምህርት ሂደት በለውጥ የታጀበ በመሆኑ ለውጡ በተግባር ተሣታፊዎቹ ዘንድ ግልፅ መሆኑ ለስኬቱ የራሱ ድርሻ አለው።

ውስብስብነት ለውጡ የሚፈልገውን አካሄድ በተመለከተ ሃላፊነት የተጣለባቸው አካላት የሚኖራቸውን ድርሻ ይመለከታል። ለውጥ ሲካሄድ የተለያዩ አካላትን ያሳትፋል (ይነካል)። ለውጡ በአንድ ቦታ ተወስኖ የሚታይ ላይሆን ይችላል። ለውጡን በሃላፊነት እየመሩ የሚያራምዱ አካላት ችሎታ፣ አመለካከት፣ እምነት፣ የማስተማር ስልት (Teaching strategy)፥ የማስተማሪያ መሣሪያዎች አጠቃቀም የትግበራውን ሁኔታ ከውስብስብነት አኳያ የሚወስኑት ናቸው። ከዚህ አንጻር (Fullan 1991:68) የትምህርት ፕሮግራም ውስብስብ ጉዳዮችን የያዘ ከሆነ ተግባር ላይ የሚያውሉትና የሚሳተፉት አካላት በተለያዩና በተለዋወጡ ቁጥር ውጤቱ የተለያየ እንዲሆን ያደርገዋል በማለት ይገልጻሉ። የአንድ ትምህርት ፕሮግራም ውስብስብ አለመሆን ተገላጭነቱን የሚያጎላው ሲሆን በሌላ አንጻር ሲታይ ደግሞ ውስብስብነቱ ተገላጭ መሆኑን ይቀንሳል። የመርሃ ትምህርት ውስብስብነትንና የትግበራን ተዛምደዊ ግንኙነት (Fullan እና Pomfref: 1977) እንደሚከተለው በቻርት ገልጸውታል።




ቻርት 4 ውስብስብነትና የትግበራ ተዛምዶ

የተነደፈው የትምህርት ፕሮግራም ውስብስብ ካልሆነና በትግበራው ተሣታፊዎች በቂ ግንዛቤ የተያዘበት ከሆነ የትግበራው ሂደት ከፍ እንደሚል፣ በአንጻሩ የፕሮግራሙ ውስብስብ ነት ያየለ ከሆነና በትግበራው ተሣታፊዎች የሚኖረው ግንዛቤ አናሳ ከሆነ ጥርጣሬንና ፍርሃ ትን ከማሳደሩም በላይ ዝቅተኛ የትግበራ ሂደት እንዲታይ ያደርጋል። የዚህ ውጤት ደግሞ ደካማ የትምህርት ውጤት (Poor educational outcome) ሊሆን እንደሚችል መገመት አዳጋች አይሆንም።

ስለዚህ የለውጡን ባህሪ ግልጽ በሆነና ውስብስብ ባልሆነ መልክ ማደራጀት ትግበራ ውን ውጤታማ የሚያደርገው መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል። ምንም እንኳ የትምህርት ሂደት በለውጥ ላይ ያለ ቢሆንም የለውጡን ሁኔታ ግልፅ በማድረግ ውስብስብነ ቱን በመቀነስ የትግበራውን ደረጃ ከፍ ማድረግ እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል። የሚነድፈ ው ዕቅድ (Intent) ግልጽና ያልተወሳሰበ መሆን የሚገባው ሲሆን በሁሉም ወይም በአብዛኛ ዎቹ የትግበራው ሂደት ተሣታፊዎች ተመሳሳይ በሆነ መልኩ እንዲረዱ በሚያስችል መልኩ መቅረብ ይኖርበታል።

## 2.4.2 የለውጥ ተሣታፊዎች ሚና፣

ትምህርት ቤት አንድ የትምህርት ፕሮግራም በተግባር የሚውልበት ሥፍራ ነው። መምህሩና ርዕሰ መምህሩ በዋናነት የትግበራውን ሚና የሚጫወቱ አካላት ናቸው። እነዚህ አካላት መርሃ ትምህርቱን ከመተግበር አኳያ ውጤታማ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ጉልህ ድርሻ አላቸው።

### 2.4.2.1 ርዕሳነ መምህራን

የየትምህርት ቤቱ ርዕሳነ መምህራን ለትምህርት ቤታቸው ካላቸው ተጠሪነት የተነሣ የመርሃ ትምህርትን ትግበራ ከመምህሩ ጋር በመሆን በማመቻቸት ዋና ተሣታፊዎች ናቸው። (Fullan 1991:143) የየትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን ሚና በተመለከተ ሲገልጹ፤ የማስተማሪያ ቦታ ማዘጋጀት፣ ተገቢ ሥልጠና ያላቸውን ሰዎች በመመደብ የትግበራን ሂደት የሚያግዙ በትግበራ ሂደት በማደናቀፍም ሆነ በማመቻቸት በኩል ቀላል የማይባል ሚና የሚጫወቱ ናቸው ይላሉ።

ርዕሳነ መምህራን በትግበራ ሂደት መሪዎች ናቸው። ይህም በመሆኑ አንድ አዲስ የትምህርት ፕሮግራም ከሚነደፍበት ጊዜ አንስቶ እስከ ትግበራው ድረስ ርዕሳነ መምህራን ተሣታፊ መሆናቸው አስፈላጊ ነው። በትግበራው ሂደት ለመምህራኑ ተገቢ ድጋፍ በመስጠት በኩል የሚጠበቅባቸውን ድርሻ በብቃትና በንቃት ለመወጣት ያስችላቸው ዘንድ ነው። (Ornstein and Hunkins 1998: 228-243) ርዕሳነ መምህራን ለውጤታማ ትግበራ ቁልፍ የሆኑ ሞተሮች ናቸው በማለት ይገልጻሉ።

የሙያ ብቃት ያላቸው ርዕሳነ መምህራን የመምህሩን ጥያቄ በማስተናገድ ፍላጎቱን በማሟላት በትምህርት አሰጣጡ ላይ የዕለት ተዕለት ክትትል ያደርጋሉ። በየጊዜውም

የክፍል ውስጥ ምልከታ በማካሔድ ምን እየተከናወነ እንደሆነ ይከታተላሉ። የራሳቸውን የሙያ ልምድ በማካፈል ሰላማዊ የመማር ማስተማር ክንውን እንዲኖርና መልካም የትግበራ ሂደት እንዲሰፍን ይጥራሉ።

ከመምህሩ ጋር በመመካከር፣ ዕውቀታቸውን በማካፈል፣ የትምህርት ቤቱን የትምህርት አሰጣጥ ማሻሻልና ብሩህ የሆነ ግብ ማመላከት የርዕሳነ መምህራን ሚና ነው። (Fullan 1991:151) ርዕሳነ መምህራን ሚናቸው ከላይ የተዘረዘረውን ቢመስልም አንዳንዶቹ ርዕሳነ መምህራን የቅርብ አመራር ሰጪና ተባባሪ ከመሆን ይልቅ የአስተዳዳሪነትና የበላይነት ባህሪ እንደሚታይባቸው አንዳንዶቹ ርዕሳነ መምህራን ከተግባር ተሳታፊነታቸው ይልቅ የአዛዥነትና የገለልተኝነት ባህሪ እንደሚታይባቸው በመግለጽ ለትምህርቱ ፕሮግራም ለውጥ ወይም ትግበ ራ ክትትል ያላቸው ጊዜ በጣም አናሳ መሆኑን ጠቁመዋል።

ርዕሳነ መምህራን ከሥራ ሰዓታቸው አብዛኛውን ለአስተዳደራዊና ለሌሎች ጉዳዮች ከማዋል ይልቅ የትምህርት ሂደቱን በመከታተል ላይ መመደብ ይኖርባቸዋል። የአዛዥነትና የበላይነት ከማሣየት ይልቅ ተባባሪነትንና አጋዥነትን ማዳበር ይኖርባቸዋል። ይህም የትግበራ ውን ስኬት ያጎለብታል።

## 2.4.2.2 መምህር

በትግበራ ሂደት የንቁ ተሳታፊነት (Active participant) ሚና የሚጫወተው መምህሩ ነው። ምክንያቱም ትግበራ በክፍል ውስጥ በመምህሩ መሪነት የሚከናወን በመሆኑ ነው። (Nunan 1988:7) መምህሩ በመንግስታዊ አካላትና በተግባራዊ ሊቀ ሥነ ልሳናት የተዘ ጋጀውን የማስተማር ዕቅድ በቀጥታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚያደርግ እንደሆነ ገልጸዋል።

በአንድ ትምህርት ቤት ያሉ መምህራን የመርሃ ትምህርቱን ለውጥ በጥሩ ጎኑ ካላዩትና ካልተቀበሉት ወይም ደግሞ ካልተረዱት ለውጡ ተግባራዊ ይሆናል ማለት እንደማ ይቻል (Gene 1995:173) ይጠቁማሉ። በትምህርት ቤት ደረጃ ለሚታየው ለውጥ በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ያለው ትግበራ ቀጥተኛ የሆነ ድርሻ አለው። የመምህሩ ተሳትፎ ወሳኝ በመ ሆኑ መምህሩ ሊተኮርበት እንደሚገባ የመስኩ ምሁራን (Fullan 1991:117-124 Ornstein እና Hunkins 1998:22) ጠቅሰዋል። በሌላ በኩል ምንም እንኳ መምህሩ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ቢሆንም የመምህሩ የሙያ ብቃት ብቻውን ለግቡ ወሳኝ አለመሆኑን ጠቅሰው ለውጤቱ መልካም መሆን የዕቅዱ አዘጋጆችና የትግበራው ተሣታፊዎች ተዋህደው ለአንድ አላማ የተነሱ መሆን እንደሚኖርባቸው ያስረዳሉ። ይህም ሆኖ ለጥሩ የትግበራ ሂደት የመምህሩ አመለካከ ት ካልተለወጠ ምንም ቢታቀድ ውጤቱ የተፈለገውን ያህል ሆኖ ላይገኝ እንደሚችል ምሁራኑ አበክረው ያስረዳሉ።

በመሆኑም አንድ የትምህርት ፕሮግራም በአዲስ መልክ ሲታቀድ ወይም ማሻሻያ ሲደረግ መምህሩ ቀጥተኛ ተሣታፊ እንዲሆን መድረኮቹን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

### 2.4.3. ለመርሃ ትምህርት ትግበራ የአስተዳደራዊ አወቃቀር ድርሻ፣

አደረጃጀት በትግበራ ሂደት የራሱ የሆነ ድርሻ አለው። በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሰው ሃይል በብዛትና በጥራት መገኘት በመምህራኑና በትምህርት ቤቱ አስተዳደር የሚኖረው ግንኙነት፣ በመምህራኑና በመርሃ ትምህርቱ አዘጋጆች መሀል የሚኖረው ግንኙነት፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች በብዛትና በብቃት መዘጋጀትና መዳረስ የአደረጃጀት ጉዳይን የሚመለከት ነው። ትምህርት ቤቱ ከአካባቢው ማህበረሰብ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ያለው አግባብ በአደረጃጀቱ ሂደት የሚካተቱ ናቸው። የትምህርት ቤቱ አስ ተዳደር በትግበራ ሂደት እውነተኛና ተገቢ የሆነ ድጋፍ የሚያደርግ ከሆነ ውጤቱ ከፍተኛና የተፈለገውን ያህል እንደሚሆን እሙን ነው።

የመምህራንን ሙያ ተከታታይ በሆነ መልክ ለማሳደግ መጣር የአስተዳደሩ ድርሻ ነው። በአንድ ቀን የሚጠናቀቁ ወርክሾፖችን ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ዘላቂና ተከታታይነት ያላቸው ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት መምህራንን ተሣታፊ ማድረግ የትግበራውን ሂደት ያጎለብተዋል።

በትግበራው ሂደት ከመምህራን ጎን በመቆምና የዕለት ተዕለት ክትትል በማድረግ የሚከሰቱ ችግሮችን በየደረጃው መፍታት የትምህርት ቤት አስተዳደር ድርሻ ነው። ሆኖም የመምህሩን ሥነ ልቡናዊ ዝግጅት ሳይጠብቁና አመለካከቱን ለመለወጥ ጥረት ሳያደርጉ ከበላይ አካል የመጣውን መመሪያ እንዳለ በሥራ ላይ እንዲውል ጫና ቢያደርጉ በዕቅድ ደረጃ የታለመው ውጤት በትግበራው ሂደት ሊደናቀፍ ይችላል። ስለዚህ አስተዳደሩና መምህሩ እጅና ጓንት ሆነው ለትግበራ ሂደት መነሳሳት ይኖርባቸዋል።

ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁስ ማሟላት የትምህርት ቤት አስተዳደር ሃላፊነት ነው። በርካታ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት የሚረዱ ቁሳቁስን ባለማሟላታቸው የትግበራ ሂደት ሲደናቀፍ ይስተዋላል። (Pratt 1994:258) የተሳካ ትግበራ እንዳይኖር ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል ተገቢና ብቃት ያላቸው የማስተማሪያ መሣሪያዎች አቅርቦትና ቁስቁስ አለመሟላት እንደሆነ ይገልጻሉ። (Ross እና Postlethawite 1992:28) ባጠኑት ጥናት በታዳጊ አገሮች ባሉ አብዛኞቹ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የሚማሩት መሬት ላይ ተቀምጠው እንደሆነ፣ በየክፍላቸው ውስጥ ጥቁር ሰሌዳ ላይኖራቸው እንደሚችል፣ መቀመጫም ሆነ ጥቁር ሰሌዳ ቢኖራቸው እንኳ ከበቂ በታች መሆናቸውን አመልክተዋል። ይህ ደግሞ የትግበራውን ሂደት እንደሚያጓትት ይታመናል።

የመርሃ ትምህርት ትግበራን የሚያደናቅፉ ተላውጠዎች (የለውጥ ባህሪ፣ የለውጥ ተሣታፊዎች ሚናና የትግበራ አወቃቀር) በዕቅድ ደረጃ የቀረበው የትምህርት ፕሮግራም በሙሉ ወይም በከፊል እንዳይሳካ ሊያደርጉ የሚችሉ ወሳኝ ጉዳዮች መሆናቸውን መገንዘብ ተገቢ ነው።

የመርሃ ትምህርት ለውጥ ወይም ማሻሻያ ሲደረግ ለውጡ ሊታይ የሚችለው

በአምስት መልክ ሊሆን እንደሚችል (Fullan እና Pomfret 1977:361-365) ይገልጻሉ። እነዚህም አንደኛ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ለውጥ ሲሆን ለተማሪው የሚቀርብለትን የይዘት ለውጥ ይመለከታል። የአደረጃጀት ለውጥ ሁለተኛው ሲሆን ተዋረዱን በጠበቀ ሁኔታ የሚኖረው የአወቃቀር ለውጥ ነው። ሶስተኛው፣ የሚናና የባህሪ ለውጥ ነው። በመምህሩና በሌሎች መምህራን፣ በመምህራንና በተማሪዎች፣ በመምህራኑና በድጋፍ ሰጪ አካላት መሀል ያለው ግንኙነትና ሚና ለውጥ ይታይበታል። አራተኛ፣ የግንዛቤና የዕውቀት ለውጥ ነው። በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሆኑት አካላት ለለውጡ ያላቸው መረዳት ምን ያህል እንደሆነ የሚታይበት ነው። አምስተኛው፣ የአመለካከት ለውጥ ነው። በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ሂደት ተሣታፊ የሚሆኑ አካላት ሁሉ በጎ አመለካከትና ቅንነት የሚመለከት ነው።

ስለዚህ አንድ የትምህርት ፕሮግራም ሲታቀድና ለተግባራዊነት ሲዘጋጅ የትግበራውን ሂደት ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎችን በመለየትና በማጤን በቂ ዝግጅት በማድረግ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን መቀነስ ብሎም ማስወገድ ይቻላል።

አዲስ የትምህርት ፕሮግራም ሲነደፍም ለውጡ የሚነካካቸውን አካላት ሁሉ ያሳተፈ ወርክ ሾፕ፣ ሴሚናር፣ ተከታታይ ስልጠና በማዘጋጀት ለትግበራው የሚኖረውን ተነሳሽነት ማጎልበት ይቻላል። በውጤቱም በዕቅድና በትግበራ መሀል ጉልህ የሆነ ተጣጥሞሽ መመልከት ያስችላል።

በዚህ ሂደት ተማሪውም ሊታቀፍ ይገባል። ተማሪው አላማዬ ብሎ የተነሳበትን የመማር ፍላጎት በሚያረካ መልኩ መቀናጀት ይኖርበታል። ለምሳሌ በቋንቋ ትምህርት የአፍ መፍቻ ቋንቋን የመማር አላማ የሁለተኛ ቋንቋን ከመማር አላማ የተለየ ነው። ይህንን የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። የተማሪውን የመማር ፍላጎት፣ ዝንባሌ ና ዓላማ መሰረት በማድረግ መርሃ' ትምህርት መዘጋጀት እንዳለበት (Fullan እና Pomfret 1977:38) ይናገራሉ። ተማሪውም ለሚማረው ቋንቋ ያለው ፍላጎት፣ ዝንባሌና የመማር ዓላማ በመርሃ ትምህርቱ ዝግጅት ወቅት ትኩረት ሊያገኝ ይገባል። ይህ ከሆነ ደግሞ በትግበራው ተሳታፊ ከመሆኑም በላይ ለውጤቱም ድርሻ ይኖረዋል።

በመርሃ ትምህርት የሚቀርቡ አላማዎች ለተማሪው ጻራ ትኩረት መስጠት እንዳለባቸ ው (Ornstein እና Hunkins 1998:312-316) ይጠቁማሉ። ይህን ሃሳብ (Nunan 1988:55) ይጋራሉ። የተማሪውን ፍላጎት ለመረዳትም የባህሪ ጥናት ማካሔድ፣ ውይይት ማድረግ፣ መጠይቅ ማስሞላት እንደሚቻል ያብራራሉ። የሚካሔደው ጥናት በትግበራው ሂደት ተሳታፊ የሆኑ መምህራንንም ማቀፍ የሚኖርበት ሲሆን በፍላጎት አሰሳው የማህበረሰቡ፥ የርዕሳነ መም ህራንና የድጋፍ ሰጪ አካላት ተሳትፎ መታከል እንዳለበት ያስገነዝባሉ።

## 2.4.4 የማስተማሪያ መሣሪያዎች ቅንጅት

መርሃ ትምህርት የመምህር መምሪያና የተማሪ መጽሐፍት በትግበራ ሂደት ሥራ ላይ የሚውሉ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ናቸው። መርሃ ትምህርት በማዕከል ደረጃ፣ በክልል

ደረጃ ወይም በትምህርት ቤት ደረጃ ሊዘጋጅ እንደሚችል ድርሣናት ያስረዳሉ። ከመርሃ ትምህርት በመነሣት ዝርዝር ይዘትንና ተግባርን ያካተቱ የመምህር መምሪያ (የመምህሩ መጽሀፍ) እንዲሁም የተማሪ መጽሀፍ በየደረጃው ይዘጋጃሉ።

በኢትዮጵያ የትምህርት አወቃቀር መሠረት መርሃ ትምህርትም ሆነ ሌሎቹ የማስተማ ሪያ መሣሪያዎች የሚዘጋጁት በማዕከል ደረጃ ወይም በክልል ደረጃ ነው። በተለይ የመርሃ ትምህርት ዝግጅት የሚከናወነው በሥርዓተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም (ICDR) ሲሆን የመምህር መምሪያና የተማሪው መጻሕፍት እንደየሁኔታው በዚሁ ተቋም ሲዘጋጁ በክልል ደረጃም ይዘጋጃሉ።

በመሆኑም ማስተማሪያ መጻሕፍቱ በተለያየ አካል ስለሚዘጋጁና በስርጭትም ወቅት ሶስቱም የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተመጣጣኝ ላይሆን ስለሚችል ቅንጅቱን መመርመር ተገቢ ነው። አልፎ አልፎ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ከተማሪው መጽሐፍ በስተቀር መርሃ ትምህርቱና የመምህሩ መምሪያ ጨርሶ ላይገን ይችላል። በተማሪው መጽሐፍ የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት ለማከናወን አዳጋች ሊሆን ይችላል። በመሆኑም በትግበራው ቀጥተኛ የሆነው መምህር እጅ የሚገባው የተማሪው መጽሐፍ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ ሲካሄድ በማስተማሪያ መሣሪያዎች መካከል ያለውን ተቀራርቦሽ መቃኘቱ ተገቢ ነው። በማስተማሪያ መሣሪያዎች መካከል ያለውን ግንኙነት መፈተሽ ራሱን የቻለ አንድ ጥናት ነው። ይህም የይዘት ትንተና (Content analysis) ሲሆን በመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ ጥናት በመጠኑ የሚታይ ይሆናል። ይህም ጥምረት መኖር በተማሪው መጽሐፍም ሆነ በመርሃ ትምህርቱ የሰፈረውን ተቀራራቢነት የሚያመለክት ሲሆን ግምገማውን የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ ሊያሰነው ይችላል። በሁለቱ የማስተማሪያ መሣሪያዎች መካከል ጥምረት ከሌለ ቀድሞ መስራት ያለበት የጥምረት ጉዳይ ላይ እንጂ የመርሃ ትምህርት ትግበራ ላይ መሆኑ ይቀራል። የዚህም ውጤት የመርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ ውጤት ላይሰኝ ይችላል። በመሆኑም በመርሃ ትምህርቱ በመምህሩ መጽሀፍና በተማ ሪው መጽሀፍ መካከል ያለው ተጣጥሞሽ ታይቷል። (አባሪ አንድ ይመልከቱ)

በአገር ውስጥ ሁለተኛ ቋንቋን በተለይ አማርኛን ከማስተማር ጋር የተያያዙ ጥናቶች ስንመለከት በቅድሚያ የምናገኘው፣ "ትግርኛ አፍ መፍቻቸው ለሆናቸው ተማሪዎች የተዘጋጀ ው የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል የአማርኛ ትምህርት ያካተታቸው ይዘቶችጥናት"። በሚል ርዕስ ጥላሁን ገብረ ክርስቶስ በ1990 ያካሄደው የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ነው። በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገው በቀረበው ይዘት ላይ ነው። በውጤቱም በክልሉ ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል በመርሃ ትምህርቱ ተዘጋጅተው የቀረቡት ይዘቶች ከተማሪው ችሎታ በላይ መሆናቸውን በአወቃቀራቸውና በአመራረጣቸው (Grading and selection) ተገቢውን ሂደት ያልተከተሉ መሆናቸውን አመልክቷል።

ሌላው በ1992 ታደሰ ሲባሞ "በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል (1ኛ-4ኛ) ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ

መርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ በሲዳማ ዞን አራተኛ ክፍል ናሙናነት” ያጠናው የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ነው። በዚህ ጥናት መምህራን ስለአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ እንዲሁም ስለ መርሃ ትምህርቱ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ የክፍል ውስጥ ትግበራ ሂደት ደካማ መሆኑን አመልክቷል።

በነዚህ ሁለት ጥናቶች በተለያዩ ክልሎች የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሁኔታን የሚዳስሱ ግንዛበዎችን ማግኘት ይቻላል። ይህ አሁን የቀረበው ጥናት በኦሮሚያ ክልል ያለውን የመርሃ ትምህርት አተገባበር ሁኔታ ምን እንደሚመስል በመጠኑ የሚያመለክት ይሆናል። ጥናቱ ከቀደሙት ጥናቶች የሚለየው እስካሁን የተካሄዱት በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል (1-4) ያተኮሩ ሲሆን ያሁኑ ጥናት በሁለተኛው ሳይክል (5-8) ባለው ውስጥ መሆኑ፤ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የቀደሙት ጥናቶች የተካሄዱት በትግራይና በደቡብ ህዝቦች ክልሎች በመሆናቸውና አንደናው ጥናት ደግሞ በይዘት ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ያሁኑ ጥናት በኦሮሚያ ክልል ላይ ማተኮሩ በዋናነት የሚጠቀስ ልዩነት ነው።

# ምዕራፍ ሦስት


## የአጠናኑ ዘዴና ቅደም ተከተል

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ አፋቸውን በኦሮምኛ ለፈቱ ተማሪዎች የተዘጋጅውን የስምንተኛ ክፍል መርሃ ትምህርት መገምገም፥ ችግሮች ካሉ ማሳየትና መፍትሄ መጠቆም እንደሆነ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። መረጃዎችን ለመተንተን የሚከተለው ዘዴ ገለፃዊ ቅኝት (Descriptive survey) ነው። እንደ (Lang 1991:81) ይህ ዘዴ በርካታ መረጃዎችን በምልከታ፥ በቃለ መጠይቅ፥ በፅሁፍ መጠይቅና በፈተና በመሳሰሉት ለመሰብሰብና ለመተንተን የሚያስችል ነው። በመሆኑም በርዕሱ ለሚደረገው ጥናት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ዘዴው መመረጥ ችሏል።

### 3.1. ለጥናቱ የተመረጠው ሞዴል

ለዚህ ጥናት በ(Stake 1967) የተነደፈው የዓላማ የሂደትና የውጤት ተጣጥሞሽ ሞዴል (Congruence-Contingency Evaluation Model) ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ ሥራ ላይ ውሏል። ይህ የ'Stake' ሞዴል በዓላማ በተያዘውና በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለውን ተጣጥሞሽ ለማየት የሚያስችል በመሆኑ ተመርጧል። (Mc Cormic እና Jemes 1983:179) እንዲሁም (Yeoman እና Beck 1987:30-31) ሞዴሉን በተመለከተ ለተጣጥሞሽ ግምገማ የሚሆን የተሻለ ውቅር እንደሆነ ይገልፃሉ። (Ornstein እና Hunkins 1998:329) እንደሚከተለው ገልፀውታል፤ "Stake's model for planning and evaluation study provides an organizational framework that points out data to be considered and contrasts what is planned and what has occurred."

ሞዴሉ አንድ የትምህርት ፕሮግራምን በሁለት መንገድ መገምገም የሚያስችል ነው። አንዱ ወገን በቀዳሚ ነገር /Antecedent/ በመስተጋብር /Transaction/ እንዲሁም በውጤት /Outcome/ መካከል ያለው ተዋረዳዊ ትስስር /Contingency/ የሚታይበት ሲሆን ሌላው ደግሞ በታቀደውና /Intended/ በተግባር ላይ በታየው /Observed/ መካከል ያለውን ጎናዊ ዝምድና /Congruence/ የሚመዘንበት ነው።




ቻርት 5 የ'ስቴክ' የአላማ የሂደትና የወጤት ተጣጥሞሽ ሞዴል

የቀዳሚ ነገር ተለውጦዎች ለቀረበው የትምህርት ዓላማ የመምህሩ አመለካከት፥ የማስተማሪያ መሣሪያዎች በብቃት መኖርና አለመኖር፥ የክፍል ውስጥ ቁሳቁስ መሟላትና አለመሟላት፥ የትምህርት አስተዳደሩ የድጋፍ ሁኔታ ተካተው ይገኙበታል። በመስተጋብር ተላውጦዎች በዋናነት በመርሃ ትምህርቱ የተገለፀውን ወደ ተግባር ለመተርጎም የመምህሩ ብቃት የሚታይበት ሲሆን መምህሩ ከርዕሰ መምህሩ፥ ከተማሪው ጋር የሚያደርገውን ተራክቦ የሚዳስስ ነው። የውጤት ተላውጦ ደግሞ መምህሩ የቀረበውን ዕቅድ በተገቢው መንገድ ካቀረበ በኋላ በተማሪው ላይ የሚታየው የባህሪ ለውጥ የሚነፃፀርበት ነው። በዚህ ረገድ የሚኖረው የዕቅድና ምልከታ የጣጥሞሽ ለማየት በርካታ መረጃዎች በተለያየ መንገድ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል።

ሞዴሉ ሁለት የመገምገሚያ አቅጣጫ ያለው ቢሆንም ለዚህ ጥናት የተወሰደው በከፊል ነው። ይህም በቀረበው ዕቅድና /Intent/ በታየው /Observed/ ሁኔታ ላይ የሚያተኩረውን የተጣጥሞሽ ጉዳይ ለማየት በቂ ሆኖ ስለሚገኝ ነው። ጥናቱ ገላጭ እንደመሆኑ አንድን አቅጣጫ መከተል ተገቢ ይሆናል። ከዚህ አንፃር በዕቅድ የቀረበው ሲባል በመርሃ ትምህርቱ፥ በመምህሩ መምሪያና በተማሪው መፅሃፍ የቀረበውን የሚመለከት ሲሆን ምልከታው ደግሞ በመስክ መረጃ የመሰብሰብ ሂደት ከትግበራው ቀጥተኛ ተሳታፊዎች ጋር በመገናኘት በሚደረገው ጥናት የሚገኝ ነው።

### 3.2. የናሙና አመራረጥ ሂደት

ይህ ጥናት ጠቅለል ባለ መልክ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያሉትን የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት /ለኢ-አፈ.ፊ.ት/ አሰጣጥ የሚመለከት ሊሆን ቢችልም ከጊዜ፥ ከሰው ኃይልና ከበጀት እጥረት የተነሳ በምስራቅ ሸዋ ዞን ብቻ መወሰኑ የግድ ሆኗል። በዞኑ ካሉት ትምህርት ቤቶች ወካይ የሆነ ናሙና /Representative sample/ ለማግኘት ባለብዙ ደረጃ ቡድናዊ ናሙና አወሳሰድ ስልት /Multi-stage cluster sampling technique/ ተግባራዊ ሆኗል። በርካታ ቁጥር ላላቸው የመረጃ ምንጮች በዚህ ስልት መጠቀም ተገቢ እንደሆነ (Koul 1996:116) ያስረዳሉ።

#### 3.2.1. የወረዳዎችና የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

በናሙናዊ አመራረጥ አንዳንዶቹ አምስት ከመቶ በቂ ነው ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ እስከ ሰላሣ በመቶ ያደርሱታል። ሆኖም (Nachmias እና Nachmias 1987:195-196) የሚሉት ዋናው ጉዳይ ናሙናው ወካይ እንዲሆን አጥኚው ጥረት ማድረግ እንደሚገባው ነው። በዚህም መሠረት በምስራቅ ሸዋ ዞን ከሚገኙት አሥራ ሁለት ወረዳዎች /አደአ፥ አዳማ፥ አዳሚቱሉ፥ አርሲነገሌ፥ አቃቂ፥ ሻሸመኔ፥ ፈንታሌ፥ ቦሰት፥ ሲራሮ፥ ጊምቢቹ፥ ዱግዳቦራና፥ ሉሜ/ አራቱን በናሙናነት መምረጥ በማስፈለጉ በዕጣ ናሙና አዳማ፥ አደአ፥ አዳሚቱሉና ሉሜ ወረዳዎች ተመርጠዋል።

በዞኑ በጠቅላላ 65 የመንግስት የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ በናሙናነት በተመረጡት ወረዳዎች ሃያ ሰባት ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ዘጠኙ በከተማ ቀሪዎቹ አሥራ ስምንቱ በገጠር የሚገኙ ናቸው። በየወረዳዎቹ ካሉ ትምህርት ቤቶች አንድ ከከተማ አንድ ከገጠር ለመውሰድ በማሰብ የዕጣ ናሙና በመጠቀም በድምሩ ስምንት ትምህርት ቤቶች ተለይተው ተመርጠዋል። እነርሱም ከአዳማ ወረዳ አዳማ ቁጥር ሁለት ትምህርት ቤትና ወንጅ ሸዋ አለምጤና ትምህርት ቤት፥ ከአድአ ወረዳ ቦሌ ትምህርት ቤትና ደንካካ ትምህርት ቤት ከአዳሚቱሉ ወረዳ ዝዋይ ትምህርት ቤትና ቡልቡላ ትምህርት ቤት፥ ከሉሜ ወረዳ ሞጆ ቁጥር አንድ ትምህርት ቤትና ኤጀርሣ ትምህርት ቤት ተመርጠዋል።

#### 3.2.2. የተማሪዎች አመራረጥ

በዞኑ ካሉት 65 የመንግስት ትምህርት ቤቶች በ1993 ለብሔራዊ ፈተና የሚቀመጡ 3849 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 2543 ወንዶች፥ 1306 ሴቶች ናቸው። ከነዚህ ውስጥ በናሙናነት በተመረጡት ወረዳዎች 1876 ተማሪዎች ሲገኙ 1097 ወንዶች፥ 779 ሴቶች ናቸው። ቁጥሩ ይህ ቢሆንም በየወረዳዎቹና በየትምህርት ቤቶቹ ያለው ስርጭት ተመጣጣኝ ባለመሆኑና ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እኩል ድርሻ መስጠት በማስፈለጉ ከየትምህርት ቤቱ አርባ ተማሪዎችን ከመምህራን ጋር በመነጋገር ምርጫ በማካሄድ 320 ተማሪዎች 185 ወንዶች 135

ሴቶች ተመርጠው ለብቃት መለኪያው ፈተና እንዲቀመጡ በማድረግ መረጃ ሰጥተዋል። ይህ ቁጥር የጠቅላላውን ቁጥር 17.05 በመቶ ናሙና ነው።

በነዚሁ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛው ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ ስምንት መምህራን በመረጃ ሰጭነት ያገለገሉ ሲሆን እነዚህኑ መምህራን በተግባር ላይ እንዳሉ ከረዳት ተመልካች ጋር በመሆን ለሦስት ጊዜ ምልከታ ተካሂዷል። የየትምህርት ቤቶቹ ርዕሳነ መምህራን በመረጃ ሰጪነት ተወስደዋል።

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

በቂና አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት እንዲቻል ሦስት ዓይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። እነርሱም፤ የፅሁፍ መጠይቅ፥ የክፍል ውስ ጥ ምልከታና የብቃት መለኪያ ፈተና ናቸው።

### 3.3.1. የፅሁፍ መጠይቅ

በፅሁፍ መጠይቁ መረጃ የሰጡት በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራንና በጥናቱ በተሸፈኑት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ርዕሳነ መምህራን ናቸው። ለዚህም ሁለት ዓይነት የፅሁፍ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል። (አባሪ ሁለትንና ሦስትን ይመልከቱ።) መጠይቆቹ የ8ኛ ክፍልን መርሃ ትምህርት፥ የመምህር መምሪያና የተማሪውን መፅሃፍ እንዲሁም የምርምሩን ጥያቄ በማገናዘብ የተዘጋጁ ናቸው።

ለአማርኛ መምህራን የተዘጋጀው የፅሁፍ መጠይቅ ባለ አራት ክፍል ሲሆን የመጀመሪያው የመምህራኑ ዳራዊ ሁኔታ የሚገለፅበት ነው። ሁለተኛው ክፍል የመምህራኑ ስለመርሃ ትምህርቱና ትግበራው ሁኔታ አመለካከታቸውን የሚገልፁበት ነው። ይህም በመርሃ ትምህርቱ አተገባበር ላይ ያላቸውን አመለካከት በ "Likert scale"በአምስት ደረጃ (በጣም እስማማለሁ፥ እስማማለሁ፥ ለመወሰን ያዳግታል፥ አልስማማም፥ በጣም አልስማማም) ሃሳባቸውን የሚያንፀባርቁበት ነው። ሦስተኛው የፅሁፍ መጠይቁ ክፍል አደረጃጀትን የሚያመለክት ሲሆን ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት ምን ያህል የተመቻቸ ለማድረግ ጥረት እንዳደረገ የሚገልፁበት ነው። በአራተኛው ክፍል በመርሃ ትምህርት ትግበራ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ ተብለው የሚገመቱ ተላውጦዎች የተዘረዘሩበትና እንደ ተፅዕኖው ከፍተኛነትና ዝቅተኛነት በደረጃ /Ranking/ ምላሽ የሚሰጥበት ነው።

የመጠይቁን አስተማማኝነት /Reliability/ ለመጠበቅ እንዲያስችል የመጀመሪያው ረቂቅ በጥናቱ አማካሪ ከታየና ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ በዩኒቨርሲቲው ያሉ አንዳንድ የቋንቋ መምህራንና የሥነ ልቦና ሁለተኛ ዓመት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተበትኖ ገንቢ የሆነ ምላሽ ተገኝቶበት ተስተካክሏል። በተጨማሪም ለቅኝት ጥናት በተመረጡ ሁለት ትምህርት ቤቶች /አዳማ ቁጥር ሦስትና አዳማ ቁጥር አራት/ ያሉ

አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሞሉት ተደርጎ አሻሚ መልስ የተሰጠባቸውንና መልስ ያልተሰጠባቸውን እንዲሁም አቅጣጫውን የሳተ መልስ የተሰጠባቸው ጥያቄዎች እንዲስተካከሉ አንዳንዶቹም እንዲወገዱ ተደርጓል።

በርዕሰ መምህራን እንዲሞላ የተዘጋጀው የፅሁፍ መጠይቅ ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን በክፍል አንድ የርዕሰ መምህሩን ዳራዊ ሁኔታ የሚጠይቅ ነው። ክፍል ሁለት ደግሞ ስለ ትምህርት ቤቱ አደረጃጀት የሰው ኃይልና የቁሳቁስ መጠን በተለያየ መልክ ምላሽ እንዲሰ ጡ የሚጠይቅ ነው። የፅሁፍ መጠይቁ ለቅኝት ጥናት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምርህራን እንዲሞላ ተደርጎ መረጃ ሊገኝባቸው ያልቻሉ የጥያቄ ዓይነቶች በማስወገድና አሻሚ መልስ የተሰጠባቸውን ጥያቄዎች በማሻሻል ለዋናው ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት እንዲያገለግሉ ተደርጓል።

### 3.3.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ

የትግበራን ሁኔታ በተጨባጭ ለመረዳትና በቂ የሆነ ግንዛቤ ለማግኘት የክፍል ውስጥ ምልከታ ከፍተኛ ድርሻ አለው (Brandt 1981, Richards and Rodgers 1995) እንደ (Richards እና Rodgers 1995) አገላለፅ በተለይ በቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ ምልከታ ትግበራውንና የመምህሩን ብቃት በትክክል ሊያሳይ እንደሚችል ይገልፃሉ።

በዚህም መሠረት ሁለት ክፍሎች ያሉት የምልከታ ቅፅ ተዘጋጅቷል። በእርከናዊ ልኬት /Rating scale/ እና በቼክ ሊስት /Check list/ የተዘጋጀው የምልከታ ቅፅ መሠረት ያደረገው በመርሃ ትምህርቱ በመምህሩ መምሪያና በመማሪያ መፅሃፉ ያሉትን መምህሩ በክፍል ውስጥ ማከናወን የሚጠበቅበትን ተግባራት ነው። በእርከናዊ ልኬት የቀረቡት አሥራ አንድ ነጥቦች በቅኝት ጥናት ወቅት ሁለት የአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ረዳት ተመልካቾችን ገለፃ በመስጠት ከአጥኚው ጋር በመሆን በናሙናነት በተመረጡ ት ትምህርት ቤቶች ለሦስት ጊዜ የክፍል ውስጥ ምልከታ ተካሂደል። በነጥብ አሰጣጡም 86.4 በመቶ ተቀራርቦሽ በመታየቱ ለልዩነቱ መነሻ የሆኑትን በመሠረዝና አንዳንዶቹን በማስ ተካከል ለዋናው ጥናት ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

የተዘጋጀው ቼክ ሊስት ባለ አሥራ ሦስት ነጥብ ሲሆን ከረዳት ተመልካቾቹ ጋር 91.2 በመቶ የነጥብ አሰጣጥ ተቀራርቦሽ ታይቷል። ለልዩነቱ መነሻ የሆኑት እንደገና ትኩረ ት ተሰጥቷቸው ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል። በተመልካቾች መሀል ያለው የነጥብ አሰጣጥ ተቀራ ርቦሽ ለምልከታው የተዘጋጀው ቅፅ በቂ መሆኑን የሚያመለክት ነው። በመሆኑም ለዋናው ጥናት ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። በዋናው ጥናትም እያንዳንዱን መምህር ከረዳት ተመልካች ጋር በመሆን ለሦስት ጊዜ ያህል ምልከታ ተካሂደል። /አባሪ አራትን ይመልከቱ/

### 3.3.3. የብቃት መለኪያ ፈተና

ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት፥ የመምህር መምሪያና የተማሪውን

መፅሃፍ በማገናዘብ አርባ ጥያቄዎች የያዘ የብቃት መለኪያ ፈተና ተዘጋጅቷል። በብቃት መለኪያው ፈተና የሚገኘው ውጤት የመርሃ ትምህርቱን የትግበራ ደረጃ ሊያሳይ ከመቻሉም በላይ በየትኞቹ የትምህርት ዓላማዎች ላይ ይበልጥ ተግባራዊ እንደሆነ ሊያሳይ ይችላል። የብቃት መለኪያ ፈተና አንድ ተማሪ ከቀረበለት ትምህርት ውስጥ ምን ያህሉን እንዳወቀ ወይም እንደቻለ የሚያሳይ እንደሆነ (Lang 1991:174) ሲገልፁ (Ornstein እና Hunkins 1988:250-251) ይህንኑ ሃሳብ ይጋራሉ።

የፈተናው ጥያቄዎች የተዘጋጁት በአዳማ ኮሌጅ ቋንቋ መምህር ከሆኑ ሰው ጋር በመተባበር ሲሆን ጥያቄዎችን ከማውጣት በፊት በዝርዝር የቀረቡትን ዓላማዎችና ይዘቶች እንዲሁም ድግግሞሽ አንድ በአንድ ከመርሃ ትምህርቱ ውስጥ በመልቀም ይኸው ይዘትና ድግግሞሽ (Frequency) በመማሪያ መፅሃፉ ላይ መንፀባረቁ ተገናዝቧል። የቀረቡትን ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ እንደቀረበው በሦስት ርዕሶች /የትምህርት ክፍሎች/ ሥር ተዘርዝ ረዋል። የትምህርት ክፍሎቹ ንባብና ማስተዋል፥ ፅህፈትና ሥነ ልሳን ናቸው። በትምህርት ርዕሶቹ ሥር የተለያዩ ዝርዝር ዓላማዎች ተቀምጠዋል። /አባሪ አምስት ይመልከቱ/

የትምህርት ክፍሎቹ በአንደኛ ወሰነ ትምህርት እንዲሸፈኑ የተመደቡ ናቸው። በዚህ መሠረት ዝርዝር ዓላማዎችን በመያዝ "Table of specification" ከተዘጋጀ በኋላ ለእያንዳንዱ ዓላማ ትክክለኛ ውክልና የሚሰጥ አርባ ጥያቄዎች የያዘ ጥራዝ ተዘጋጀ። ይህ ንድፍ በጥናቱ አማካሪ ከታየና ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ በዩኒቨርሲቲው ለሚገኙ አንዳንድ የቋንቋ መምህራን፥ ለስርዓተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም የአማርኛ ትምህርት ቡድን፥ ለብሔራዊ ፈተናዎች ድርጅት የአማርኛ ቋንቋ ኤክስፐርት ተሰጥቶ በቂ የሆነ ማስተካከያና ማሻሻያ ተደርጎበታል።

ከዚህ በኋላም ለቅኝት ጥናት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ባሉ ሰላሣ አራት ተማሪዎች ላይ ተፈትሿል። እንደ (Madson 1983:181-183) አንድ የፈተና ጥያቄ ከተፈታኞቹ ቁጥር ዘጠና ከመቶ የሚሆኑት ከመለሱት ቀላል ሊባል እንደሚችልና ሰላሳ ከመቶ በታች ከመለሱ ከባድ ሊባል እንደሚችል ይገልፃሉ። በዚህም መሠረት ለፈተና የተቀመጡት ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጡት መልስ በሠንጠረዥ ተመዝግቦ ታይቷል። ዘጠና ከመቶ በላይ በሆኑ ተፈታኞች ትክክለኛ መልስ የተሰጠባቸው አምስት ጥያቄዎችና ሰላሳ ከመቶ በታች ምላሽ የተሰጠባቸው ሁለት ጥያቄዎች እንዲለወጡና እንዲስተካከሉ ተደርጓል።

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ በቅኝት ጥናት ወቅት በቂ ሆኖ ባለመገኘቱና ተማሪዎቹ ሁሉንም ጥያቄዎች ከጊዜ ማጠር የተነሳ ሳይሞክሩ እንዳይቀሩ በማሰብና ሁሉም ጥያቄዎች መመለስ ስለሚኖርባቸው በሙከራው ጥናት የመጨረሻው ተማሪ የፈተና ወረቀት የመለሰበት ጊዜ የዋናው ፈተና ጊዜ እንዲሆን ማስተካከያ ተደርጓል።

የፈተናው አስተማማኝነት ሊያሳይ በሚችለው በ(Kuder Rechardson Formula 21 (Lang 1991:62) በመጠቀም ተሰልቷል። ይህ ቀመር አንድ ጊዜ በመፈተን ውጤቱን ማስላት

የሚያስችል እንደሆነ (Fraas 1983:69) ይጠቀማሉ። በስሌቱም መሠረት አስተማማኝነቱ 0.49 በመሆኑና ይህም ተቀባይነት ያለው አሃዝ በመሆኑ ፈተናው ለዋናው ጥናት እንዲውል ተደርጓል።

## 3.4. ጥናቱ የተከተለው መረጃዎችን የመተንተኛ ዘዴ

የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተንና ለመተርጎም የተለያዩ ስታትስቲካዊ ስልቶች ሥራ ላይ ውለዋል። ከምርምር ጥያቄዎች ቀዳሚው (ገፅ 4 ይመልከቱ) የመምህራንን አመለ ካከት ለማወቅ የቀረበው ሲሆን ለዚህ ምላሽ ለማግኘት የቀረቡት የአመለካከት ጥያቄዎች ቀደም ሲል እንደተገለፀው ባለ አምስት ደረጃ (በጣም እስማማለሁ፥ እስማማለሁ፥ ለመወሰን ያዳግታል፥ አልስማማም፥ በጣም አልስማማም) ናቸው። መምህራኑ በእያንዳንዱ አረፍተ ነገር ላይ የሰጧቸው ምላሾች በመደመርና በማእከላዊ ቴስት (Median test) ከፍተኛ ዝቅተኛ በማለት ተከፍሏል። የማእከላዊ ቴስቱን በማስላት ሂደት ምላሽ የሰጡት መምህራን በሁለት ማለትም በገጠርና በከተማ ተከፍለዋል። የእያንዳንዱ መምህር አመለካከት ከተመደበበት ትምህርት ቤት አንፃር ተመዝግቧል።

በዝቅተኛና በከፍተኛ መካከል ያለውን ልዩነት ለማነፃፀር "Chi square ($x^2$) test" ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ይህም ውጤት ከጥቅል ውጤት ጋር ለማነፃፀር ጥቅል አማካይ (Grand median) ተነፃፅሯል። ለዚህም Älpha (α) 0.05) level of significance በመገልገል ነው።

ከጥቅል አማካይ በታች መሆን መምህራኑ ለመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ያላቸውን አሉታዊ (Negative) አመለካከት ሲጠቁም ከጥቅል አማካይ ከፍ ብሎ መታየቱ ለትግበራው ያላቸውን አዎንታዊ (Positive) አመለካከት የሚያሳይ ሆኗል። (ሠንጠረዥ ሁለት ይመልከቱ)

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ (ገፅ 4 ይመልከቱ) ለመመለስ በዋናነት በምልከታው የተሰበ ሰበው መረጃ ተተንትኗል። እያንዳንዱ መምህር ለሦስት ጊዜ ምልከታ የተካሄደበት ሲሆን ውጤቱን ወደ አንድ በማጠቃለል በአሃዝ ተሰልቶ በመቶኛ ተገልጿል። በገጠርና በከተማ ምን ያህል ልዩነት እንዳለ በትንተና ቀርቧል። (ሠንጠረዥ ሦስትና አራት ይመልከቱ)

የምልከታው ቅፅ በሁለት የተከፈለ (ሀናለ) ሲሆን በፊደል ተራ 'ሀ' እርከናዊ ልኬት (Rating scale) አሥራ አንድ ነጥቦችን የያዘ ዝርዝር ተዘጋጅቷል። ይህም በተደጋጋሚ አልፎ አልፎ እና አያደርግም በሚል በሦስት ደረጃ የተከፈለ ነው። በአጥኚውና በረዳት ተመልካቹ የተሰጡት የአንድ መምህር ምልከታ ውጤቶች በአንድ ተጠቃሎ ተሰልቷል። በፊደል ተራ 'ለ' ሥር አሥራ ሦስት ያህል ነጥቦች የተዘረዘሩ ሲሆን አማራጮቹም አዎ/የለም የሚሉ ናቸው። በምልከታው ጊዜ የታየው ነገር አዎ በሚለው ሥር ምልክት ሲደረግበት ካልታየ ደግሞ የለም በሚለው ሥር ምልክት ይደረግበታል። በአጥኚውና በረዳቱ አማካይነት በየጊዜው የተሰጡት ነጥቦች ድግግሞሽ ጭማቂ ተጠቃሎ

በአንድ ተመዝግቧል። ይህም እያንዳንዱ መምህር በመርሃ ትምህርቱ ከተገለፀው አንፃር ያከናወነውንና ያላከናወነውን ተግባር ከማመልከቱም በላይ በገጠርና በከተማ ያለውን ልዩነት ያሳያል። ይህም በመቶኛ ተሰልቶ ከተተነተነ በኋላ ትርጉም ተሰጥቶታል።

የምርምሩ ሦስተኛ ጥያቄ (ገፅ 4) ይመለከቱ በስፋት ምላሽ የሚያገኘው ከብቃት መለኪያ ፈተና ነው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው ፈተናው የተዘጋጀው የቀረበውን ይዘትና ዝርዝር ዓላማ መሠረት በማድረግና እያንዳንዱ ዓላማ ምን ያህል ድግግሞሽ እንዳለው በማስላት ነው። እነዚህ አርባ ጥያቄዎች በሦስቱ የትምህርት ክፍሎች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይህም ተማሪዎቹ በየትኛው የትምህርት ክፍል ላይ የበለጠ ግንዛቤ አግኝተዋል የሚለውን ለይቶ ለመናገር የሚያስችል በመሆኑ ነው።

በገጠርና በከተማ መሀከል ያለውን ልዩነት ለመመልከት "Alpha 0.05 level of significance" በመጠቀም ተሰልቷል። ተማሪዎችን በገጠርና በከተማ ከፋፍሎ ማየት ያስፈለገበት ምክንያት የገጠሮቹ ከከተሞቹ ዝቅተኛ ብቃት ይኖራቸዋል በሚለው መነሻ መላምት መሠረት ነው። ይህን ሊያሰኝ የሚችለው በከተማ የሚገኙ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው ተጋልጦ በገጠር ከሚገኙ ተማሪዎች የተሻለ እንደሆነ በመገመት ነው።

የቀረቡትን አርባ ጥያቄዎች ከቀረበው የትምህርት ክፍል አንፃር በሦስት በመክፈል በእያንዳንዱ ላይ የትምህርትና የፈተና ባለሙያዎችን በማሳተፍ የማለፊያ ወሰን (Cutoff score) እንዲወሰን ተደርጓል። ይህም ከዚህ የትምህርት ክፍል ቢያንስ እስከዚህ ድረስ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል የሚል መነሻ በመያዝና የጋራ ስምምነት በማድረግ ነው። በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሠረት የአንድ ተማሪ የማለፊያ ነጥብ 50 ከመቶ ማግኘት ሲሆን በዚህ የብቃት መለኪያ ፈተና የተወሰደው የማለፊያ ነጥብ ግን ከዚህ የተለየ ነው። በዚህም መሠረት የሚከተለው ሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል።

ሠንጠረዥ 1 የማለፊያ ወሰን ማመልከቻ

| የትምህርት ክፍል | የወጡ ጥያቄዎች ብዛትና ተራ ቁጥራቸው | የማለፊያ ወሰን |
|---|---|---|
| ንባብና ማስተዋል | 8<br>(1÷2÷3÷4÷5÷6÷25÷29) | 5 |
| ፅህፈት | 13<br>(7÷8÷9÷10÷11÷12÷16÷21÷35÷36÷37÷38÷39) | 7 |
| ሥነ ልሳን | 19<br>(13÷14÷15÷17÷18÷19÷20÷22÷23÷24÷26÷27÷28÷30÷31÷32÷33÷34÷40) | 10 |
| ጠቅላላ | 40 | 22 |

ሦስቱ የትምህርት ክፍሎች በመርሃ ትምህርቱ የተገለፁና በአንደኛው ወሰነ ትምህርት የሚሸፈኑ ሲሆኑ በዝርዝር ዓላማው ካላቸው ድግግሞሽ በመነሳት ከየትምህርት ክፍሎች

በመቶኛ በማስላት ከአርባው ምን ያህሉን ጥያቄ መሸፈን እንዳለበት ከተለየ በኋላ ጥያቄዎ ች ተቀርፀዋል። በዚህም መሠረት ከንባብና ማስተዋል ስምንት ጥያቄዎች የወጡ ሲሆን ተማሪው ከስምንቱ አምስቱን (62.5) ከመለሰ አልፏል ማለት ይቻላል። በፅህፈት ትምህርት አሥራ ሦስት ጥያቄዎች የወጡ ሲሆን ተማሪው ሰባቱን (53.8) ከመለሰ አልፏል ማለት ይቻላል። በሥነ ልሳን ትምህርት ተማሪው ከቀረቡለት አሥራ ዘጠኝ ጥያቄዎች አሥሩን (52.6) ከመለሰ አልፏል ማለት ይቻላል። በድምሩ ከአርባው ጥያቄ ሃያ ሁለት (55%) የመለሰ ተማሪ አልፏል ማለት ይቻላል።

በዚህም መልክ የተመዘገበው የተማሪዎች ውጤት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡ በሁለት (ያለፉ/ያላለፉ) በመክፈል በመቶኛ ተሰልቶ ተተንትኗል። በቀረበው የትምህርት ክፍል የአላፊ ተማሪዎች ቁጥር በርካታ መሆን በዚያ ረገድ የተማሪዎችን ብቃት የሚያመለክት ሲሆን የአላፊዎች ቁጥር አነስተኛ መሆን የቀረበውን ትምህርት ተግባራዊ መሆኑን ጥርጣሬ ላይ የሚጥል ይሆናል። በአጠቃላይ ውጤት ያለፉና ያላለፉ ተማሪዎች ቁጥር የመርሃ ትምህርቱን ትግበራ ስኬታማ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚጠቁም ይሆናል።

በየወረዳዎቹ መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት በየወረዳዎቹ የተመዘገቡት ውጤቶች ተነፃፅረዋል። ይህን ለማየት በ"Chi square ($x^2$) " በ "alpha 0.05 level of significance" ተሰልቷል። መርሃ ትምህርቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ተግባራዊ ከሆነ በተማሪዎች ውጤት ላይም የሚታየው ለውጥ ልዩነት ላያሳይ ይችላል። እንዲሁም በዚሁ ስሌት የገጠርና የከተማ ተማሪዎች ውጤት ተነፃፅሯል፥

የምርምሩ አራተኛና አምስተኛ ጥያቄዎች (ገፅ 4 ይመልከቱ) ለመምህራኑና ለርዕሰ መምህራኑ ከቀረቡት መጠይቆችና በተገኙት ምላሾች የአሃዝና የምርጫ ጥያቄዎችን ታሊ /Tally/ በማድረግ፥ ሃተታዊ መልሶችን እያንዳንዳቸውን በመተንተን ምላሽ የተሰጠባቸው ሲሆን በተለይም ለመምህራኑ በመጠይቁ ክፍል አራት የቀረቡት ደረጃ የማውጣት ዓረፍተ ነገሮች የተሰጣቸው ደረጃ አማካይ (Mean rank) ለመላሾቹ ቁጥር በማካፈል የሚገኝ ሲሆን ዝቅተኛ አማካይ ደረጃ ያገኘው የመጀመሪያውን ደረጃ ሲይዝ ከፍተኛ አማካይ ደረጃ የያዘው ዓረፍተ ነገር የመጨረሻውን ደረጃ ይይዛል። ትርጉሙም ከላይ ከመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚቀመጡት የዓረፍተ ነገር ደረጃዎች የመርሃ ትምህርት ትግበራን መሳካት የሚቀንሱ ሆነው ሲገኙ ወደ መጨረሻው ላይ የሚመጡት የተፅዕኖአቸው ልክ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል። (ሠንጠረዥ አሥራ አንድ ይመልከቱ)

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንተናና ትርጓሜ

በዚህ ምዕራፍ በፅሁፍ መጠይቆች፥ በክፍል ውስጥ ምልከታና በብቃት መለኪያ ፈተና የተሰበሰቡበት መረጃዎች በሰንጠረዥ አማካይነት ይቀርባሉ። ለምርምሩ መነሻ የሆኑትን አምስት ጥያቄዎች ከመመለስ አንፃር የመተንተንና የመተርጎም ተግባር ይከናወናል።

### 4.1. የመምህራን ለመርሃ ትምህርቱና ለትግበራው ያላቸው አመለካከት፥

የአንድ ሰው አመለካከት የሚመነጨው ስለሚጠየቀው ነገር ካለው ዕውቀትና ግንዛቤ ነው። የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራንም ስለመርሃ ትምህርቱ ከሚኖራቸው ዕውቀትና ግንዛቤ (Knowledge and understanding) የተነሣ የራሳቸው አመለካከት ይኖራቸዋል።

ሠንጠረዥ 2 የመምህራን ስለመርሃ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት በገጠርና በከተማ

| የአመለካከት ውጤት | መልስ የሰጡ መምህራን | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከተማ | % | ገጠር | % | ድምር | % |
| ከአማካይ በላይ | 3 | 75 | 1 | 25 | 4 | 50 |
| ከአማካይ በታች | 1 | 25 | 3 | 75 | 4 | 50 |
| ድምር | 4 | 100 | 4 | 100 | 8 | 100 |
| $x^2$=0.5 | | | | | | |

የመላሾችን ጥቅል አማካይ በመውሰድ የተገኘው 52.5 ነው (አባሪ 8ሀ) ይመልከቱ ከጥቅል አማካይ በላይና በታች ያገኙት መምህራን በትምህርት ቤት ዓይነት (በገጠርና በከተማ) ተለይተው ተቀምጠዋል። የ"Chi square test" ስታትስቲክ ከሠንጠረዡ በመነሳት ተሰልቷል። $x^2$=0.5 ሲሆን "Critical chi square value ($x^2$=3.84, df =1 $P\leq0.05$" ይህም በlevele of significance $P\leq0.05$ መሠረት በገጠርና በከተማ መሀከል ጉልህ የሆነ ስታትስቲካዊ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል።

በሠንጠረዥ ሁለት ላይ እንደተመለከተው በገጠር ያሉ መምህራን አብዛኞዎቹ (75% የሚሆኑት) ከአማካዩ በታች እንዳሉ ሲያሳይ በከተማ 75% ከአማካይ በላይ ሆነው ተገኝተዋል። 75% የከተማዎቹና 25% የገጠሮቹ በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ላይ አዎንታዊ አመለካከት /Positive attitude/ ያላቸው መሆኑን በአንፃሩ 25% የከተማዎቹ 75% የገጠሮቹ መምህራን ለመርሃ ትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው አሳይቷል። በጥቅሉ ሲታይ ደግሞ 50% የሚሆኑት መምህራን በመርሃ ትምህርቱ ለቀረበው ዝርዝር ተግባር ቀና አመለካከት ያላቸው መሆኑን አሳይቷል።

በገጠር ካሉት መምህራን 50% የሆኑት ለደረጃው የሚመጥን ስልጠና ያላቸው ሲሆን ግማሾቹ ስልጠና ያልወሰዱ ናቸው። ምንም እንኳ በፍላጎታቸው ቢመደቡም ለመርሃ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛነት 75% አሳይቷል። ይህም መርሃ ትምህርቱን ለመተግበር ያላቸው ስልጠና አናሳ ከመሆኑ የመነጨ ነው ማለት ይቻላል።

ሃምሣ ከመቶዎች ያህሉ አሉታዊ አመለካከት ቢያሳዩም 37.5% በፍላጎት 62.5% ከስልጠና አንፃር የተመደቡ ናቸው። በምርጫም ሆነ በስልጠናቸው የተመደቡት ያለፍላጎት የተመደቡ ባለመሆናቸው ላሳዩት 50% አሉታዊ አመለካከት መሠረቱ ፍላጎት አለመሆኑን መረዳት ይቻላል። መረጃ ከሰጡት መምህራን 37.5% ለደረጃው የሚመጥን ስልጠና የሌላቸ ው መሆኑን በመጠይቁ የገለፁ ሲሆን 62.5% የሚሆኑት ለመርሃ ትምህርቱ አተገባበር በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸው ገልፀዋል። ስለዚህ ለመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ያላቸው አመለካከት 50% አዎንታዊ 50% አሉታዊ ሊሆን ችሏል።

በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን ለተዘጋጀው ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለ ካከትና ተነሳሽነት ወሳኝ ድርሻ አለው። የመርሃ ትምህርቱ ተተግባሪነት በከተማ 75% በገጠ ር 25% ብቻ ሲያደርገው በድምሩ ትግበራው ከአመለካከት አንፃር በ50% ብቻ የተደገፈ ነው። ይህም መርሃ ትምህርቱ ተግባራዊ የሆነው በግማሽ አቅም መሆኑን ያመለክታል። የምርምሩ የመጀመሪያ ጥያቄ በዚህ አንፃር የሚታይ ይሆናል።

## 4.2. የመምህራን የክፍል ውስጥ የማስተማር ብቃት

የመማሪያ ክፍል ትክክለኛው የትግበራ ሂደት የሚከናወንበት ስፍራ ነው። የተዘጋጀው ትምህርት፥ መምህሩና ተማሪው በቀጥታ የሚገናኙበት ነው። የትግበራን ስኬታማነት በሙሉ ልብ መናገር የሚቻለው በክፍል ውስጥ የሚደረገውን መስተጋብር በመመልከት ነው። በጥናቱ የቀረበውን ሁለተኛ ጥያቄ ለመመለስ ቀጥሎ ያሉት ሠንጠረዦች ቀርበዋል

ሠንጠረዥ 3 በእርከናዊ ልኬት የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤት መግለጫ

| ተቁ | የማስተማር ክንውን | እርከናዊ ልኬት | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | | | | | | ገጠር | | | | | | ጠቅላላ | | | | | |
| | | በተደጋጋሚ | | አልፎ አልፎ | | አያደርግም | | በተደጋጋሚ | | አልፎ አልፎ | | አያደርግም | | በተደጋጋሚ | | አልፎ አልፎ | | አያደርግም | |
| | | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % |
| 1 | በየደረጃው ለሚደረገው ተግባር መግለጫ ይሰጣል | 4 | 33.3 | 5 | 41.5 | 3 | 25 | 4 | 33.3 | 6 | 50 | 2 | 16.7 | 8 | 33.3 | 11 | 45.8 | 5 | 20.8 |
| 2 | በመረጃ የተደገፈ መረጃ ይሰጣል | 4 | 33.3 | 6 | 50 | 2 | 16.7 | 4 | 33.3 | 6 | 50 | 2 | 16.7 | 8 | 33.3 | 12 | 50 | 4 | 16.7 |
| 3 | ተማሪዎችን ምጋቤ ምላሽ ይጠይቃል | 7 | 58.3 | 4 | 33.3 | 1 | 8.3 | 7 | 58.3 | 3 | 25 | 2 | 16.7 | 14 | 58.3 | 7 | 29.2 | 3 | 12.5 |
| 4 | ተማሪዎችን ለማሳተፍ ይጥራል | 5 | 41.5 | 5 | 41.5 | 2 | 16.7 | 6 | 50 | 5 | 41.5 | 2 | 16.7 | 11 | 45.8 | 10 | 41.7 | 4 | 16.7 |
| 5 | ትምህርቱን ተማሪ ተኮር /Learner centered/ ለማድረግ ይጥራል | - | - | 8 | 66.7 | 4 | 33.3 | 5 | 41.5 | 6 | 50 | 1 | 8.3 | 5 | 20.8 | 14 | 58.3 | 5 | 20.8 |
| 6 | ጠቃሚ ሃሳቦችን በሰሌዳው ይፅፋል | 5 | 41.5 | 7 | 58.3 | - | - | 3 | 25 | 7 | 58.3 | 2 | 16.7 | 8 | 33.3 | 14 | 58.3 | 2 | 8.3 |
| 7 | ክሂሎችን ለማዛነቅ /Integrating skills/ ይጥራል | 2 | 16.7 | 6 | 50 | 4 | 33.3 | 2 | 16.7 | 8 | 66.7 | 2 | 16.7 | 4 | 16.7 | 14 | 58.3 | 6 | 25 |
| 8 | ትምህርቱን ከዕለት ሁኔታ ጋር እንዲያገናዝቡ ያደርጋል | 5 | 41.5 | 7 | 58.3 | - | - | 3 | 25 | 7 | 58.3 | 2 | 16.7 | 8 | 33.3 | 14 | 58.3 | 2 | 8.3 |
| 9 | ተማሪዎችን በተናጠል ለመርዳት ይጥራል | 5 | 41.5 | 4 | 33.3 | 3 | 25 | 3 | 25 | 7 | 58.3 | 2 | 16.7 | 8 | 33.3 | 11 | 45.8 | 5 | 20.8 |
| 10 | በንግግር ሃሳባቸውን እንዲሰጡ ያደርጋል | 5 | 41.5 | 7 | 58.3 | - | - | 5 | 41.5 | 6 | 50 | 1 | 8.3 | 10 | 41.7 | 13 | 54.2 | 1 | 4.2 |
| 11 | የቋንቋውን ህግ በራሳቸው ጥረት እንዲደርሱበት መንገድ ይከፍታል | - | - | 6 | 50 | 6 | 50 | 2 | 16.7 | 8 | 66.7 | 2 | 16.7 | 2 | 8.3 | 14 | 58.3 | 8 | 33.3 |

*ድግ=ድግግሞሽ (Frequency)

ሠንጠረዥ 4 በቼክ ሊስት የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤት መግለጫ

| ተ ቁ | የማስተማር ክንውን | ቼ ክ ሊ ስ ት | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | | | | | ገጠር | | | | | ጠቅላላ | | | | |
| | | አዎ | | የለም | | ጠቅላላ | አዎ | | የለም | | ጠቅላላ | አዎ | | የለም | | ጠቅላላ |
| | | ድግ | % | ድግ | % | | ድግ | % | ድግ | % | | ድግ | % | ድግ | % | |
| 1 | ትምህርቱን በዓላማ ይጀምራል | 5 | 41.7 | 7 | 58.3 | 12 | 4 | 33.3 | 8 | 66.7 | 12 | 9 | 37.5 | 15 | 62.5 | 24 |
| 2 | ያለፈውን ትምህርት ይከልሳል | 5 | 41.7 | 7 | 58.3 | 12 | 6 | 50 | 6 | 50 | 12 | 11 | 45.8 | 13 | 54.2 | 24 |
| 3 | የቤት ሥራ ያርማል | 8 | 66.7 | 4 | 33.3 | 12 | 5 | 41.7 | 7 | 58.3 | 12 | 13 | 54.2 | 11 | 45.8 | 24 |
| 4 | መማሪያ መፅሃፉን ይጠቀማል | 8 | 66.7 | 4 | 33.3 | 12 | 7 | 58.3 | 5 | 41.7 | 12 | 15 | 62.5 | 9 | 37.5 | 24 |
| 5 | የክፍል ሥራ ይሰጣል | 7 | 58.3 | 5 | 41.7 | 12 | 6 | 50 | 6 | 50 | 12 | 13 | 54.2 | 11 | 45.8 | 24 |
| 6 | በክፍል ሥራ ጊዜ ለተማሪዎች እገዛ ያደርጋል | 5 | 41.7 | 7 | 58.3 | 12 | 3 | 25 | 9 | 75 | 12 | 8 | 33.3 | 16 | 66.7 | 24 |
| 7 | በራሳቸው ልምምድ እንዲያደርጉ ይተዋቸዋል | 4 | 33.3 | 8 | 66.7 | 12 | 4 | 33.3 | 8 | 66.7 | 12 | 8 | 33.3 | 16 | 66.7 | 24 |
| 8 | የቡድን ሥራ ያበረታታል | 3 | 25. | 9 | 75 | 12 | 5 | 41.7 | 7 | 58.3 | 12 | 8 | 33.3 | 16 | 66.7 | 24 |
| 9 | የቤት ሥራ ይሰጣል | 9 | 75 | 3 | 25 | 12 | 4 | 50 | 6 | 50 | 12 | 15 | 62.5 | 9 | 37.5 | 24 |
| 10 | የዕለቱን ትምህርት ያጠቃልላል | 6 | 50 | 6 | 50 | 12 | 5 | 41.7 | 7 | 58.3 | 12 | 11 | 48.8 | 13 | 54.2 | 24 |
| 11 | ዕለታዊ/ሳምንታዊ ዕቅድ ይዟል | 7 | 58.3 | 5 | 41.7 | 12 | 2 | 16.7 | 10 | 83.3 | 12 | 9 | 37.5 | 15 | 62.5 | 24 |
| 12 | የቀረበው ትምህርትና የተዘጋጀው ዕቅድ ይጣጣማሉ | 6 | 50 | 6 | 50 | 12 | 2 | 16.7 | 10 | 83.3 | 12 | 8 | 33.3 | 16 | 66.7 | 24 |
| 13 | ዕለታዊ/ሳምንታዊ ዕቅድ ከዓመታዊ ዕቅድ የተወሰደ ነው | 6 | 50 | 6 | 50 | 12 | 1 | 8.3 | 11 | 91.7 | 12 | 7 | 29.2 | 17 | 70.8 | 24 |

*ድግ=ድግግሞሽ (Frequency)

በሠንጠረዥ 3 እና 4 የቀረበው የክፍል ውስጥ ምልከታ ድግግሞሽ ነው። የመምህ ራኑን የክፍል ውስጥ ተግባራዊ ክንውን ያሳያል። ከሠንጠረዦቹ መረዳት እንደሚቻለው የተ ወሰኑ ክንውኖች ተግባራዊ ሲደረጉ አንዳንዶቹ በዝቅተኛ ሁኔታ ተግባራዊ ሆነዋል። በመርሃ ትምህርቱም ሆነ በመምህሩ መምሪያ እንዲያለማምዱ፥ እንዲያሳዩ ማድረግ፥ ተማሪዎች በራሳ ቸው እንዲደርሱባቸው ማመቻቸት፥ የመምህሩ ተግባራት መሆናቸው ተመልክቷል። በሠንጠረ ዥ 3 የቀረበው የዚህን ትግበራ ውጤት ነው። በመርሃ ትምህርቱም ሆነ በመምህሩ መምሪ ያ ላይ ያሉትን ተግባራት መምህራኑ የተመለከቷቸው መሆኑን በሰጧቸው ምላሾች አረጋግጠዋ ል። ሆኖም ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ከማድረግ አንፃር በቋንቋ ትምህርት በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ማስተማር ሂደት ተግባቦታዊ ስልት ከመጠቀምና በመርሃ ትምህርቱ የተገለፀውንና በመምህሩ መምሪያ የቀረበውን ከመፈፀም ይልቅ ቀደም ሲል የነበራቸውን ልምድና ዕውቀት ብቻ በመያዝ ክፍል ውስጥ ገብተው የሚያስተምሩ መሆናቸውን መመልከት ተችሏል።

ለተማሪዎች ጠቃሚ ነጥቦችን በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማሳየት በመምህሩ መምሪያ የተጠቀሰ ነው። በዚህ ረገድ በጥቅሉ በሠንጠረዥ 3 መሠረት 33.3% በተደጋጋሚ ሲጠቀሙ 58.3% አልፎ አልፎ ተጠቅመዋል 8.3% ደግሞ በሰሌዳው ላይ ምንም ነገር አልፃፉም። መማሪያ መፅሃፉን የሚጠቀሙ በሠንጠረዥ 4 መሠረት 62.5% በመሆናቸውና በአብዛኞዎቹ ትምህርት ቤቶች መፃህፍት አንድ ለአንድ ወይም አንድ ለሁለት የተከፋፈል በመሆኑ በሰሌዳው ላይ ለመፃፍ አስገዳጅነት ላይኖረው ይችላል። ሆኖም በቋንቋ ትምህርት መምህሩ ትምህርቱን ለማዛነቅ (Integrate) ሲባል አንዳንድ ነጥቦችን በሰሌዳው ላይ በመፃፍ ማሳየት ይጠበቅበታል። ትምህርቱን ለማዛነቅ ጥረት የሚያደርጉት 16.7% ሲሆኑ 58.3% አልፎ አልፎ 25% ደግሞ ምንም ጥረት የማያደርጉ ናቸው። እነዚህ ነጥቦች በጋራ የሚያሳዩት መምህራኑ በመርሃ ትምህርቱ የተጠቀሰውን ለማስተላለፍ ያላቸው ብቃት መካከለኛ መሆኑን ነው።

ተማሪዎቹ የተማሩትን ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲያገናዝቡ ማድረግ ከመምህሩ የሚጠበቅ ተግባር ነው። ይህም ትምህርቱን አይረሴ ከማድረጉም በላይ ተማሪዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ሲኖሩ የሚጠቀሙበትን የቋንቋ ስርዓት እንዲያዳብሩና እንዲያገናዝቡ ስለሚረዳ ነው። ነገር ግን በዚህ ረገድ 33.3% መምህራን በተደጋጋሚ ሲያከናውኑ 58.3% አልፎ አልፎ የሚያከናውኑ ናቸው። 8.3% የሚሆኑት አያከናውኑም። ይህ የመርሃ ትምህርቱ ን ትግበራ ብቃት የሚቀንስ ከመሆኑም በላይ በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በአብዛኛው በልምምድ ላይ ያተኮረ፥ ብዙዎቹን መልመጃ ዎች ከመምህሩ ይልቅ ተማሪው ማከናወን እንደሚኖርበት የቋንቋ ማስተማር ባለሙያዎች ይገልፃሉ። በምልከታው እንደታየው 20.8% የሚሆኑት ብቻ ሰፊውን ጊዜ ለተማሪው ልምም ድ ሲሰጡ 58.3% አልፎ አልፎ ለተማሪው የልምምድ ጊዜ ይሰጣሉ። 20.8% ለተማሪው ምንም የልምምድ ጊዜ አይሰጡም። ተማሪዎች ስለቋንቋው በራሳቸው ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ ከመምህሩ የሚጠበቅና መርሃ ትምህርቱን በተግባር የማዋል እንቅስቃሴ ነው።

66.7% የሚሆኑት መምህራን ተማሪዎች ልምምድ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ አይፈጥሩም።

በአንድ ክፍለ ጊዜ ክንውን ያለፈውን ትምህርት በመግቢያው ላይ መከለስና የዕለቱ ን ትምህርት ማቅረብ በመጨረሻም የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለል ተገቢነት ያለው አካሄድ ነው። 54.2% የሚሆኑት ያለፈውን ትምህርት በመከለስ ከመጀመራቸውም በላይ 54.2% የሚሆኑት በክፍለ ጊዜው መጨረሻ የዕለቱን ትምህርት ሳያጠቃልሉ ይወጣሉ። በመርሃ ትምህርቱም ሆነ በመምህሩ መምሪያ መምህሩ የዕለቱን ትምህርት በምን መልክ መጀመር እንደሚገባ ከመግለፃቸውም በላይ የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለያ በመስጠት መጨረስ እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ። አብዛኞዎቹ መምህራን ይህንን ሲያከናውኑ አልታዩም።

የመማር ማስተማር ሂደት በአንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ከክፍል ውጭም የሚቀጥል ነው። መምህራኑ በክፍል ውስጥ ሊከናወኑ የማይችሉ ተግባራትን ወይም በጊዜ እጥረት ሳይከናወኑ የሚቀሩ ተግባራትን በቤት ሥራ መልክ መስጠት ይኖርባቸዋል። በምልከታው መሠረት 62.5% የቤት ሥራ የሚሰጡ መሆኑ ተስተውሏል። በቤት ሥራ መልክ የተሰጠው ተግባር የትምህርቱ አካል በመሆኑ ተማሪዎች ማከናወን አለማከናወናቸው በመምህሩ መፈተሽ ይኖርበታል። ጥሩ የሰሩትን በማበረታታት ደከም ያሉትን በመምከር ለተከታዮቹ መልመጃዎች ማዘጋጀት የመምህሩ ተግባር ነው። 54.2% የሰጡትን የቤት ሥራ ሲያርሙ 45.8% እርማት ሳያደርጉ ወደ ሌላ ተግባር ይሸጋገራሉ። ይህም ተማሪዎቹ ወደፊት የሚሰጣቸውን የቤት ሥራ ለመስራት የሚኖራቸው ተነሳሽነት ሊቀንስ ይችላል።

የቀረበውን ትምህርት በክፍል ሥራ መልክ እንዲያከናውኑ የተለያዩ ተግባራትን መስጠት ተገቢ እንደሆነ ይታመናል። 54.2% የክፍል ሥራ የሚሰጡ ሲሆን የክፍል ሥራው ን እየተዘዋወሩ በማበረታታትና በመምከር ክንውኑ እንዲፈፀም ያላቋረጠ ድጋፍ ማድረግ ከመምህራን ይጠበቃል። ሆኖም 33.3% ብቻ ተገቢውን ድጋፍ ሲያደርጉ ቀሪዎቹ በክፍል ሥራ ጊዜ የፈተና ወረቀት በማረም፥ መፅሃፍ በማንበብ፥ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ክፍሉን ጥሎ በመሄድ ክፍለ ጊዜውን ሲፈፅሙ አልፎ አልፎ የሚሰጠው የክፍል ሥራና የሚተውለት ጊዜ ባለመመጣጠኑ የክፍል ሥራው ሳያልቅ ክፍለ ጊዜው ይጠናቀቃል። በመሆኑም የክፍል ሥራው ወደ ቤት ሥራነት ይለወጣል።

የቋንቋ መምህር የልምምድ ተግባራትን በቡድን እያከፋፈለ ተማሪዎቹ እንዲያከናውኑ ማቀናጀት ይኖርበታል። እርስ በርስ እንዲነጋገሩ እንዲተቻቹና እንዲማማሩ ከማድረጉም በላይ በጓደኞቻቸው ፊት ለመናገር የፃፉትንም ለማንበብ አስተያየት ለመስጠት ፍርሃታቸው ስለሚ ወገድ ነው። 66.6% መምህራን የቡድን ሥራ ሲያበረታቱና ሲያቀናጁ አልታዩም። በቋንቋ ትምህርት የቡድን ሥራ መበረታታት እንዳለበት በመምህሩ መምሪያ ተገልጿል።

መምህራኑ በሰጡት ምላሽና ርዕሰ መምህራኑም እንደገለፁት ከሆነ 90% የሚሆኑት መምህራን መርሃ ትምህርቱን በተገቢው ሁኔታና በብቃት ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል።

እስካሁን በቀረበው ትንተና በምርምሩ ሁለተኛ ጥያቄ መምህራኑ በመርሃ ትምህርቱ የተገለፀውን ተግባራዊ ለማድረግ ያላቸው ዝግጅት ምን ያህል እንደሆነ ምላሽ ተሰጥቷል።

## 4.3. የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማራመድ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊ ሁኔታዎች

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ሁለት ሠንጠረዦች የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ለኦሮምኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ትግበራ ለማራመድ በትምህርት ቤቱ መሟላት ያለባቸው ቁሳዊ ነገሮችና የለውጥ ተሳታፊዎች ሚና ይተነተናል። በአንድ የትምህርት አውድ መሠረታዊ የክፍል ውስጥ ቁሳቁስ የማስተማሪያ መሣሪያዎች፥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፥ ለተለያዩ ጉዳዮች የተመደበው ጊዜ፥ በርዕሰ መምህራን የሚደረግ ድጋፍ፥ የደብተሮች፥ የወረቀቶች፥ የመፃፊያዎች አቅርቦት የራሳቸው የሆነ ድርሻ ይኖራቸዋል። የለውጥ ተሳታፊ አካላት መምህራን ከመምህራን፥ መምህራን ከርዕሰ መምህራን ያላቸው ግንኙነት ምን መልክ እንዳለው መታየቱ በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ይህ ክፍል በጥናቱ መነሻ የተጠቀሰውን አራተኛ ጥያቄ የሚመልስ ይሆናል።

ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ 5 የቁሳቁስ አቅርቦት መግለጫ

| ተቁ | የመማሪያ ክፍል ገፅታ /ቁሳቁስ/ | መ ል ስ የ ሰ ጡ መ ም ህ ራ ን | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ N=4 | | | | | | ገጠር N=4 | | | | | | አጠቃላይ N=8 | | | | | |
| | | በቂ | | መካከለኛ | | የለም | | በቂ | | መካከለኛ | | የለም | | በቂ | | መካከለኛ | | የለም | |
| | | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % |
| 1 | የተማሪዎች መቀመጫና ጠረጴዛ | 2 | 50 | 1 | 25 | 1 | 25 | - | - | 2 | 50 | 2 | 50 | 2 | 25 | 3 | 37.5 | 3 | 37.5 |
| 2 | የመምህሩ መቀመጫና ጠረጴዛ | - | - | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - | - | - | 4 | 100 | - | - | 1 | 12.5 | 7 | 87.5 |
| 3 | ጥቁር ሰሌዳ | 3 | 75 | 1 | 25 | - | - | 2 | 50 | 2 | 50 | - | - | 5 | 62.5 | 3 | 37.5 | - | - |
| 4 | የማስታወቂያ ሰሌዳ በክፍል ውስጥ | 1 | 25 | 2 | 50 | 1 | 25 | - | - | - | - | 4 | 100 | 1 | 12.5 | 2 | 25 | 5 | 62.5 |
| 5 | የሰሌዳ ማፅጃ /ዳስተር/ | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - | - | - | 2 | 50 | 2 | 50 | 1 | 12.5 | 5 | 62.5 | 2 | 25 |
| 6 | የአማርኛ ትምህርት መርጃ | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - | - | - | 2 | 50 | 2 | 50 | 1 | 12.5 | 5 | 62.5 | 2 | 25 |
| 7 | መስኮት | 2 | 50 | 2 | 50 | - | - | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - | 3 | 37.5 | 5 | 62.5 | - | - |
| 8 | በር | 3 | 75 | 1 | 25 | - | - | 2 | 50 | 2 | 50 | - | - | 5 | 62.5 | 3 | 37.5 | - | - |
| 9 | የክፍሉ ስፋት ከተማሪዎች ብዛት አንፃር | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 50 | 2 | 50 | 1 | 25 | 1 | 25 | 3 | 37.5 | 2 | 25 | 3 | 37.5 |
| | ድምር | | | | | | | | | | | | | 29.2 | | 40.3 | | 30.5 | |

*ድግ=ድግግሞሽ (Frequency)

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ 6 ለመምህራን የተሰጡ የፅህፈት መሣሪያዎች

| ተቁ | የፅህፈት መሣሪያ አቅርቦት | መልስ የሰጡ መምህራን | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ N=4 | | | | | | ገጠር N=4 | | | | | | ጠቅላላ N=8 | | | | | |
| | | በቂ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በቂ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በቂ | | መካከለኛ | | የለም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ዓመታዊ ዕቅድ ማዘጋጃ ወረቀት | 4 | 100 | - | - | - | - | 3 | 75 | 1 | 25 | - | - | 7 | 87.5 | 1 | 12.5 | - | - |
| 2 | ሳምንታዊ ዕቅድ ማዘጋጃ ወረቀት | 3 | 75 | 1 | 25 | - | - | 3 | 75 | 1 | 25 | - | - | 6 | 75 | 2 | 25 | - | - |
| 3 | ደብተር | - | - | 3 | 75 | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 50 | 1 | 25 | 1 | 12.5 | 5 | 62.5 | 2 | 25 |
| 4 | መፃፊያ | 2 | 50 | 2 | 50 | - | - | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - | 3 | 37.5 | 5 | 62.5 | - | - |
| 5 | ፈተና ማዘጋጃ ወረቀት | 3 | 75 | 1 | 25 | - | - | 2 | 50 | 2 | 50 | - | - | 5 | 62.5 | 3 | 37.5 | - | - |

በሠንጠረዥ 5 የቀረበው በክፍል ውስጥ መሠረታዊ የሆኑና የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚደግፉ ሁኔታዎች ስርጭት ነው። በሠንጠረዥ 6 ደግሞ በትምህርት ቤቱ በኩል ለመምህራን የሚቀርቡ የፅህፈት መሣሪያዎች አቅርቦት ተዘርዝሯል። በከተማም ሆነ በገጠር ያሉ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ወንበርና ጠረጴዛ አቅርቦት ከበቂ በታች መሆኑን መረጃው ያመለክታል። 50% የሚሆኑ በከተማ የሚገኙ መምህራን የተማሪዎች ወንበርና ጠረጴዛ በቂ መሆኑን ሲገልፁ በገጠር ያሉ መምህራን በቂ አለመሆኑን አመልክተዋል። በድምር ሲታይም 25% ብቻ የወንበሮች አቅርቦት በቂ እንደሆነ ገልፀዋል።

በገጠርም ሆነ በከተማ የመምህሩ ጠረጴዛና ወንበር መሟላትን በተመለከተ 100% ከበቂ በታች መሆኑን ሲገልፁ 87.5% ጨርሶ እንደሌለ አመልክተዋል። በየትምህርት ቤቶቹ የተማሪዎችም ሆነ የመምህራን ወንበርና ጠረጴዛ በተሟላ መልኩ አለመገኘቱን መረጃው ያመለክታል።

በመማሪያ ክፍሎች 62.5% የሚሆኑ መላሾች ጥቁር ሰሌዳ በበቂ ሁኔታ እንደሚገኝ ሲገልፁ በገጠርና በከተማ የጎላ ልዩነት አልታየም። በአብዛኛዎቹ መማሪያ ክፍሎች ጥቁር ሰሌዳ በበቂ ሁኔታ መገኘቱን ያመለክታል። በክፍል ውስጥ ስዕሎችንና ፖስተሮችን ለመለጠፍ የሚያገለግል ሰሌዳ በ62.5% መላሾች የተሟላ አለመሆኑ ተገልጿል። የሰሌዳ ማፅጃ/ዳስተር በገጠርም ሆነ በከተማ ከበቂ በታች 87.5% መገኘቱን መላሾች አመልክተዋል።

የመማሪያ ክፍሎች ስፋት ከተማሪዎች ብዛት አንፃር የተገኘው ምላሽ 37.5% ተመጣጣኝ እንደሆነ 37.5% የማይመጣጠን እንደሆነ 25% መካከለኛ እንደሆነ ገልፀዋል።

በክፍል ውስጥ ያሉ የማስተማሪያ መሣሪያዎች /ቁሳቁስ/ 29.2% በቂ ነው ሲሉ 40.3% መካከለኛ 30.5% አለመሟላቱን ገልፀዋል። መረጃው የሚያሳየው አቅርቦቱ ከበቂ በታች መሆኑን ነው። (Ross እና Postiethwaite 1992:28) ዚንባቡዌ ውስጥ ባካሄዱት ጥናት በአብዛኛዎቹ አዳጊ አገሮች ተማሪዎች መሬት እንደሚቀመጡ/መቀመጫ እንደሌላቸው/የውስጥ አደረጃጀታቸው ከበቂ በታች መሆኑን ያመለከቱ ሲሆን በትምህርት ሚኒስቴር (1986:45) በ"ERGESE" ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ያለው አጠቃላይ የትምህርት ስርዓት ግምገማዊ ጥናት አብዛኛዎቹ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቁሳቁስ ያልተሟላ እንደሆነ አመልክቷል። ይህ ጥናትም ችግሩ እስካሁን ድረስ የቀጠለ መሆኑን ያሳያል።

በሠንጠረዥ 6 87.5% መላሾች በቂ የሆነ ዓመታዊ ዕቅድ ማዘጋጃ ወረቀት እንደሚቀርብላቸው አመልክተዋል። 75% የሚሆኑት ሳምንታዊ ዕቅድ ማዘጋጃ ቅፅ እንደሚሰጣቸው አመልክተዋል። የፈተና ማዘጋጃ ወረቀት በበቂ ሁኔታ ይቀርብልናል ያሉት 62.5% ሲሆኑ 12.5% የሚሆኑ የማስተማሪያ ፅሁፍ (Note) ማዘጋጃ ደብተር በበቂ ሁኔታ እንደሚቀርብላቸው ገልፀዋል። መፃፊያን በተመለከተ 37.5% በቂ ነው ሲሉ 62.5% ከበቂ በታች እንደሆነ

ጠቁመዋል። በገጠርና በከተማ ያለው ልዩነትም የጎላ አይደለም። የመምህራኑ ምላሽ ከርዕሰ መምህራኑ ምላሽ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ታይቷል።

በመረጃው መሠረት አብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች ለመምህራኑ በቂ የፅህፈት መሣሪያ እንደሚያድሉ መገንዘብ ተችሏል። ይህም መርሃ ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር መምህራን ለሚያሳዩት ትጋት አዎንታዊ ድርሻ ይኖረዋል።

ሠንጠረዥ 7 የማስተማሪያ መሣሪያዎች በበቂ ሁኔታ መገኘት ወይም አለመገኘትን የሚያሳይ

| የመፅሃፍ ዓይነት | መልስ የሰጡ መምህራን N=8 | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አለ | | የለም | | ጠቅላላ | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| መርሃ ትምህርት | 8 | 100 | - | - | 8 | 100 |
| የመምህር መምሪያ | 8 | 100 | - | - | 8 | 100 |
| የተማሪ መፅሃፍ | 5 | 62.5 | 3 | 37.5 | 8 | 100 |

በየትምህርት ቤቶቹ መርሃ ትምህርቱም ሆነ የመምህሩ መምሪያ 100% መላሾች የገለፁት የሚገኝ መሆኑን ነው። በአብዛኛው የሚታወቀው መርሃ ትምህርትም ሆነ የመምህር መምሪያ በየትምህርት ቤቱ የማይገኙ መሆኑን ነው። ይህ ጥናት ግን እነዚህ ማስተማሪያ መሣሪያዎች ከተማሪው መፅሃፍ ይልቅ የተዳረሱ መሆኑን አመልክቷል። ይህም በመርሃ ትምህርቱ ምን እንደታቀደ በመምህሩ መምሪያ ምን ዓይነት ስልት ተከትሎ ማስተማር እንደሚገባ መምህራኑ የማየት ዕድሉ አላቸው። በርዕሰ መምህራን በኩል የተማሪውን መፅሃፍ አስመልክቶ የተገኘው ምላሽ በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ጨርሶ እንዳልደረሰና በተወሰኑት ደግሞ ስርጭቱ አንድ ለአንድ (1:1) መሆኑን አመልክቷል። ሆኖም አንድ ለአንድ ተዳርሷል በተባለባቸው ትምህርት ቤቶች በምልከታው ጊዜ እንደታየው በክፍል ውስጥ መፅሃፍ ይዘው የተገኙት በጣት የሚቆጠሩ ተማሪዎች ብቻ ናቸው።

ሠንጠረዥ 8 የርዕሰ መምህራን ድጋፍ ከመምህራን ምላሽ የተገኘ

| ክንውን | አማራጮች | መልስ የሰጡ መምህራን N=8 | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | | ገጠር | | ጠቅላላ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| በርዕሰ መምህር በሴሚስተር ምን ያህል ጊዜ ይጎበኛሉ | 1 | 4 | 100 | 2 | 50 | 6 | 75 |
| | 2 | - | - | 2 | 50 | 2 | 25 |
| | 3 | - | - | - | - | - | - |
| | ከዚያ በላይ | - | - | - | - | - | - |
| ጉብኝቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚያግዝ መልኩ ነው | አዎ | 4 | 100 | 4 | 100 | 8 | 100 |
| | አይደለም | - | - | - | - | - | - |
| ለመርሃ ትምህርቱ ትግበራ የተሳካ መሆን ከትምህርት ቤቱ ድጋፍ ይደረግልዎታል | አዎ | 3 | 75 | 4 | 100 | 7 | 87.5 |
| | አይደረግልኝም | 1 | 25 | - | - | 1 | 12.5 |
| የሚደረግልዎ ድጋፍ በየትኛው ደረጃ ይካተታል | ከፍተኛ | 1 | 25 | 4 | 100 | 5 | 62.5 |
| | መካከለኛ | 2 | 50 | - | - | 2 | 25 |
| | ዝቅተኛ | 1 | 25 | - | - | 1 | 12.5 |
| ችግር ሲያጋጥምዎ በመወያየት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ያደርጋሉ | አዎ | 4 | 100 | 4 | 100 | 8 | 100 |
| | አላደርግም | - | - | - | - | - | - |

በመርሃ ትምህርት ትግበራ ላይ የለውጥ ተሳታፊዎች ሚና ምን እንደሚመስል በምዕራፍ ሁለት ተዘርዝሯል። በሠንጠረዥ 8 መምህራኑ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር የተደረገላቸውን ድጋፍ በሚመለከት የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ተተንትኗል። ርዕሳነ መምህራን በትምህርት ቤታቸው መልካም የሆነ የመማር ማስተማር ድባብ በመፍጠር ረገድ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው። መምህሩ ከርዕሰ መምህሩ ጋር የሚኖረው የሰመረ ግንኙነትና የሚደረግለት ድጋፍ መኖር በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል። (Ornstein እና Hunkins 1998:228-243) እንደሚገልፁት ጠንካራ የሆኑ ርዕሳነ መምህራን የመርሃ ትምህርት ትግበራ የተሳካ እንዲሆን ጥረት ቢያደርጉም ይህ በሁሉም ርዕሳነ መምህራን ዘንድ የተሳካ እንደማይሆን በዚህም ምክንያት የታቀዱ ዓላማዎች እንደሚጨናገፉ ያስረዳሉ። በዚህ ጥናት የታየው እንደሚያመለክተው መምህራን የሚጎበኙት (የክፍል ውስጥ ምልከታ) በሴሚስተር አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ የገለፁት በከተማ 100% በገጠር 50% ናቸው። በከተማ ያሉ ርዕሳነ መምህራን ካለው የመምህራንና የክፍሎች ብዛት አንፃር የጊዜ እጥረትን እንደምክንያት አድርገው ለጉብኝቱ ጊዜ የሚያንሳቸው መሆኑን ያቀርባሉ። በምዕራፍ ሁለት እንደተጠቀሰው አብዛኛዎቹ ርዕሳነ መምህራን የትምህርቱን ሥራ ከመስራት ይልቅ ወደ አስተዳደራዊና ግላዊ ተግባር እንደሚያዘነብሉ ተጠቅሷል። ይህ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ድርሻ ይኖረዋል።

ሆኖም በሴሚስተር አንድ ጊዜ በሚያደርጉት ጉብኝት 100% መላሾች የመማር ማስተ ማሩን ሂደት በሚያግዝ መልኩ መሆኑን ጠቁመዋል። ለመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ድጋፍ የሚደረግላቸው 87.5% ሲሆኑ 12.5% ድጋፍ እንደማይደረግላቸው ገልፀዋል። የሚደረግላቸውን የድጋፍ ደረጃ ሲመልሱ 62.5% ከፍተኛ 25% መካከለኛ 12.5% ዝቅተኛ እንደሆነ አመልክተዋል።

መምህራን በሥራቸው ሂደት ለሚገጥማቸው ችግር የጋራ መፍትሄ ለመፈለግ በመነጋገ ር መስራት ይጠበቅባቸዋል። (Fullan 199:2) እንደገለፁት በመምህራን እርስ በርስና በርዕሰ መምህሩ መካከል ሙያዊ ትስስር ካለ (ተባብሮ የመስራት ባህሉ ከዳበረ) የትምህርት ሂደቱ የሰመረ ይሆናል። በዚህም ጥናት የተገኘው ውጤት መምህራኑ ተባብሮ የመስራት ባህል እንዳላቸው የሚያመለክት ነው። በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ላይም በጎ ድርሻ ይኖረዋል።

ሠንጠረዥ 9 የተመደበው ክፍለ ጊዜ፥ የመምህራን ጫናና የተማሪዎችን ብዛት የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ምላሽ የተሰጠባቸው መጠይቆች | አማራጮች | መልስ የሰጡ መምህራን | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | | ገጠር | | ጠቅላላ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| ለትምህርቱ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በመርሃ ትምህርቱ የቀረበውን በወቅቱ ለማጠናቀቅ በቂ ነው | አዎ | - | - | 2 | 50 | 2 | 25 |
| | አይደለም | 4 | 100 | 2 | 50 | 6 | 75 |
| በሳምንት የያዙት የክፍለ ጊዜ ብዛት በማስተማር ሥራዎ ላይ ጫና አሳድሯል | አዎ | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 25 |
| | አላሣደረም | 3 | 75 | 3 | 75 | 6 | 75 |
| በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ብዛት በመማር ማስተማሩ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል | አዎ | 2 | 50 | 4 | 100 | 6 | 75 |
| | አላሣደረም | 2 | 50 | - | - | 2 | 25 |

ከሠንጠረዥ ዘጠኝ መረዳት የሚቻለው የተመደበውን ትምህርት በወቅቱ ለማጠናቀቅ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ አይደለም ያሉት በከተማ 100% ሲሆን በገጠር 50% ናቸው። በድምሩ 75% የሚሆኑ በቂ አለመሆኑን አመልክተዋል። በሳምንት የተመደበው ክፍለ ጊዜ ሁለት ብቻ በመሆኑ ትምህርቱ ሙሉ በሙሉ ሳይሸፈን ዓመቱ እንደሚያልቅ ያስረዳል።

መምህራኑ በሳምንት የያዙት ክፍለ ጊዜ ብዛት በመማር ማስተማሩ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ተጠይቀው 75% አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳላሳደረባቸው አመልክተዋል። ይህም መምህራኑ በሳምንት የያዙት ክፍለ ጊዜ ብዛት ተጠይቀው በሰጡት መልስ (አባሪ ሰባትን ይመልከቱ) 87.5% ከ20 ክፍለ ጊዜ በታች የያዙ መሆኑ ተመልክቷል። የክፍለ ጊዜው ብዛት አሁን

በሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ ብዙ ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ የመምህራኑ መልስ ከዚህ ጋር የሚገናዘብ ይሆናል።

በመማር ማስተማር ሂደት በአንድ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ያሳደረው ተፅዕኖ እንዳለ ተጠይቀው ሲመልሱ በከተማ 50% በገጠር 100% አሉታዊ ተፅዕኖ አለው ሲሉ በድምሩ 75% የሚሆኑት የተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ መብዛት አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው አመልክተዋል። እስካሁን በተደረጉ ጥናቶች በአዳጊ አገሮች በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር በርካታ እንደሆነና ተማሪውን በተናጠል አውቆ ለመርዳትና ቡድናዊ ሥራ በመስጠት ለማለማመድ አስቸጋሪ እንደሆነ ይጠቁማሉ። ይህ ጥናት በተካሄደባ ቸው ትምህርት ቤቶች በአንድ ክፍል ውስጥ በአማካይ 83 ተማሪዎች እንደሚማሩ የጠቆሙ ሲሆን ይህ ቁጥር ከክፍሎች ስፋትና ከወንበሮች ብዛት አንፃር ሲታይ በርካታ ነው የሚያሰ ኝ በመሆኑ የመምህራኑ መልስ ተገቢ ሆኖ ይታያል። በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪው በግልና በቡድን በርካታ መለማመጃዎችን መስራት የሚጠበቅበት በመሆኑ የተማሪው ቁጥር በአንድ ክፍል ውስጥ መብዛት የትግበራው ሂደት እንደሚወስነው ይታመናል።

ሠንጠረዥ 10 የመምህር መምሪያው ይዘት ከመማሪያ መፅሃፉ አንፃር

| የቀረቡ መጠይቆች | አማራጮች | መልስ የሰጡ መምህራን N=8 | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | | ገጠር | | ጠቅላላ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| የመምህር መምሪያው በተማሪው መፅሃፍ የቀረበውን ለማስተማር በቂ መነሻ ነው | አዎ | 4 | 100 | 3 | 75 | 7 | 87.5 |
| | አይደለም | - | - | 1 | 25 | 1 | 12.5 |
| የተማሪዎች መፅሃፍ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው_____ ነው | ተስማሚ | 4 | 100 | 4 | 100 | 8 | 100 |
| | ቀላል | - | - | - | - | - | - |
| | አስቸጋሪ | - | - | - | - | - | - |
| ስለ ቋንቋ ትምህርት በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፓሊሲ የተገለፀውን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ አለው | አዎ | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 25 |
| | በመጠኑ | 3 | 75 | 3 | 75 | 6 | 75 |
| | የለኝም | - | - | - | - | - | - |
| ተዘጋጅተው ከቀረቡት ውጭ ሌሎች ማስ ተማሪያዎች ይጠቀማሉ | አዎ | 3 | 75 | 3 | 75 | 6 | 75 |
| | አልተጠቀመም | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 25 |
| እንደ ዋና የማስተማሪያ መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙት | መርሃ ትምህርት | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 25 |
| | የተማሪው መፅሃፍ | 2 | 50 | 2 | 50 | 4 | 50 |
| | የመምህሩ መፅሃፍ | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 25 |
| መፅሃፍት ቤት ስለመኖሩ | አለ | 1 | 25 | - | - | 1 | 12.5 |
| | የለም | 3 | 75 | 4 | 100 | 7 | 87.5 |

በሠንጠረዥ 10 የቀረበው መረጃ መምህራኑ ስለማስተማሪያ መሣሪያዎቹና ስለአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ያላቸው ግንዛቤ በሚመለከት ነው። የመምህሩ መምሪያ የተማሪውን መፅሃፍ ይዞ ለማስተማር በቂ መነሻ ነው ያሉት 87.5% ናቸው። 100% የተማሪው መፅሃፍ ለማስተማር ተስማሚ መሆኑን አመልክተዋል። 50% የሚሆኑ መላሾች የተማሪው መፅሃፍ ከሌሎቹ ይልቅ በማስተማሪያ መሣሪያነት እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ ከነዚህ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ውጪ ተጨማሪ ሌሎች መፃህፍትን የሚገለገሉ 75% መሆናቸው ተመልክቷል። ቅኔ መፃህፍትን፥ ልቦለድ መፃህፍትን፥ የአማርኛ ፈሊጦች የሚያቀርቡ መሆና ቸውንም ገልፀዋል።

አዲሱን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ አስመልክቶ ያላቸው ግንዛቤ መጠነኛ እንደሆነ 75% የሚሆኑ የገለፁ ሲሆን መምህራን ስለትምህርት ፖሊሲና የትምህርት ዕቅድ በቂ ግንዛቤ ከሌላቸው ለመርሃ ግብሩ ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ተሳትፎ አናሳ ሊሆን እንደሚችል በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል።

የመማር ማስተማርን ሂደት ለማገዝ በየትምህርት ቤቶቹ ቤተመፃህፍት መኖሩ

አስፈላጊ ነው። ሆኖም የርዕሳነ መምህራኑ ምላሽ የሚያሳየው 87.5% ትምህርት ቤቶች ቤተ መፃህፍት እንደሌላቸው በጥናቱ ተመልክቷል።

በሠንጠረዥ 10 ላይ በመመሥረት የቀረቡት ትንታኔዎች በትምህርት ቤት ያለው የመማር ማስተማር ሁኔታ ያሳያሉ። ይህም የመርሃ ትምህርቱ ትግባራ በምን ደረጃ እንዳለ የራሱን ጥቆማ የሚሰጥ ይሆናል።

## 4.4. የመርሃ ትምህርትን ትግበራ ሂደት የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ሠንጠረዥ መምህራኑ በተፅዕኖ አድራሽነታቸው አንፃር ደረጃ እንዲያወጡላቸው ተደረጎ የእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር ውጤት አማካይ ተወስዶ የተገኘውን ደረጃ የያዘ ነው።

ሠንጠረዥ 11 በመርሃ ትምህርት ትግበራ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ ተብለው የሚገመቱ ተላውጦዎችና በመምህራኑ የተሰጣቸው ደረጃ

| ተቁ | ሁኔታዎች | መልስ የሰጡ መምህራን | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | | ገጠር | | ጠቅላላ | |
| | | አማካይ | ደረጃ | አማካይ | ደረጃ | አማካይ | ደረጃ |
| 1 | የማስተማሪያ መሣሪያ እጥረት | 5.2 | 3 | 4.5 | 4 | 4.8 | 2 |
| 2 | የክፍለ ጊዜ ማነስ | 3.2 | 1 | 5.5 | 5 | 4.3 | 1 |
| 3 | አማርኛን ለማስተማር ደስተኛ አለመሆን | 6 | 5 | 7.5 | 8 | 6.7 | 8 |
| 4 | የትምህርት ቤቱ ድጋፍ ዝቅተኛ መሆን | 7.7 | 9 | 9.2 | 11 | 8.4 | 11 |
| 5 | በቂ የሙያ ማሻሻያ አለመኖር | 9 | 12 | 6.7 | 7 | 7.7 | 9 |
| 6 | የተማሪው ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት | 5.5 | 4 | 4.5 | 3 | 5 | 3 |
| 7 | አማርኛ ቀላል ትምህርት ነው የሚል አመለካከት | 5 | 2 | 7.5 | 8 | 6.2 | 6 |
| 8 | የተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር አለመፈለግ | 8.2 | 11 | 7.5 | 8 | 7.8 | 10 |
| 9 | የሰለጠኑ ባለሙያዎች እጥረት | 7.5 | 6 | 11.2 | 12 | 9.3 | 12 |
| 10 | አዲሱን መርሃ ትምህርት ለመገንዘብ የሚደረገው ጥረት አነስተኛ መሆን | 7.5 | 6 | 5.7 | 6 | 6.6 | 7 |
| 11 | የአካባቢ ተፅዕኖ | 8 | 10 | 4 | 2 | 6 | 5 |
| 12 | ስለ ፖሊሲው ያለ ግንዛቤ አናሳነት | 7.5 | 6 | 3.7 | 1 | 5.6 | 4 |

ተፅዕኖ ያሳድራሉ ተብለው የሚታሰቡ ሃሳቦችን በሠንጠረዥ 11 እንደሚታየው መምህራኑ በደረጃ አስቀምጠዋቸዋል። እያንዳንዱ መምህር የሰጠው መልስ ደረጃ በከተማና በገጠር ተለይቶ አማካይ (Mean) ወጥቶለታል። በጠቅላላው ደግሞ የተፅዕኖ አድራጊዎቹን ደረጃ ለመለየት የአጠቃላይ መላሾች ድምሩ አማካይ ደረጃ ተቀምጧል። በተገኘው አማካይ ደረጃ (Mean rank) መሠረት አንደኛ ሆኖ የተገኘው የክፍለ ጊዜ ማነስ ነው። የማስተማሪያ

መሣሪያዎች እጥረትና የተማሪው ቁጥር በአንድ ክፍል ውስጥ መብዛት ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ይዘዋል።

ይህ ውጤት በሠንጠረዥ 9 እንደተመለከተው የክፍለ ጊዜው አነስተኛ መሆንን ከገለፁት 75% ጋር የሚስማማ ነው። የትምህርት ቤቱ ድጋፍና የሰለጠኑ ባለሙያዎች እጥረት የሚሉት ከሚያሳድሩት ተፅዕኖ አንፃር አሥራ አንደኛና አሥራ ሁለተኛውን ደረጃ ይዘው ይገኛሉ። ይህም በሠንጠረዥ 7 62.5% የሚሆኑ ከትምህርት ቤቱ ድጋፍ እንደሚደረ ግላቸው ከገለፁት ጋር የሚስማማ ነው። 62.5% ለደረጃው የሚመጥነውን (12+2) ደረጃ የያዙ መሆናቸው (አባሪ ሰባት ይመልከቱ) ስልጠናቸው በቂ እንደሆነ ያሳያል። ይህም ችግሩ አነስተኛ እንደሆነ ይጠቁማል።

በዚህ መልክ አምስተኛው የምርምር ጥያቄ ምላሽ ያገኘ ሲሆን የትኞቹ ተፅዕኖዎች በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊነት እንዳላቸው ሊያሳይ ችሏል።

## 4.5. የተማሪዎች የብቃት መለኪያ ፈተና

ይህ ክፍል ከምርምሩ ጥያቄዎች ሦስተኛውን ለመመለስ የሚያስችል ሲሆን የተማሪዎቹ ውጤት ቀጥሎ ባሉት ሠንጠረዦች ተጠናቅሯል።

ሠንጠረዥ 12 በየትምህርት ክፍሎቹ ከማለፊያ ወሰን በላይና በታች ያመጡ የከተማና የገጠር ተማሪዎች ጥቅል ውጤት በመቶኛ

| የትምህርት ክፍል | ፆታ | ተ ማ ሪ ዎ ች | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | | | | ገጠር | | | | ጠቅላላ | | | |
| | | በላይ | | በታች | | በላይ | | በታች | | በላይ | | በታች | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| ንባብና ማስተዋል | ወ | 78 | 48.8 | 12 | 7.5 | 72 | 45 | 23 | 14.4 | 150 | 46.9 | 35 | 10.9 |
| | ሴ | 57 | 35.6 | 13 | 8.1 | 56 | 35 | 9 | 5.6 | 113 | 35.3 | 22 | 6.9 |
| | ድ | 135 | 84.4 | 25 | 15.6 | 128 | 80 | 32 | 20 | 263 | 82.2 | 57 | 17.8 |
| ፅሀፈት | ወ | 64 | 40 | 26 | 16.2 | 59 | 36.8 | 36 | 22.5 | 123 | 38.4 | 62 | 19.4 |
| | ሴ | 55 | 34.4 | 15 | 9.4 | 47 | 29.4 | 18 | 11.2 | 102 | 31.9 | 33 | 10.3 |
| | ድ | 119 | 74.4 | 41 | 25.6 | 106 | 66.3 | 54 | 33.7 | 225 | 70.3 | 95 | 29.7 |
| ሥነ ልሳን | ወ | 55 | 34.4 | 35 | 21.9 | 52 | 32.5 | 13 | 26.9 | 107 | 33.4 | 78 | 24.4 |
| | ሴ | 47 | 29.4 | 23 | 14.4 | 32 | 20 | 33 | 20.6 | 79 | 24.7 | 56 | 17.5 |
| | ድ | 102 | 63.7 | 58 | 36.3 | 84 | 52.5 | 76 | 47.5 | 186 | 58.1 | 134 | 41.9 |
| ጠቅላላ | ወ | 59 | 36.9 | 31 | 19.4 | 50 | 31.3 | 45 | 28.1 | 109 | 34.1 | 76 | 23.8 |
| | ሴ | 48 | 30 | 22 | 13.7 | 38 | 23.8 | 27 | 16.9 | 86 | 26.9 | 49 | 15.3 |
| | ድ | 107 | 66.9 | 53 | 33.1 | 88 | 55.4 | 72 | 45 | 195 | 60.9 | 125 | 39.1 |

ሠንጠረዥ 13 በብቃት መለኪያ ፈተና የከተማና የገጠር ተማሪዎች ከማለፊያ ወሰን በላይና በታች ያስመዘገቡት ውጤት ንፅፅር

| የትምህርት ምድብ | ተ ማ ሪ ዎ ቹ | | |
|---|---|---|---|
| | የብቃት ደረጃ | ከተማ | ገጠር |
| ንባብና ማስተዋል 01 | በላይ | 135 | 128 |
| | በታች | 25 | 32 |
| | ድምር | 160 | 160 |
| | $X^2 = 0.768$ | | |
| ፅህፈት 02 | በላይ | 119 | 106 |
| | በታች | 41 | 54 |
| | ድምር | 160 | 160 |
| | $X^2 = 3.25$ | | |
| ሥነ ልሳን 03 | በላይ | 102 | 84 |
| | በታች | 58 | 76 |
| | ድምር | 160 | 160 |
| | $X^2 = 3.71$ | | |

ሠንጠረዥ 14 በወረዳዎች መሀከል ማለፊያ ወሰንን መሠረት በማድረግ በየትምህርት ክፍሉ ያስመዘገቡት ውጤት

| የትምህርት ክፍሉ | ተ ማ ሪ ዎ ች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የብቃት ደረጃ | አዳማ | ሉሜ | አደአ | አዳሚቱሉ | ጠቅላላ |
| ንባብና ማስተዋል 01 | በላይ | 71 | 69 | 60 | 63 | 263 |
| | በታች | 9 | 11 | 20 | 17 | 57 |
| | ድምር | 80 | 80 | 80 | 80 | 320 |
| | $X^2 = 6.14$ | | | | | |
| ፅህፈት 02 | በላይ | 59 | 64 | 45 | 57 | 225 |
| | በታች | 21 | 16 | 35 | 23 | 95 |
| | ድምር | 80 | 80 | 80 | 80 | 320 |
| | $X^2 = 9.591$ | | | | | |
| ሥነ ልሳን 03 | በላይ | 57 | 43 | 37 | 49 | 186 |
| | በታች | 23 | 37 | 43 | 31 | 134 |
| | ድምር | 80 | 80 | 80 | 80 | 320 |
| | $X^2 = 11.243$ | | | | | |

በሠንጠረዥ 12 የቀረበው በየትምህርት ክፍል የተመዘገበውን ውጤት ሲሆን ይህም በያታ፥ በገጠር በከተማና በጥቅል እንዲሁም ከአጠቃላይ 40 ጥያቄዎች ምን ያህሉ ከማለፊያ ወሰን በላይና በታች እንደሆኑ የሚያሳይ ነው። ይህ ሠንጠረዥ በሠንጠረዥ 13 እና 14 ለቀረበው ትንታኔ መርጃ ሆኖ ያገለግላል።

በሠንጠረዥ 14 መሠረት በወረዳዎች መካከል ልዩነት እንዳለ ለማየት በተደረገው ስሌት የንባብና ማስተዋል ($x^2$=6.14) ተገኝቷል። (አባሪ 8ለ) ይህም ($x^2$, df=3, 0.05= 7.815) የወሳኝ ($x^2$) ዋጋ "Critical chisquare value" በመሆኑና በደረጃው $P \leq 0.05$ በሚለው መርህ በወረዳዎች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል። በየወረዳዎቹ ያሉ ተማሪዎች ይህንን የትምህርት ክፍል በተመለከተ ያስመዘገቡት ውጤት የተራራቀ አይደለም ሠንጠረዥ 12 ቢታይ 84.4% በከተማ 80% በገጠር ከማለፊያ ወሰን በላይ አስመዝግበዋል።

የፅህፈት ትምህርት ውጤታቸውን በተመለከተ በተሰራው ስሌት $x^2$=9.591 ተገኝቷል። ይህ ስሌት የወሳኝ $x^2$ ዋጋ ($x^2$, df=3, 0.05= 7.815) በመሆኑ ውጤቱ በልጦ ይታያል። ይህም $P \leq 0.05$ መርህ መሠረት በወረዳዎቹ መሀከል ልዩነት ያለ መሆኑን ያሳያል። ከማለፊያ ወሰን በላይና በታች ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር በየወረዳዎቹ ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል። ሠንጠረዥ 12 ያለው መረጃ እንደሚያመለክተው በሉሜ ወረዳ 80% ያለፉ ሲሆን በአደአ ወረዳ 56.25% ብቻ አልፈዋል። ይህም በየወረዳዎቹ ጉልህ የሆነ የአተገባበር ልዩነት እንዳለ ያሳያል።

በሥነ ልሳን ትምህርት በየወረዳዎቹ ያሉት ተማሪዎች ውጤት ተነፃፅሯል። በዚህም ስሌት $x^2$=11.243 ሆኖ ተገኝቷል። የወሳኝ $x^2$ ዋጋ ($x^2$, df=3, 0.05=7.815) በመሆኑና በ $P \leq 0.05$ መሠረት በወረዳዎቹ መካከል ስታትስቲካዊ ልዩነት የተመዘገበ መሆኑን ያሳያል። ይህ ውጤት ከሠንጠረዥ 12 አመዘጋገብ ጋር ሲገናዘብ በአዳማ ወረዳና በአደአ ወረዳ ያለው ልዩነት ከፍተኛ እንደሆነ ተመዝግቧል። አዳማ 71.25% ያለፉ ሲሆን አደአ 46.25% ብቻ ናቸው ያለፉት በሌሎችም ወረዳዎች ልዩነት መኖሩን ሠንጠረዡ ያመለክታል።

አጠቃላዩን ልዩነት ለመመልከት ሠንጠረዥ 12 መመልከት ያስፈልጋል። ንባብና ማስተዋልን በሚመለከት 84.4% ከከተማ ያለፉ ሲሆን 80% ከገጠር አልፈዋል። የ $x^2$=0.76 ውጤት ተገኝቷል። ቢሆንም ልዩነቱ የጎላ አለመሆኑን ያሳያል። ፅህፈትን በሚመለከት 74.4% ከከተማ 66.3% ከገጠር አልፈዋል። በንፅፅሩም የ $x^2$=3.25 በመሆኑ የጎላ ስታትስቲካዊ ልዩነት እንዳለ ያመለክታል። ይህም የገጠር ዝቅ እንደሚል ያሳያል። የሥነ ልሳን ትምህርትን በተመለከተ 63.7% ከከተማ 52.5% ከገጠር አልፈዋል። $x^2$=3.71 በመገኘቱ ይህም በውጤት ልዩነት የሚታይባቸው መሆኑን ይጠቁማል። በዚህም የገጠሮቹ ዝቅ ብለዋል። በቀረቡት ሦስት የትምህርት ክፍሎች በድምሩ 66.9% ከከተማ 55.4% ከገጠር አልፈዋል። በዚህ ጥናትም ከገጠር ተማሪዎች ይልቅ የከተማ ተማሪዎች የተሻለ

ነጥብ እንዳስመዘገቡ ማየት ተችሏል። ይህም ቀደም ሲል የተቀመጠውን ግምት ትክክለኛነት አረጋግጧል።

የትምህርት ዓላማዎችንና የትምህርት ክፍሎችን መሠረት በማድረግ በቀረበው የብቃት መለኪያ ፈተና ንባብና ማስተዋልን 82.2% ከማለፊያ ወሰን በላይ አግኝተውበታል። ፅህፈት ን 70.3% ከማለፊያ ወሰን በላይ አግኝተውበታል። በሥነ ልሳን ደግሞ 58.1% ከማለፊያ ወሰን በላይ አግኝተውበታል። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ንባብና ማስተዋል ከፅህፈትና ከሥነ ልሳን የትምህርት ክፍሎች ይልቅ ከፍ ያለ አተገባበር የታየበት መሆኑን ነው።

የሥነ ልሳን ትምህርት ከቀረቡት ሌሎች ሁለት የትምህርት ክፍሎች ዝቅተኛውን የአላፊዎች ቁጥር ይዟል። ይህም 58.1% ነው። ይህም 63.7% በከተማ ሲሆን 52.5% በገጠር ነው። ከመምህራኑ ምላሽ እንደተገኘው በገጠር 50% የሚሆኑት ለደረጃው በቂ ስልጠና የሌላቸው በመሆኑና የሥነ ልሳን ትምህርትን ለማስተማር ስልጠና የግድ አስፈላጊ በመሆኑ የተማሪዎቹ ውጤት ከዚህ የተነሳ ዝቅተኛ እንደሆነ መገመት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 14 የ$x^2$ ውጤት መሠረት በፅህፈትና በሥነ ልሳን ትምህርት ውጤት በወረዳዎች መካከል ልዩነት ተመዝግቧል። ይህም መርሃ ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር የሚታይ ልዩነት ነው።

ሠንጠረዥ 12÷ 13 እና 14 የምርምሩን ሦስተኛ ጥያቄ የመለሱ ሲሆን 60.9% ተማሪዎች አልፈዋል። 39.1% አላለፉም የመርሃ ትምህርቱ ትግበራ በዚሁ መጠን የተሳካ መሆኑን ስሌቱ ያመለክታል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ፥ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳቦች

### 5.1. ማጠቃለያ

ጥናቱ በኦሮሚያ ክልል በተለይ በምስራቅ ሸዋ ዞን አፋቸውን በኦሮምኛ ለፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት መገምገም ችግሮችን መለየትና መፍትሄ መጠቆም ነው። ገለፃዊ ቅኝት የመረጃ አተናተን ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል። ለመረጃም ከዞኑ ከሚገኙ አሥራ ሁለት ወረዳዎች አራቱ ከተመረጡ በኋላ ከየወረዳዎቹ ሁለት ሁለት ትምህርት ቤቶች /አንድ ከከተማ አንድ ከገጠር ተመርጠዋል። የፅሁፍ መጠይቅ፥ የክፍል ውስጥ ምልከታ እንዲሁም የብቃት መለኪያ ፈተና ከየትምህርት ቤቶቹ መምህራን ርዕሰ መምህራንና ከተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ አገልግለዋ ል። የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ይጠቃለላል።

አንደኛ፥ መምህራኑ ስለአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ያላቸው ግንዛቤ 75% መጠነኛ ነው። ይህም የመርሃ ትምህርቱን ትግበራ የተሟላ አያደርገውም። የግንዛቤው ችግር በሠንጠረዥ 11 መሠረት አራተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል። መምህራን ስለአዲሱ የትምህርት ፕሮግራም በቂ ግንዛቤ ከሌላቸው የትግበራ ሂደት በሙሉም ሆነ በከፊል ሊደናቀፍ እንደሚ ችል ይታመናል። (ቻርት 4 ያገናዝቧል)

ሁለተኛ፥ በክፍል ውስጥ በተካሄደው ምልከታ 58.3% መምህራን የክፍል ሥራና የቤት ሥራ የሚሰጡ ሲሆን 54.2% የሚሆኑት የሰጡትን የቤት ሥራና የክፍል ሥራ ያርማሉ። ከግማሽ በላይ የሚሆኑት መምህራን በታቀደው መሠረት እያከናወኑ ይገኛሉ ማለት ያስችላል።

ሦስተኛ፥ ከመምህራኑ 75% የሚሆኑት መርሃ ትምህርቱን በተገቢው መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ ስልጠና እንደሚያስፈልጋቸው ገልፀዋል። በመሆኑም በክፍል ምልከታው ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ለማድረግ ጥረት ያደረጉት 25% የሚሆኑት ብቻ ናቸው። ይህም ከተከታታይ ስልጠና ማነስ የመነጨ ሊሆን ይችላል።

አራተኛ፥ ቁሳዊ አደረጃጀት ላይ 40.3% መካከለኛ 29.2% በቂ አቅርቦት እንዳለ አመልክተዋል። ምንም ያልተሟላባቸው 30.5% ናቸው። ይህም መርሃ ትምህርቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ ዝቅተኛ ነው።

አምስተኛ፥ የፅሁፍ መጠይቅ ከቀረበላቸው መምህራን 75% የሚሆኑት በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የሚጎበኙት በሴሚስተር አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ ሲገልፁ 87.5%

የሚሆኑት ጉብኝቱ የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚደግፍ መልኩ መሆኑን ገልፀዋል። የጉብኝቱ ድግግሞሽ አነስተኛ ቢሆንም መልካም የሆነ የሥራ ግንኙነት የሚፈጥር ሆኖ ታይቷል።

ስድስተኛ፥ በአንድ ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች በአማካይ 83 መሆኑ በመማር ማስተማሩ ላይ አሉታዊ ድርሻ አበርክቷል። ተማሪዎችን በተናጠልና በቅርበት ለማገዝ አላስቻለም፤ የክፍልና የቤት ሥራ ሰጥቶ ለማረም አላመቸም፤ ተማሪዎችን በቡድን ከፋፍሎ ለማሰራትና ለመቆጣጠር አላስቻለም።

ሰባተኛ፥ ለትምህርቱ በሳምንት የተመደበው ሁለት ክፍለ ጊዜ በቂ አለመሆኑን 75% የሚሆኑት አመልክተዋል። ይህም በቂ መለማመጃ ለመስጠት የቤት ሥራና የክፍል ሥራ ለመስጠትና ለማረም፥ የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት በተገቢው ጊዜ ለማጠናቀቅ እንደማያስ ችል ጠቁመዋል። መምህራኑ በደረጃ ሲያስቀምጡም የክፍለ ጊዜውን ማነስ አንደኛ ደረጃ ላይ አስይዘውታል።

ስምንተኛ፥ በብቃት መለኪያው ፈተና መሠረት 60.9 ያለፉ ሲሆን 39.1 ማለፍ አልቻሉም። ይህም የመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ከግማሽ በላይ የተሳካ መሆኑን ያሳያል። ሆኖም አስተማማኝ ውጤት ነው ማለት የሚቻልበት አይደለም። በውጤቱም በወረዳዎች እንዲሁም በገጠርና በከተማ ልዩነቶች ተከስተዋል።

ዘጠነኛ፥ የሥነ ልሳን ትምህርት ከቀረቡት ትምህርቶች አንፃር ዝቅተኛ ውጤት የተመዘገበበት ነው። ጎልቶ የሚታየው በገጠር ሲሆን አንዱና ዋነኛው ምክንያት ሊሆን የሚችለው የሰለጠነ ባለሙያ በብቃት አለመመደቡ ነው።

## 5.2. መደምደሚያ

በጥናቱ ግኝት መሠረት በምስራቅ ሸዋ ዞን ለስምንተኛ ኦሮምኛ ክፍል የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት በአብዛኛው ተግባራዊ እንደሆነ ማየት ተችሏል። በዕቅዱና በትግበራው መካከል ከ50% በላይ ተጣጥሞሽ ታይቶበታል። ይህም ሊታወቅ የቻለው መምህራንና ርዕሰ መምህራን በፅሁፍ መጠይቁ ከሰጧቸው መልሶች፥ በክፍል ውስጥ ከተካሄደው ምልከታና ለተማሪዎች ከተሰጠው የብቃት መለኪያ ፈተና ውጤት ነው።

በመርሃ ትምህርቱ ከታቀደው ከአማካይ በላይ ተግባራዊ መሆኑን የክፍል ውስጥ ምልከታው አረጋግጧል። በርካታ ተማሪዎች የቀረበላቸውን የብቃት መለኪያ ፈተና ማለፋቸው ይህንኑ የሚገልፅ ነው። የመምህራኑ አመለካከት 50% አዎንታዊ መሆኑ የመርሃ ትምህርቱ ትግበራ በአብዛኛው መሳካቱ ከዚህ ጋር የሚታይ ነው።

የተማሪ መፃህፍትን በተመለከተ በአማካይ (2:3) ሁለት መፅሃፍ ለሦስት መሆኑ

ከአንድ ትምህርት ቤት በስተቀር በሌሎቹ ትምህርት ቤቶች በቂ መፃህፍት መኖሩን ያመለክ ታል። መምህራኑም በሰጡት ምላሽ 100% መርሃ ትምህርቱን የመምህሩን መምሪያና የተማሪ ውን መፅሃፍ እንደሚያገኙ አመልክተዋል። ምን እንደታቀደ እንዴት መቅረብ እንዳለበትና ምን እንደቀረበ መመሪያ ለማግኘት አመቺ ሁኔታ መፈጠሩን ያሳያል። የትግበራው ሂደት በአብዛኛው የተሳካ መሆኑ ከዚህ ጋር የሚያያዝ ሊሆን ይችላል።

በመሆኑም በታቀደውና በተግባር ላይ የታየው ውጤት ከ50% በላይ ነው ቢባልም አመርቂ ነው ማለት አይቻልም። ስለዚህ የመርሃ ትምህርቱን ትግበራ ሙሉ ለሙሉ ስኬታማ ነት ለማየትና ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማሸጋገር የትግበራ መሰናክል ሆነው የታዩት ሊወገዱ ይገባል።

## 5.3. የመፍትሄ ሃሳቦች

ከጥናቱ ግኝት በመነሳት የመፍትሄ ሃሳቦችን መሰንዘር አስፈላጊ ነው። በዚህም መሠረት፥

1. በመርሃ ትምህርቱ የተጠቀሰውን ተግባራዊ ለማድረግ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው 50% በመሆናቸው ይህን ቁጥር ከፍ ለማድረግና ለመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ቀና አመለካከት ለማሳደር ተከታታይ የሆነ ስልጠናዎችና ወርክሾፖች በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ መምህራኑ በወረዳና በዞን ደረጃ መዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው።

2. የፅህፈትና የሥነ ልሳን ትምህርቶችን ለማስተማር በሙያው መሰልጠን ወሳኝ በመሆኑ የሚመደቡት መምህራን 12+2 ደረጃ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል። የአንደኛ ደረጃ መምህራንን የሙያ ብቃት ለማሳደግ በ1993 የተጀመረው የተልዕኮ ትምህርት በተጠናከረ ሁኔታ መቀጠል አለበት ከዚህም ሌላ ሌሎች የሙያ ላይ ስልጠናዎች (In service training) መካሄድ ይኖርባቸዋል።

3. መምህራን ከአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጋር ያላቸው ትውውቅ መጠነኛ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል። ስለዚህ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከመርሃ ትምህርት አዘጋጆችና ከፖሊሲ አውጭዎች ጋር በመቀናጀት የግንዛቤ ማሳደጊያ ጉባኤዎች ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

4. ትምህርቱን ለሳምንት በተመደበው ሁለት ክፍለ ጊዜ ለመሸፈን የማይቻል መሆኑ ተረጋግጧል። ከመላሾቹ 87.5% የሚሆኑት ወደ ሦስት ክፍለ ጊዜ ከፍ ቢል እንደሚሻል አመልክተዋል። የክልሉ ትምህርት ቢሮም ለትምህርቱ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ ማነስ ተመልክቶ አስፈላጊ ማሻሻያ ማድረግ ይኖርበታል።

5. የተማሪዎች በአንድ ክፍል መብዛት በትግበራው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረ በጥናቱ ተመልክቷል። ስለዚህ ትምህርት ቤቶቹም ሆኑ ወረዳው እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ

ድርጅቶች በየጊዜው እያደገ የሚመጣውን የተማሪ ቁጥር በመገንዘብ የመማሪያ ክፍሎችን ለመገንባት በየዓመቱ ዕቅድ መያዝና ግንባታ ማካሄድ ይኖርባቸዋል።

6. በምልከታ እንደታየው 54.2% የሚሆኑት የሰጡትን የቤት ሥራና የክፍል ሥራ ያርማሉ። የሁሉንም ተማሪዎች ማረም ስለማይችሉ የሚያርሙት በተወሰነ ደቂቃ መሸፈን የቻሉትን ያህል ነው። ለዚህም በክፍል ውስጥ ያሉት ተማሪዎች ብዛት አንዱና ዋነኛው ምክንያት ነው። ስለዚህ በተራ ቁጥር 5 የቀረበው መፍትሄ እንደተጠበቀ ሆኖ በርካታ የመማሪያ ክፍሎች በቢሮነትና በመጋዘንነት ከማገልገላቸው ይልቅ በመማሪያ ክፍልነት እንዲያገለግሉ መደረግ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም በየክፍሉ ተማሪዎችን በተመጣጠነ መልኩ በመደልደል የመማር ማስተማሩን ሂደት ማመቻቸት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ድርሻ ነው።

7. በርዕሰ መምህራን የሚደረገው ተከታታይ ምልከታ የመርሃ ትምህርቱን ትግበራ እንደሚያ ጎለብተው ይታመናል። ሆኖም ርዕሳነ መምህራን የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር ምልከታ የሚያካሂዱት በሴሚስተር አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑ ተስተውሏል። ስለሆነም ርዕሳነ መምህራን አስተዳደራዊ ሥራቸውን በመቀነስ ለትምህርቱ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የምልከታ ድግግሞሽን ከፍ ማድረግና በመርሃ ትምህርት ትግበራ ላይ የሚነጋገር ስብሰባ ማካሄድ ይኖርባቸዋል።

8. ቤተመፃህፍት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያገኙትን ዕውቀት የሚያመሳክሩበት፥ የሚያዳብሩ በት፥ ለተጨማሪ ዕውቀት ንባብ የሚያካሄዱበት፥ በግዢም ሆነ በሌላ መንገድ በቀላሉ ሊያገኟቸው የማይችሏቸውን መፃህፍት የሚያገኙበት ሥፍራ ነው። ሆኖም 87.5% በሚሆኑት ትምህርት ቤቶች ቤተመፃህፍት እንደሌለ ተረጋግጧል። ስለዚህ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የየወረዳዎቹን ትምህርት ቤቶች ጽህፈት ቤቶችና መንግስታዊና መንግስ ታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር በየትምህርት ቤቶቹ ቤተመፃህፍት በመገንባትና የመፃህፍት ግዢ በማድረግ ማደራጀት ይጠበቅባቸዋል።

9. ይህ ጥናት ከአገሪቱ በአንዱ ዞን ባሉ ትምህርት ቤቶች ላይ የተካሄደ ነው። ፍላጎት ያላቸው ተመራማሪዎች ይህን ጉዳይ በሌላ አውዶችና ሁኔታዎች በሌሎች ዞኖችና ክልሎች በመውሰድ ቢያጠኑ መልካም ነው።

# ዋቢ ምንጮች

## ሀ. የእንግሊዝኛ ምንጮች


Allen, J.P.B 1984. "General purpose Language Teaching: A variable Focuse Approach" in C.J. Brumfit ed. General English syllabus Dedsign. Oxford: Pergamon.

Aspinwall, A. Kath *et al.* 1992. Managing Evaluation In Education. London: Mackays of Chatman P.L.C.

Beauchamp G. 1968. Carriculum Theory (2nd ed). USA: Kagg.

Brandt, R.S. (ed). 1981 Applied strategies for carriculum Evaluation. Washington: Association for Supervision and Carriculum Development.

Brown, H.D. 1994 Principles of Language Learning and Teaching. Englewood Cliffs: Prentice Hall Regents.

Cronback, L.J. 1963. "Course Improvement Through Evaluation." In Teachers College Record Vol. 68. No. 8. Colombia University.

Davies, I.K..1981. Instructional Technique. New York: McGraw Hill Book Company.

Dubin F. and E. Olshtain. 1987. Course Design: Developing Programme and Material for Language Learning. Cambridge: CUP.

Fraas, J. W. 1983. Basic concepts in Educatiotional Research. London: University Press of America.

Fullan and Pomfret. 1977 "Research on Carriculum and Instruction Implementation", Review of Educational Research, Vol. 47, No2.

Fullan, M. 1981. "The Relationship Between Evaluation and Implementation" , In Lewy Arich and David Nevo (eds). Evaluation Roles in Education. London: Gordon Breach.

____________1991. The new meaning of Educational change. New York: Teachers College Press, Colombia Univeristy.

____________1993. Change Forces. London: The Flamer Press.

Gene, E. Hall. 1995. "The Local Educational Change Process and Policy Implementation", in International Prespectives on Educational Reform and Policy Implementation. Edited by Carter, D.S.G. and Marine H.o'Neill. London: London: The Falmer Press.

Giroux, H.A. *et al* (eds).1981. Carriculum and Instruction. USA: McCutchan Publishing Corporation.

Lang, G. and George D.H. 1991. A practical Guide to Research Methods (4th ed). New York: University of America.

ICDR. 1995. Some Hints on Carriculum Development Process. Addis Ababa (Unpublished)

Koul, L. 1996. Methodology of Educational Research. (2nd Revised edition) New Dehil: Vikas, Publishing house privet Ltd.

Lewy, A. (ed) 1977. Hand Book of Curriculum Evaluation. Paris: Longman Inc.

MacDonald F. 1978. "Evaluating Preservice Teachers Competance", Journal of Teachers Education Vol. 28., No. 2.

Madsen, H.S. 1983. Techniques in Testing. Oxford: OUP.

McCormic, R. and James, M. 1983. Carriculum Evaluation in schools. 2nd ed. London: Routledge.

Ministry of Education 1986. "Evaluation Research of the General Education System in Ethiopia (ERGESE)", Addis Ababa (Unpublished).

Nachmias, D. and Chava Nachmias. 1987. Research Methods in the Social Sciences (3rd ed). New York: St Martin's Press.

Nixon, U. 1989. "Norzanza: An Evaluation Simulation in Teacher Training." ELTJ. Vol. 42, No. 2

Nunan, D. 1987. Guideline for the Development of Curriculum Resource. Adelaide: National Curriculum Resource Center.

____________1988. Syllabus Design. Oxford: OUP.

Ornstein, A. C. and Hunkins. 1988. Curriculum: Foundations, Principles and Issues. New Jersy: Pretice Hall. Inc.

____________1998. Curriculum: Foundations, Principles and Issues. (3rd ed) Boston: Allyn and Bacon.

Popham, W. J. 1993. Educational Evaluation . (3rd ed) Boston: Allyn and Bacon.

Posener, G. J. 1992. Analysing the Curriculum. New York McGraw Hill, Inc.

Pratt, D. 1998. Curriculum: Design and Development. New York: HBJP.

____________1994. Curriculum Planning: A Hand Book for Professionals. New York: Harcor Brace College Publishers.

Provus, Matcom 1971. Discripancy Evaluation for Educational Program Implementation and Assesment. Barkeley: McCutchan Publishing Corporation.

Richards, J. C. and T. S. Rodgers 1995. Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge: CUP.

Ross, K. N. and Postlethwaite J. N. 1992. Indicators of the quality of Education: A summary of National Study of Primery school in Zimbabwe. Paris: International Institute for Educational Planning Printshop.

Shiundu, J.S. and S. Jomulando. 1992. Curriculum Theory and Practice in Kenya. Nairobi: OUP.

Stake, R. E. 1967. "The countenance of Educational Evaluation", Teachers College Record. Vol. 68, No. 7.

____________1975. "Language, Rationality, and Assesment" in Curriculum Evaluation, Edited by David and Payne. USA: D.C. Heat and Campany.

Stenhouse, L. 1975. An Introduction to Curriculum Research and Development. London: Heinemann.

Sterm, H.H. 1984. "Review and Discussion." General English Syllabus Design. ELT Documents 118. C.J. Brumfit (ed.). Oxford: Pergamon Press Ltd.

Stern, /H.H./ 1992. Issues and Options in Language Teaching. Oxford: OUP

Sounders, M. and Graham Vulliamy. 1983. "The Implementation of Curriculum Reform: Tanzania and Pupa New Guinea", Comparative Education Review, Vol. 27, No. 3

Stufflbeam, D. 1973. "The context, Input, Process and Product Model of Evaluation" in Educational Technology Review Series. Vol. 11.

____________1983. "The CIPP Model for Program Evaluation" in Evaluation Model. Edited by George F. Madaus, Michael S. Seriven and Daniel L. Stufflbeam. Boston: Kluwer-Nijhoff.

Toba, H. 1962 Curriculum Development: Theory and Practice. Newyork: Harcourrt Brace Jouanovich, inc.

Tyler, R. W. 1949. Basic Principles of Curiculum and Instruction. Chicago and London. The University of Chicago Press.

Tyler, R. W. 1983 "A Rational for Program Evaluation" in Madaus, G. F. *et al* Evaluation Models. Boston: Nijoff Publishing.

UNESCO. 1978 Planning the Primery School Curriculum in Developing Countries. Paris. International Institute for Educatiotional Planning.

Yeoman, G.D. and Beck A.W. 1987 Curriculum Evaluation. Nothingham University school of Education Publication Department.

## ለ. የአማርኛ ምንጮች


ታደሰ ሲባሞ። 1992። "በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ: የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ መርሃ ትምህርት ትግበራ ግምገማ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ። 1989። <u>የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ፥ 4ኛ መጽሐፍ።</u> ፊንፊኔ፥ ት. መ. ማ. ማ. ድ።

________ 1990። <u>የአማርኛ ቋንቋ ማስተማርያ፥ 4ኛ መጽሐፍ።</u> ፊንፊኔ፥ ት. መ. ማ. ማ. ድ።

________ 1990። <u>የአማርኛ መማሪያ፥ 4ኛ መጽሐፍ።</u> ፊንፊኔ፥ ት. መ. ማ. ማ. ድ።

የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት። 1986። <u>አጠቃላይ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ</u> አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ጥላሁን ገብር ክርስቶስ። 1990። "ትግሪኛ አፍ መፍቻቸው ለሆናቸው ተማሪዎች የተዘጋጀው የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሣይክል ያማርኛ ትምህርት ያካተታቸው ይዘቶች ጥናት" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። (ያልታተመ)።

**አባሪ አንድ በመርሃ ትምህርቱ በመማሪያ መፅሃፍና በመምህሩ መፅሃፍ መካከል ያለው ተጣጥሞሽ**

| የመፅሃፉ ርዕስ | ዝርዝር ዓላማ | ንባብና ማስተዋል | | ፅህፈት | | ሥነ ልሳን | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግ | % | ድግ | % | ድግ | % |
| መርሃ ትምህርት | 19 | 4 | 21 | 6 | 31.6 | 9 | 47.4 |
| የተማሪ መፅሃፍ | 154 | 37 | 24 | 47 | 30.5 | 70 | 45.5 |
| የመምህሩ መፅሃፍ | 154 | 33 | 21.4 | 56 | 36.3 | 65 | 42.5 |
| አማካይ | | | 22.1 | | 32.8 | | 45 |

*ድግ=ድግግሞሽ

# አባሪ ሁለት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## ቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል
## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በምስራቅ ሸዋ ዞን በማስተማር ላይ ባሉ የ8ኛ ክፍል /አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ/ መምህራን የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

የተወደዳችሁ መምህራን፦

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት ለኢ-አፈ-ፊት ተማሪዎች አማርኛን ለማስተማር የተዘጋጀውን የ8ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ትግበራ /Syllabus Implementation/ ምን መልክ እንዳለው መረጃ ለመሰብሰብ ነው።

⇒ከመጠይቁ የሚገኘው መረጃ ለዚህ ጥናት ብቻ የሚውል ይሆናል

⇒ጥያቄዎቹን በግልፅነት በመመለስ ለጥናቱ ውጤት መሳካት ትብብርዎን አጥኚው በትህትና ይጠይቃል

⇒ለሚያደርጉት መልካም ትብብር ሁሉ በቅድሚያ ያመሰግንዎታል።

ማሳሰቢያ

1. በዚህ መጠይቅ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም
2. በጥናቱ ውጤት ላይ ችግር ስለሚያስከትል መጠይቁን በጥንድ ወይም በቡድን ተመካክሮ መሙላት የሚደገፍ አይደለም።

## <u>ክፍል አንድ፡</u> ዳራዊ ሁኔታ /Background/

የት/ቤቱ ስም ________________________ ከተማ ☐ ገጠር ☐

ወረዳ ________________________

አማራጭ መልሶች ባሉበት የ (✓) ምልክት ያስቀምጡ

1. ፆታ ወንድ ______ ሴት ______
2. ዕድሜ ______
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋዎ __________ ሁለተኛ ቋንቋዎ __________
4. የትምህርት ደረጃ
   የኮሌጅ ዲፕሎማ በአማርኛ __________
   የኮሌጅ ዲፕሎማ በሌላ ትምህርት __________
   12+2 ______ 12+1 ______ 12+TTI ______ 10+2 ____
   ሌላ ከሆነ ይጠቀስ ________________

5. የአገልግሎት ዘመን

1-5____ 6-10____ 11-15____ 16-20____ 21-25____ 26ና በላይ____

6. በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት የሰሩባቸው ዓመታት
1-4______ 5-8______ 9-12______ ከ12 በላይ______

7. አሁን የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩት
ያለፍላጎትዎ ተመድበው ነው______ በራስዎ ፍላጎት ነው__________
ስለሰለጠኑበት ነው__________

8. በአሁኑ ወቅት ከ8ኛ ክፍል በተጨማሪ አማርኛን የሚያስተምሩባቸው ክፍሎች?
5ኛ______ 6ኛ______ 7ኛ______ ሌሎች______ የሉም______

9. ከአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ የሚያስተምሩት ሌላ የትምህርት አይነት አለ?
አዎ__________ የለም__________
መልስዎ አዎ ከሆነ ይጥቀሱ____________________

10. የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩት
ለኢ-አፈፊት ብቻ__________ ለአፈፊቶቹም ለኢ-አፈፊቶቹም________

11. መልስዎ ለሁለቱም የሚል ከሆነ በአፈፊቶቹና በኢ-አፈፊቶቹ መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት ይመዝኑታል?
ከፍተኛ______ መካከለኛ________ ዝቀተኛ______ ልዩነት የላቸውም______

12. ለ10ኛው ጥያቄ መልስዎ ለሁለቱም የሚል ከሆነ በአንድ መምህር እንዲማሩ መደረጉ በመርሀ ትምህርቱ ትግበራ ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ አለ?
አዎ__________ የለም__________

13. በአንድ ሳምንት የሚያስተምሩት ጠቅላላ የክ/ጊዜ ብዛት
ከ10 በታች____ ከ10-15____ 16-20____ 21-25____ ከ25 በላይ____

14. ከማስተማር ሥራ በተጨማሪ በት/ቤቱ የተሰጥዎት የሥራ ድርሻ አለ?
አዎ________ የለም________

## ክፍል ሁለት፦ አመለካከት /Attitude/

ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ሀሳቦች የርስዎ አመለካከት የሆነውን በቁጥሮቹ ሥር (✓) በማድረግ ያመልክቱ:: የነጥቦቹ አሰጣጥ፤

5. በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ
4. እስማማለሁ
3. ለውሣኔ ያስቸግረኛል
2. አልስማማም
1. በከፍተኛ ደረጃ አልስማማም

| የጥያቄ ቁጥር | ጥያቄ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በመርሃ ትምህርቱና በመምህሩ መምሪያው ላይ የቀረቡት የ8ኛ ክፍል 4ኛ መጽሐፍ አላማዎች ተቀባይነት ያላቸው ናቸው | | | | | |
| 2 | በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ትምህርት አደረጃጀት ተከታታይነት የጠበቀ ነው:: | | | | | |
| 3 | በመማሪያ መፅሃፉ የቀረቡትን መልመጃዎች በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል:: | | | | | |
| 4 | በዚህ ደረጃ ተዘጋጅቶ የቀረበው የ8ኛ ክፍል አማርኛ የመምህሩ መምሪያ መፅሃፍ መምህራን በቅድሚያ እንዲዘጋጁ በቂ መረጃ ይሰጣል | | | | | |
| 5 | መልመጃዎቹን ተማሪዎቹ በተገቢው ሁኔታ እንዲያከናውኑዋቸው ለማድረግ የመምህራንን ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል | | | | | |
| 6 | በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ትምህርት ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚገናዘብ ነው:: | | | | | |
| 7 | የቀረበው ትምህርት በደረጃው ካሉ ሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ግንኙነት በቂ ነው:: | | | | | |
| 8 | ተማሪው እንዲያከናውን የቀረቡለት ተግባራት ተተግባሪ /Applicable/ የሚሆኑ ናቸው:: | | | | | |
| 9 | በመርሃ ትምህርቱ ላይ እንደተጠቀሰው የተማሪዎቹን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ፣ የመፃፍ ክሂሎችን እንዲሁም የሥነ ልሣንና የሥነ ፅሁፍ ዕውቀት ለማዳበር የሚያስችል ነው:: | | | | | |
| 10 | በመምህሩ መምሪያ ላይ እንደተጠቀሰው ተማሪዎቹ የ8ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ሲጨርሱና ወደ ዘጠነኛ ክፍል ሲዛወሩ በብሔራዊ ደረጃ በአንድ መልክ ለሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ብቁ ሆነው ይገኛሉ:: | | | | | |
| 11 | የቀረቡትን መልመጃዎች የተማሪዎችን ተሣትፎ የሚያዳብሩ ናቸው:: | | | | | |
| 12 | የቀረቡት ይዘቶች ከተማሪው ዕውቀት ጋር ተመጣጣኝ ናቸው:: | | | | | |
| 13 | የመምህራኑ ተግባር በመፅሃፍ ውስጥ የተቀመጡትን ብቻ ለተማሪዎች ማቅረብ ነው:: | | | | | |

## ክፍል ሦስት፦ አስተዳደር ነክ

3.1. ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች ፊደሎችን በማክበብ ወይም በባዶው ቦታ ሀሣብዎን በመፃፍ መልስ ይስጡ።

1. የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ 4ኛ መፅሃፍ በእጅዎ ወይም በትምህርት ቤትዎ አለ? ሀ. አዎ ለ. የለም

2. የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ 4ኛ መፅሃፍ (Teacher's Guide) በእጅዎ ወይም በትምህርት ቤትዎ አለ? ሀ. አዎ ለ. የለም

3. ለሁለተኛ ጥያቄ መልስዎ "ለ" ከሆነ የሚያስተምሩትን ሥራ እንዴት እያቀዱት ነው?

____________________________________________

____________________________________________

4. በትምህርት ቤትዎ የአማርኛ ቋንቋ ዲፓርትመንት አለ? ሀ. አዎ ለ. የለም

5. ለአራተኛው ጥያቄ መልስዎ "ሀ" ከሆነ የ8ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ትግበራን በተመለከተ ውይይት አካሒዳችሁ ታውቃላችሁ? ሀ. አዎ ለ. አናውቅም

6. መርሃ ትምህርቱን በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ ሥልጠና ያስፈልገኛል ይላሉ? ሀ. አዎ ለ. አያስፈልገኝም

7. በተራ ቁጥር ስድስት ለሰጡት መልስ ምክንያትዎን ቢያቀርቡ ____________________________________________

8. ለትምህርቱ የተመደበው ክ/ጊዜ በመርሃ ትምህርቱ የቀረበውን በወቅቱ ለማጠናቀቅ በቂ ነው ብለው ያምናሉ ሀ. አዎ ለ. አላምንም

9. መልስዎ "ለ" ከሆነ ስንት ክ/ጊዜ ቢመደብ ይሻላል ይላሉ? ____________

10. በሳምንት የያዙት የክ/ጊዜ ብዛት በማስተማር ሥራዎ ላይ ጫና አሳድሯል? ሀ. አዎ ለ. አላሳደረም መልስዎ አዎ ከሆነ ምን አይነት? ________

____________________________________________

____________________________________________

11. በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች በአማካይ ስንት ተማሪዎች በአንድ ክፍል ይማራሉ?

ሀ. ከ40 በታች ለ. 40-60 ሐ. 60-80 መ. 80 በላይ

12. በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር በመማር ማስተማሩ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል?
   ሀ. አዎ ለ. አላሳደረም
   መልስዎ አዎ ከሆነ ተፅዕኖውን ይጥቀሱ ________________________________

______________________________________________________________

13. በዲፓርትመንት ተጠሪ ወይም በት/ቤቱ ር/መምህር በሴሚስተር ምን ያህል ጊዜ ይጎበኛሉ? ሀ. 1 ጊዜ ለ. 2 ጊዜ ሐ. 3 ጊዜ መ. ከዚያ በላይ

14. በር/መምህሩ የሚደረገው ጉብኝት የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚያግዝ መስኩ የሚደረግ ነው ሀ. አዎ ለ. አይደለም

15. የመርሃ ትምህርቱ ትግበራ (Syllabus Implementation) የተሟላ እንዲሆን ከት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ድጋፍ ይደረግልዎታል? ሀ. አዎ ለ. አይደረግልኝም

16. ድጋፍ ከተደረገልዎ በየትኛው ደረጃ ይካተታል?
   ሀ. ከፍተኛ ለ. መካከለኛ ሐ. ዝቅተኛ

17. ለኢ. አፊፌት ተማሪዎች የተዘጋጀውን መፅሃፍ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው
   ሀ. ተስማሚ ነው ለ. በጣም ቀላል ነው ሐ. በጣም አስቸጋሪ ነው

18. የመምህር መምሪያው በተማሪው መፅሃፍ የቀረበውን ለማስተማር በቂ መነሻ ነው
   ሀ. አዎ ለ. አይደለም

19. እንደ ዋነኛ ማስተማሪያ መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙበት
   ሀ. መርሃ ትምህርቱን ለ. የተማሪውን መፅሃፍ ሐ. የመምህሩ መምሪያን

20. ተዘጋጅተው ከቀረቡት የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውጪ በሌሎች ይጠቀማሉ
   ሀ. አዎ ለ. አልጠቀምም

21. ለሃያሁለተኛው ጥያቄ መልስዎ አዎ (ሀ) ከሆነ የሚጠቀሙባቸውን ይጥቀሱ ________

______________________________________________________________

22. በሥራዎ ሂደት ችግር ሲያጋጥምዎ (ሌሎችም ሲያጋጥማቸው) በመወያየት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ያደርጋሉ? ሀ. አዎ ለ. አላደርግም

23. አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በተለይ ስለ ቋንቋ ትምህርት የተገለፀውን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ አለዎ? ሀ. አዎ ለ. በመጠኑ ሐ. የለኝም

24. በዚህ ፖሊሲ ላይ ከሥራ ባልደረቦችዎ ጋር ይወያያሉ?
   ሀ. አዎ ለ. አልፎ አልፎ ሐ. አልወያይም

25. የተዘረጋው የትምህርት አደረጃጀት (ት/ቤት ወረዳ ዞን ክልል) መርሃ ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር ያለው አስተዋፅኦ
   ሀ. ከፍተኛ ነው ለ. መካከለኛ ነው ሐ. ዝቀተኛ ነው

26. ኢ-አፈፊት ተማሪዎች 8ኛ ክፍልን ሲያጠናቅቁ ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር ተመጣጣኝ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ይኖራቸዋል ይላሉ?
ሀ. አዎ ለ. አልልም
ለሰጡት መልስ ምክንያት ይጥቀሱ________________

27. መርሃ ትምህርቱን ከመተግበር አንፃር የታዩና እስካሁን ያልተጠቀሱ ችግሮች ካሉ በባዶው ቦታ ይዘርዝሩ________________
________________
________________
________________
________________

## 3.2. ቁሣዊ አደረጃጀት

| ተ.ቁ | የቁሣቁሥ ሁኔታ/ዓይነት | በቂ | መካከለኛ | ዝቀተኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የተማሪዎች መቀመጫና ጠረጴዛ | | | |
| 2 | የመምህሩ መቀመጫና ጠረጴዛ | | | |
| 3 | ጥቁር ሰሌዳ | | | |
| 4 | የማስታወቂያ ሰሌዳ /በክፍል ውስጥ/ | | | |
| 5 | የሰሌዳ ማፅጃ /ዳስተር/ | | | |
| 6 | የአማርኛ ትምህርት መርጃ | | | |
| 7 | መስኮት | | | |
| 8 | በር | | | |
| 9 | የክፍሉ ስፋት ከተማሪዎች ብዛት አንፃር | | | |

## 3.3. የፅህፈት መሣሪያ አቅርቦት

| ተ.ቁ | | በቂ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አመታዊ ዕቅድ ማዘጋጃ ወረቀት | | | |
| 2 | ሣምንታዊ ዕቅድ ማዘጋጃ ወረቀት | | | |
| 3 | ደብተር | | | |
| 4 | መፃፊያ /እርሳስ፣ እስክርቢቶ/ | | | |
| 5 | ወረቀት /ፈተና ማዘጋጃ/ | | | |

## ክፍል አራት

ከዚህ በታች ከ 1-12 የተዘረዘሩት በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነጥቦች ናቸው:: ከዕሁፎቹ ፊት ለፊት ባለው ክፍት ቦታ ከቀረቡት ውስጥ ነጥቡን ስንተኛ ደረጃ ላይ እንደሚያስቀምጡት ቁጥሩን በመፃፍ ያመልክቱ /ደረጃ ያውጡላቸው/ ተፅዕኖው ከፍተኛ ነው የሚሉትን አንደኛ በማድረግ ይጀምሩ/

| ተ.ቁ. | በትግበራ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ነጥቦች | ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | የማስተማሪያ መሣሪያዎች እጥረት | |
| 2 | የክ/ጊዜ ማነስ | |
| 3 | አማርኛን ለማስተማር ደስተኛ አለመሆን | |
| 4 | የት/ቤቱ ድጋፍ ዝቀተኛ መሆን | |
| 5 | በቂ የሙያ ማሻሻያ አለመኖር | |
| 6 | የተማሪው ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት | |
| 7 | አማርኛ ቀላል ትምህርት ነው የሚል አመለካከት | |
| 8 | ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር አለመፈለግ | |
| 9 | የሰለጠኑ ባለሙያዎች አለመመደብ /እጥረት/ | |
| 10 | አዲሱን መርሃ ትምህርት ለመገንዘብ የሚደረግ ጥረት አነስተኛ መሆን | |
| 11 | የአካባቢው ተፅዕኖ | |
| 12 | ስለ ፖሊሲው ያለው ግንዛቤ አናሳነት | |

ስላደረጉት ትብብር አጥኚው
በድጋሚ ያመሰግንዎታል

# አባሪ ሦስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የቋንቋ ጥናት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ክፍል
## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በምስራቅ ሸዋ ዞን ባሉ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርእሳነ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ።

ውድ ርእሰ መምህር፥

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር (በኦሮምኛ አፋቸውን ለፈቱ) የቀረበውን የ8ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ትግበራ /Implementation/ በሚመለከት መረጃ መሰብሰብ ነው። መረጃው ለዚሁ ጥናት ብቻ የሚውል ስለሆነ ጥናቱ ጠቃሚ ውጤት ማስገኘት እንዲችል ምላሾችን በግልጽነት እንዲሰጡ አጥኚው ያሳስባል።

ለሚያደርጉት ትብብር በቅድሚያ ያመሰግናል።

ማሳሰቢያ: የፊደል ምርጫ ባለበት ፊደሉን በማክበብ ይመልሱ
አማራጮቹ ክፍት ቦታዎች ከሆኑ (✓) ምልክት ይጠቀሙ
የፅሁፍ ምላሽ ለሚፈልጉ ደግሞ የተሟላ መልስ በመፃፍ ይመልሱ

1. የትቤቱ ስም ____________________
   ከተማ ☐ ገጠር ☐
   ወረዳ ____________________
2. የትምህርት ደረጃ ____________________
3. ዕድሜ ____________________
4. በርዕሰ መምህርነት ያገለገሉባቸው አመታት ቁጥር ____________
5. በትምህርት ቤትዎ የሚገኙ መምህራን ብዛት: ወንድ____ ሴት ______ ድምር ____
6. የመምህራን ስልጠና ሁኔታ
   የኮሌጅ ዲፕሎማ __________ 12+TTI __________
   12+2 __________ 12 ያጠናቀቁ __________
   12+1 __________ 10+2 __________

የተለየ ካለ ይገለፅ ____________________

7. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብዛትና የስልጠና ሁኔታ

| ክፍል | ብዛት | ስልጠና /የትምህርት ደረጃ/ |
|---|---|---|
| 5ኛ ክፍል | ______ | ______________ |
| 6ኛ ክፍል | ______ | ______________ |
| 7ኛ ክፍል | ______ | ______________ |
| 8ኛ ክፍል | ______ | ______________ |

8. አማርኛን በኦሮምኛ ክፍሎች የሚያስተምሩ መምህራንና የስልጠና ሁኔታ

| ክፍል | ብዛት | ስልጠና /የትምህርት ደረጃ/ |
|---|---|---|
| 5ኛ ክፍል | ______ | ______________ |
| 6ኛ ክፍል | ______ | ______________ |
| 7ኛ ክፍል | ______ | ______________ |
| 8ኛ ክፍል | ______ | ______________ |

9. በት/ቤቱ ጠቅላላ የመማሪያ ክፍሎች ብዛት ______________

10. በአንድ ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች ብዛት በአማካይ ______________

11. በአንድ ክፍል የሚገኙ ወንበሮች ብዛት አማካይ ______________

12. ቤተመፃህፍት /ንባብ ክፍል/ ሀ. አለው ለ. የለውም

13. በት/ቤትዎ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀው መፅሀፍ በበቂ ሁኔታ ተዳርሷል ሀ. አዎ ለ. አልተዳረሰም

14. የመፅሀፍ ስርጭት

ሀ. አንድ መፅሀፍ ለአንድ
ለ. አንድ መፅሀፍ ለሁለት
ሐ. አንድ መፅሀፍ ለሦስት
መ. አንድ ለአራት
ሠ. አንድ ለአምስት
ረ. አንድ ለስድስት
ሰ. መፅሀፍ ጨርሶ የለም

15. አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት ትግበራ ያደናቅፋሉ የሚሏቸው (ካሉ) ይዘርዝሩ። ______________

______________________________

______________________________

______________________________

16. በኦሮምኛው ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን በአንድ ሴሚስተር ምን ያህል ምልከታ ያደርጋሉ?______________

17. በምልከታው የተመለከቷቸው ዋና ዋና ችግሮች ይዘርዝሩ። ______________

______________________________

______________________________

18. በኦሮምኛው ክፍል አማርኛን ከሚያስተምሩ ጋር በተናጠል ወይም በዲፓርትመንት ደረጃ ስብሰባ ያደርጋሉ? ______________

______________________________

19. በተራ ቁጥር 18 መሠረት መምህራኑ በዋናነት የሚያነሷቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?

___

___

20. ለእነዚህ መምህራን ተጨማሪ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል ይላሉ? ሀ. አዎ

ለ. አያስፈልጋቸውም ለሰጡት መልስ አጭር መግለጫ ቢሰጡ ___

___

___

21. በተለያዩ ወርክሾፖችና ሴሚናሮች አማካይነት ከአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጋር ትውውቅ አድርገዋል? አዎ ___ አላደረግሁም ___

22. ከበላይ አካል (ከወረዳ) የትምህርት ትግበራ ሂደት ለማመቻቸት የሚደረግ ድጋፍ እንዴት ይገልፁታል? በቂ ___ መካከለኛ ___ ድጋፍ የለም___

23. ት/ቤትዎ ለመምህራን የሚያደርገው የእቃ አቅርቦት ሁኔታ በሠንጠረዥ ይሙሉ።

| ቁሳቁስ | በበቂ ሁኔታ | በመጠኑ | የለም |
|---|---|---|---|
| አመታዊና ሳምንታዊ እቅድ ማዘጋጃ ወረቀት | | | |
| መፃፊያ /እስኪርቢቶ እርሳስ/ | | | |
| ተከታታይ ምዘና መመዝገቢያ ቅፅ | | | |
| የፈተና /ቴስት/ ማዘጋጃ ወረቀት | | | |
| የመርጃ መሣሪያዎች ማዘጋጃ | | | |

24.

| የክፍል ደረጃ | የሴክሽኖች ብዛት | የተማሪዎች ብዛት | | | የኦሮምኛ ክፍል ብዛት | የኦሮምኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | | |

# አባሪ አራት

## የክፍል ውስጥ ምልከታ

ሀ. እርከናዊ ልኬት /Rating Scale/

የት/ቤቱ ስም: ______________________________

ወረዳ ______________________

ክፍል ______________________

የምልከታው ቀን ______________

ክፍለ ጊዜ __________ ከ_____ ሰዓት እስከ______ ሰዓት

የትምህርቱ ርዕስ ______________________

| ተ.ቁ. | የማስተማር ክንውን | በተደጋጋሚ | አልፎ አልፎ | አያደርግም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በየደረጃው ለሚደረገው ተግባር ምን ያህል መግለጫ ይሰጣል? | | | |
| 2 | በመረጃ የተደገፈ መግለጫ ምን ያህል ይሰጣል? | | | |
| 3 | ተማሪዎችን ምን ያህል ምጋቤ ምላሽ ይጠይቃል? | | | |
| 4 | ተማሪዎች ምን ያህል ተሣታፊ ናቸው? | | | |
| 5 | ትምህርቱን ተማሪ ተኮር ለማድረግ ምን ያህል ይጥራል? | | | |
| 6 | ጠቃሚ ነጥቦችን በሰሌዳው በምን ሁኔታ ይፅፋል? | | | |
| 7 | ክሂሎችን ለማዛነቅ ምን ያህል ይጥራል? | | | |
| 8 | ትምህርቱን ከዕለት ሁኔታ ጋር እንዲያገናዝቡ ምን ያህል ይጥራል? | | | |
| 9 | ተማሪዎችን በተናጠል ለመርዳት የሚያደርገው ጥረት ምን ያህል ነው? | | | |
| 10 | በንግግር ሃሣባቸውን እንዲገልፁ ምን ያህል ይጥራል? | | | |
| 11 | የቋንቋውን ህግ በራሳቸው ጥረት እንዲደርሱበት ምን ያህል ጥረት ያደርጋል? | | | |

ለ. ቼክሊስት (✓)

| ተ.ቁ. | ክንውን | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| 1 | ትምህርቱን በዓላማ ይጀምራል? | | |
| 2 | ያለፈውን ትምህርት ይከልሳል? | | |
| 3 | የቤት ሥራ ያርማል? | | |
| 4 | መማሪያ መፅሃፉን ይጠቀማል? | | |
| 5 | የክፍል ሥራ ይሰጣል? | | |
| 6 | በክፍል ሥራ ጊዜ ለተማሪዎች እገዛ ያደርጋል? | | |
| 7 | በራሳቸው ልምምድ እንዲያደርጉ ይተዋቸዋል? | | |
| 8 | የቡድን ሥራን ያበረታታል? | | |
| 9 | የቤት ሥራ ይሰጣል? | | |
| 10 | የዕለቱን ትምህርት ማጠቃለያ ይሰጣል? | | |
| 11 | መምህሩ የማያውቀው ነገር ገጥሞታል? | | |
| 12 | ዕለታዊ/ሳምንታዊ ዕቅድ ይዟል? | | |
| 13 | የቀረበው ትምህርትና የተዘጋጀው ዕቅድ ይጣጣማሉ? | | |
| 14 | ዕለታዊው/ሳምንታዊው ዕቅድ ከዓመታዊ ዕቅድ የተወሰደ ነው? | | |

## አባሪ አምስት ዝርዝር የአወቃቀር ሠንጠረዥ

| የትምህርት ክፍል | የቀረበው ዝርዝር ዓላማ | ድግግሞሽ | ድግግሞሽ ከመቶ እጅ | ከ40 የሚሸፍነው በመቶኛ | የወጡ ጥያቄዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| ፅህፈት | -ሆሄያትን በተገቢው መንገድ በመቅረፅ ይጽፋሉ<br>-መስመር ጠብቀው ይፅፋሉ<br>-ሆሄያትን አገጣጥመው ቃላት ይፅፋሉ<br>-ቃላትን አገጣጥመው ዓረፍተ ነገር ይፅፋሉ<br>-ዓረፍተ ነገርን አገጣጥመው አንቀጽ ይፅፋሉ<br>-በስርዓተ ነጥቦች ይገለገላሉ፤ ጭረት÷ይዘት÷ትምህርተ ጥቅስ | 6 | 31.57 | 12.6 | 13 |
| ሥነ ልሳን | -ድርብ ቃላትን ይለያሉ<br>-የቃልን ቀጥታ ትርጉም ይሰጣሉ<br>-በመዝገበ ቃላት ይገለገላሉ<br>-ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ይሰጣሉ<br>-የስም ገላጮችን ይለያሉ<br>-ጠብቀውና ላልተው የሚነበቡ ቃላትና ሀረጎችን ይለያሉ<br>-በተለያዩ ዘዴዎች ቃላትን ይመሰርታሉ÷ ሆሄያትን በመገጣጠም ቃላት ይመሰርታሉ ከቃላት ሌሎች ቃላትን ይመሰርታሉ<br>-በዋና ቃል ላይ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን በመጨመር ቃላት ይመሰርታሉ<br>-ምህፃረ ቃላትን ይመሰርታሉ ምህፃረ ቃላትን ይፈታሉ | 9 | 47.36 | 18.9 | 19 |
| ንባብና ማስተዋል | -ቃልን ሀረግንና ዓረፍተ ነገርን ይለያሉ የቃላትን ምንነት ተገንዝበው ይገለገሉባቸዋል<br>-ሀረግን ለይተው ያወጣሉ<br>-ዓረፍተ ነገርን ይለያሉ<br>-ሆሄያትንና ቃላትን እያቀያየሩ በተለያየ መንገድ በስርዓት በመደርደር የትርጉም ለውጥ ማምጣቱን ይለያሉ | 4 | 21.05 | 8.4 | 8 |
| ድምር | 19 ዓላማዎች | 19 | 99.98 | 39.9 | 40 |

# አባሪ ስድስት

## የ1993 አንደኛ ወሰነ ትምህርት ማጠቃለያ የአማርኛ ቋንቋ የብቃት መለኪያ ፈተና ለ8ኛ ኦሮሚፋ ክፍል

ወረዳ________________ ኮድ________________

ት/ቤት________________ ኮድ__________

ስም ከነአባት________________

መለያ ቁ.________________

**<u>አጠቃላይ መመሪያ</u>**:- በዚህ የፈተና ጥራዝ 40 ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ጥያቄዎቹን ለመሥራት የተፈቀደው ጊዜ <u>ስልሳ ደቂቃ</u> (አንድ ሰዓት) ለቀረቡት ጥያቄዎች አልፎ አልፎ መመሪያዎች ተሰጥተዋል:: መመሪያዎቹን መሠረት በማድረግ መልሶቻችሁን ስጡ::

*መመሪያ አንድ*

<u>ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ ከስሩ ላሉት አራት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መልስ ነው የምትሉትን በባዶው ቦታ አስቀምጡ::</u>

በዘመናዊ የህክምና ሙከራዎች ሻይ ጠቃሚ የሆኑ ጠባዮች እንዳሉት ተረጋግጧል:: በሻይ ውስጥ የሚገኘው ካፌን ዋናውን የነርቭ ክፍል እንደሚያነቃቃና ጠጪውን ዝግጁ እንደሚያደርገው ታውቋል:: አንድ የነርቭ ስፔሻሊስት እንደገለፁት ሻይ መጠጣት የአዕምሮን ሥራ በአስር በመቶ እንደሚያሻሽለው ውጤቱም ለአርባ አምስት ደቂቃዎች ያህል እንደሚቆይ አረጋግጠዋል:: በሻይ ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ውሁዶች እንደ አልከሎይድስ ያሉት ደግሞ የተለጣጭ ጡንቻዎችን የግፊት ችሎታ እንደሚያጠናክሩና ድካምንም እንደሚያስወግዱ ተረጋግጧል:: በተጨማሪም ሻይ መጠጣት ሽንትን ከሰውነት ውስጥ ለማስወገድ እንደሚጠቅም እንክብል መድኃኒት ሆኖ ያገለግላል:: በተጨማሪም የተጠጡ አልኮሎችንና የአልኮል ውጤቶችንም ለማውጣትና ለማስወገድ ያገለግላል:: በሻይ ውስጥ የሚገኙት የአልኮሎይድና የአሮማቲክ ውሁዶች የጨጓራ ፍሳሾችን ለማፋጠን የስብ ቅባትንና የፕሮቲንን ንጠረ ነገሮች በአፋጣኝ ለመፍጨትና ለማሟሟት፣ ሥጋ ከተበላ በኋላ የሚፈጠረውን የቅባት መጠን ለማስወገድ እንደሚጠቅሙ ተረጋግጧል::

ከአማርኛ መማሪያ 4ኛ መጽሐፍ (8ኛ ክፍል) የተወሰደ::

## ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች፦

____ 1. በምንባቡ መሠረት ሻይ ጠቃሚ የሆኑ ጠባዮች እንዳሉት የተረጋገጠው

ሀ. በአንድ የነርቭ ስፔሻሊስት ለ. ቡናና ሻይ መስሪያቤት

ሐ. በዘመናዊ ህክምና ሙከራዎች መ. ይዘት ባለው ውሁዶች

____ 2. ከሚከተሉት አንዱ በምንባቡ የተባለ አይደለም

ሀ. ሽንትን ከሰውነት ውስጥ ለማስወገድ የሻይ እንክብል መውሰድ ጠቃሚ ነው

ለ. ሻይ መጠጣት የአዕምሮን ሥራ አስር ከመቶ ያሻሽላል

ሐ. በሻይ ውስጥ የሚገኘው ካፌን ዋናውን የነርቭ ክፍል ያነቃቃል

መ. በሻይ ውስጥ የሚገኙ ውሁዶች ሥጋ ከተበላ በኋላ የሚፈጠረውን የቅባት መጠን ለማስወገድ ይጠቅማሉ።

____ 3. የአዕምሮ ሥራ በአሥር በመቶ የሚሻሻለው

ሀ. ለ45 ደቂቃ ሻይ በመጠጣት ለ. ሻይ ከተጠጣ ከ45 ደቂቃ በኋላ

ሐ. ሻይ ጠጥቶ ለ45 ደቂቃ ያህል መ. ለ45 ደቂቃ ሻይ ማፍላት

____ 4. የሚፈጠረውን የቅባት መጠን ለማስወገድ እንደሚጠቅም ተረጋግጧል።
/የተሰመረበት ቃል ሊተካው የሚችለው ቃል/

ሀ. ገለል ለማድረግ ለ. ለማጥፋት

ሐ. ለመግደል መ. ለመግፋት

## መመሪያ ሁለት

ከ5 8 ያሉትን ጥያቄዎች ለያንዳንዱ በተሰጠው መመሪያ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በተሰጠው ባዶ ቦታ መልሱ /ፃፉ/

____ 5. ጎበዝ ተማሪ ጠንክሮ ይሰራል። /የተሰመረበትን ቃል ሊተካ የሚችለው/

ሀ. ደርቆ ለ. በርትቶ ሐ. ተጨንቆ መ. ተጣድፎ

____ 6. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ አንዱ ሊሎቹን አጠቃልሎ ሊወክል ይችላል።

ሀ. ሳር ቤት ለ. ቆርቆሮ ቤት ሐ. መኖሪያ ቤት መ. ሰቀላ ቤት

____ 7. ቀጥሎ የቀረቡት ስሞች በፊደል ተራ ቢቀመጡ ቅደም ተከተሉ የሚሆነው

1. ግርማ 2. ሀብታሙ 3. ሰይድ 4. ጫላ

ሀ. 2÷3÷1÷4 ለ. 2÷4÷3÷1

ሐ. 1÷3÷4÷2 መ. 3÷2÷4÷1

____ 8. 1. ገረመው 2. ገላገሉ 3. ጉዲና 4. ጌጤ

በፊደል ተራ ሲቀመጡ ቅደም ተከተሉ የሚሆነው

ሀ. 2÷1÷3÷4 ለ. 1÷2÷4÷3

ሐ. 3÷1÷2÷4 መ. 2÷1÷4÷3

ቀጥሎ ከ9-12 የስርዓተ ነጥብ ጥያቄዎች ቀርበዋል ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ በመልስ መስጫው ቦታ ፃፉ

____ 9. ወደ ገበያ የሔደችው ማን ናት ____ በክፍት ቦታው የሚገባው ሥርዓተ ነጥብ

ሀ. ። ለ. ? ሐ. ፡ መ. .

___ 10. የሰው የሆነ ሃሣብ በፅሁፍ ውስጥ ሲገኝ ለመለየት የምንጠቀመው ስርዓተ ነጥብ

ሀ. :　　ለ. “ ”　　ሐ. ::　　መ. ( )

___ 11. ስርቶ አደር በሁለቱ ቃላት መሀከል የሚገባው ሥርዓተ ነጥብ

ሀ. :　　ለ.　　ሐ. :　　መ. .

___ 12. ትክክለኛውን ሥርዓተ-ነጥብ የተከተለው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

ሀ. "ትምህርት እንዴት ነው? ብሎ ጠየቀው::"
ለ. "ትምህርት እንዴት ነው" ብሎ ጠየቀው::
ሐ. "ትምህርት እንዴት ነው? ብሎ ጠየቀው"
መ. "ትምህርት እንዴት ነው?" ብሎ ጠየቀው::

**ከ13 33 ለቀረቡት የተለያዩ ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ትክክል የሆነውን መልስ ፊደል ለመልስ በተተወው ባዶ ቦታ ላይ ፃፉ**

_____ 13. ቀጥሎ ያሉት ቃላት በቅደም ተከተል ሲደረደሩ የሚያስገኙት ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው? /በላና ቁርስ ሄደ ትምህርት ወደ/

ሀ. ወደ ትምህርት ቤት ሄደ በላና ቁርስ::
ለ. በላና ወደ ትምህርት ቤት ቁርስ ሄደ::
ሐ. ቁርስ በላና ወደ ትምህርት ቤት ሄደ::
መ. ቁርስ በላና ሄደ ወደ ትምህርት ቤት::

_____ 14. ስርዓት እና ማህበር በጋራ ሊመሰረቱ የሚችሉት ጥምር ቃል

ሀ. ማህበረ ስርዓት　　ለ. ስርዓት ማህበር
ሐ. ስርዓተ ማህበር　　መ. ጥምር ቃል አይመሰርቱም

_____ 15. በርትቶ ያጠና ነበር፤ _____ ፈተናውን አላለፈም:: በክፍት ቦታው የሚገባው አያያዥ ቃል

ሀ. ነገር ግን ለ. ስለሆነም　　ሐ. በመሆኑ　　መ. ስለዚህ

_____ 16. መስሪያ ቤትን ከመስሪያ ቤት መስሪያ ቤትን ከግለሰብ የሚያገናኝ ደብዳቤ

ሀ. የሥራ ደብዳቤ　　ለ. የዘመድ ደብዳቤ
ሐ. ኢ-መደበኛ ደብዳቤ　　መ. የቤተሰብ ደብዳቤ

_____ 17. ሁለት እርሳስ ስጠኝ:: በዚህ ዓረፍተ ነገር የስም ገላጭ ቃሉ

ሀ. ሁለት　　ለ. እርሳስ　　ሐ. ስጠኝ　　መ. ገላጭ ቃል የለም

_____ 18. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ምንም የድምፅ ለውጥ ሳያሳይ የ- በቅጥያነት የሚቀበለው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ከወጣቶች　　ለ. በሰለ　　ሐ. ለገደለ　　መ. ሊመጣ

_____ 19. ልጅ ብሎ ልጄ ከተባለ መኪና ብሎ _______ ይባላል::

ሀ. መኪኔ　　ለ. መኪናዬ　　ሐ. መኪናዋ　　መ. መኪና

_____ 20. ከሚከተሉት አንዱ መነሻ ቅጥያ ነው::

ሀ. የ-　　ለ. አል-ም　　ሐ. -ዎች　　መ. -ች

_____ 21. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በአህፅሮት ሲፃፍ
ሀ. የ.መ.ድ. ለ. የተ.መ.ድ. ሐ. የ.ተ.መ.ድ መ. የተ.መ.ድርጅት

_____ 22. ነገረን = እሱ ቢሆን ሰጠቻችሁ _________ ይሆናል።
ሀ. ለናንተ ለ. ለነሱ ሐ. እሷ መ. እሱን

_____ 23. ጎበዙ ተማሪ ፈተናውን በጥሩ ውጤት አለፈ። የዚህ አረፍተነገር የስም ገላጭ ቃል የቱ ነው
ሀ. ጎበዙ ለ. ተማሪ ሐ. ፈተናውን መ. አለፈ

_____ 24. ከሚከተሉት ቃላት በንበት (በመጥበቅና በመላላት) ከሁለት በላይ ፍች ያለው የትኛው ነው?
ሀ. ጠላ ለ. መና ሐ. ሳለ መ. ፈላ

_____ 25. ከሚከተሉት ስሞች አንዱ የተለየ ሙያ/ተግባር አለው
ሀ. ጠር ለ. ጋሻ ሐ. መድሻ መ. ጎራዴ

_____ 26. ቅርፁን ሳይለውጥ -ነት የሚለውን ቅጥያ የሚቀበለው
ሀ. ሩጫ ለ. ጤና ሐ. ዋና መ. ሥራ

_____ 27. ከሚከተሉት አንዱ -ዎች አይቀበልም
ሀ. ህፃናት ለ. ዶሮ ሐ. ቀበሮ መ. በቅሎ

_____ 28. ትናንት የመጣው እንግዳ ዛሬ ተመልሶ ሔደ። ይህ ፅሁፍ የቀረበው በ_____ ደረጃ ነው።
ሀ. ቃል ለ. ሀረግ ሐ. ዓረፍተ-ነገር መ. አንቀፅ

_____ 29. ምሣሽን በልተሻል? ይህ ዓረፍተ ነገር _______ ነው።
ሀ. መጠይቅ ለ. አብሣሪ ሐ. ትዕዛዝ መ. አሉታዊ

_____ 30. ቀጭኑ ልጅ ነጭ ልብስ ለብሶ እየተኩራራ መጣ። በዚህ ዓረፍተ ነገር የግስ ገላጭ ሆኖ የገባው ቃል
ሀ. ቀጭኑ ለ. ነጭ ሐ. ለብሶ መ. እየተኩራራ

_____ 31. ከሚከተሉት አንዱ ፀረ- ጋር ተጣምሮ ቃል አይመሰርትም
ሀ. ሰላም ለ. ፀሃይ ሐ. ኤድስ መ. ሰብል

_____ 32. ከሚከተሉት ቅጥያዎች አንዱ ከሚገባበት ቦታ አንፃር ይለያል
ሀ. -ን ለ. -ች ሐ. -ዎች መ. ሲ-

የ 33 ና 34 ጥያቄዎች ተስማሚዎቹን ተውላጠ ስሞች በሰንጠረዡ በመሙላት መልሱ

| | | ነጠላ ቁጥር | | | | | ብዙ ቁጥር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ግስ | 1ኛ መደብ እኔ | 2ኛ መደብ አንተ | 2ኛ መደብ አንቺ | 3ኛ መደብ እሱ | 3ኛ መደብ እሷ | 1ኛ መደብ እኛ | 2ኛ መደብ እናንተ | 3ኛ መደብ እነሱ |
| 33 | ሰጠ | | | | | | | | |
| 34 | መለሰ | | | | | | | | |

35. አ..መ..ድ በዝርዝር ሲፃፍ

36. በችኮላ ለማከናወን ጉዳይን አደገኛ መሞከር ነው /ቃላቱን ተገቢውን ቅደም ተከተል በማስያዝ ዓረፍተ ነገር ፃፉ/

37. ቀጥሎ ያለውን ዓረፍተ ነገር ስህተቱን በማረም እነደገና አስተካክለህ ፃፍ "ድመቷ ወተቱን ጠጣ::"

38. <u>ዛሬ የጣለው ዝናብ በርካታ ቤቶችን አፈራረሰ</u> /ይህን ዓረፍተ ነገር በተሰጠው ባዶ ቦታ በጥሩ እጅ ፅሁፍ መስመር ጠብቃችሁ እንደገና ፃፉት/

39. ቀጥሎ ያሉትን አራት አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸውን በማስጠበቅ አንድ አንቀጽ አድርጋችሁ ፃፉ /እንደቅደም ተከተላቸው ቁጥር በመስጠት ልትጀምሩ ትችላላችሁ/

⇒ አየሩ ቀዝቀዝ ብሏል

⇒ ከዚያም ወፍራም ልብስ ደረብ አደርጋለሁ

⇒ ስለዚህ ወደቤት ቶሎ መሄድ ይኖርብኛል

⇒ ይህን ካላደረግሁ ህመሜ ሊቀሰቀስብኝ ይችላል::

40. አፈራረሰው ከዚህ ቃል -ቦታ በማለዋወጥ

-ፊደላቱን በመቀናነስ

መመሥረት የሚቻለውን ቃል ያህል በዝርዝር ፃፉ

## አባሪ ሰባት መልስ የሰጡ መምህራን የግል መረጃ ሠንጠረዥ

| መለያ | የቀረቡ አማራጮች | መልስ የሰጡ መምህራን | |
|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | በመቶኛ |
| ፆታ | ወንድ | 3 | 37.5 |
| | ሴት | 5 | 62.5 |
| | ድምር | 8 | 100 |
| የትምህርት ደረጃ | በአማርኛ 12+2 | 5 | 62.5 |
| | በሌላ 12+2 | - | |
| | 12+1 | - | |
| | 12+TTI | 3 | 37.5 |
| | 10+2 | - | |
| | ሌላ | - | |
| | ድምር | 8 | 100 |
| የአፍ መፍቻ ቋንቋ | አማርኛ | 6 | 75 |
| | ኦሮምኛ | 2 | 25 |
| | ድምር | 8 | 100 |
| ሁለተኛ ቋንቋ | አማርኛ | 2 | 40 |
| | ኦሮምኛ | 3 | 60 |
| | ድምር | 5 | 100 |
| የአገልግሎት ዘመን | 1-5 | | |
| | 6-10 | | |
| | 11-15 | 2 | 25 |
| | 16-20 | 5 | 62.5 |
| | 21-25 | 1 | 12.5 |
| | ከ26 በላይ | - | |
| | ድምር | 8 | 100 |
| በአማርኛ ቋንቋ የሰሩባቸው ዓመታት | 1-4 | 1 | 12.5 |
| | 5-8 | 2 | 25 |
| | 8-12 | - | - |
| | ከ12 በላይ | 5 | 62.5 |
| | ድምር | 8 | 100 |
| ከ8ኛ ክፍል ሌላ የሚያስተምሩባቸው ክፍሎች | 5ኛ | 2 | 25 |
| | 6ኛ | 4 | 50 |
| | 7ኛ | 8 | 100 |
| | ሌሎች | - | |
| | የለም | - | |
| የክፍለ ጊዜ ብዛት በሳምንት | ከ10 በታች | 1 | 12.5 |
| | 10-15 | 5 | 62.5 |
| | 16-20 | 1 | 12.5 |
| | 21-25 | 1 | 12.5 |
| | ከ25 በላይ | - | - |
| | ጠቅላላ | 8 | 100 |
| አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩት | ለኢ-አፈፊት | 3 | 37.5 |
| | ለሁለቱም | 5 | 62.5 |
| | ድምር | 8 | 100 |
| ከማስተማር ውጭ ሌላ ሥራ በአስተዳደሩ የተሰጣቸው | አዎ | 7 | 87.5 |
| | የለም | 1 | 12.5 |
| | | 8 | 100 |

# አባሪ ስምንት ''ሀ''

የመምህራን አመለካከት ስሌት ($x^2$)

| | | |
|---|---|---|
| N=8 | Town=4 | Rural=4 |
| ከ65 | 58 | 57 |
| ያስመዘገቡት | 55 | 52 |
| | 53 | 51 |
| | 52 | 44 |

ጥቅል አማካይ (Grand median)

58 57 55 53 52 52 51 44

$$\frac{53+52}{2} = 52.5$$

የ $x^2$ አማካይ ቴስት ($x^2$ median test statistics) ስሌት

ቀመር $$x^2 = \frac{N\left[(AD-BC)-\frac{N}{2}\right]^2}{(A+B)\,(C+D)\,(A+C)\,(B+D)}$$

| | | | |
|---|---|---|---|
| A=3 | B=1 | C=1 | D=3 |
| A+B=4 | C+D=4 | A+C=4 | B+D=4 |

And N=A+B+C+D=8

$$x^2 = \frac{8[(9-1)-4]^2}{256}$$

$= \mathbf{0.5}$

## አባሪ ስምንት ''ለ''

የብቃት መለኪያ ፈተና በገጠርና በከተማ ንፅፅር የ $x^2$ ስሌት

$$x^2 = \frac{N[(AD-BC)-\frac{N}{2}]^2}{(A+B)(C+D)(A+C)(B+D)}$$

01= N=320 A=135 B=128 C=25 D=32

$$x^2 = \frac{320[(135x32)-(128x25)-160]^2}{(135+128)(25+32)(135+25)(128+32)}$$

$$= \frac{294912000}{383769600}$$

= **0.768**

02= N=320 A=119 B=106 C=41 D=54

$$x^2 = \frac{320[(119x54)-(106x41)-160]^2}{(119+106)(41+54)(119+41)(106+54)}$$

$$= \frac{1779648000}{54720000}$$

= **3.25**

03= N=320 A=102 B=84 C=58 D=76

$$= \frac{320[(102x76)-(84x58)-160]^2}{(102+84)(58+76)(102+58)(84+76)}$$

$$= \frac{2367488000}{638054400}$$

= **3.71**


## አባሪ ስምንት ''ሐ''

$x^2 = \Sigma \frac{(f_o - f_e)^2}{fe}$

| 01 | $f_o$ | $f_e$ | $(f_o-f_e)^2$ | $\frac{(f_o-f_e)^2}{f_e}$ | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 71 | 65.75 | 27.562 | 0.419 | |
| 2 | 69 | 65.75 | 10.562 | 0.160 | |
| 3 | 60 | 65.75 | 33.062 | 0.502 | |
| 4 | 63 | 65.75 | 7.562 | 0.115 | |
| 5 | 9 | 14.25 | 27.562 | 1.934 | |
| 6 | 11 | 14.25 | 10.562 | 0.160 | |
| 7 | 20 | 14.25 | 33.062 | 2.320 | |
| 8 | 17 | 14.25 | 7.562 | 0.530 | **$x^2$=6.14** |

| 02 | $f_o$ | $f_e$ | $(f_o-f_e)^2$ | $\frac{(f_o-f_e)^2}{f_e}$ | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 59 | 56.25 | 7.562 | 0.134 | |
| 2 | 64 | 56.25 | 60.062 | 1.067 | |
| 3 | 45 | 56.25 | 126.5622.250 | | |
| 4 | 57 | 56.25 | 0.562 | 0.010 | |
| 5 | 21 | 23.75 | 7.562 | 0.318 | |
| 6 | 16 | 23.75 | 60.062 | 2.528 | |
| 7 | 35 | 23.75 | 126.5625.328 | | |
| 8 | 23 | 23.75 | 0.562 | 0.023 | **$x^2$=9.591** |

| 03 | $f_o$ | $f_e$ | $(f_o-f_e)^2$ | $\frac{(f_o-f_e)^2}{f_e}$ | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 57 | 46.5 | 100.25 | 2.370 | |
| 2 | 43 | 46.5 | 12.25 | 0.263 | |
| 3 | 37 | 46.5 | 96.25 | 1.940 | |
| 4 | 49 | 46.5 | 6.25 | 0.134 | |
| 5 | 23 | 33.5 | 110.25 | 3.291 | |
| 6 | 37 | 33.5 | 12.25 | 0.365 | |
| 7 | 43 | 33.5 | 90.25 | 2.694 | |
| 8 | 31 | 33.5 | 6.2 | 0.186 | **$x^2$=11.243** |


አባሪ ዘጠኝ
EAST SHEWA ADMINISTRATIVE ZONE
39°00'
NORTH SHEWA
REGION TWO
GIMBICHU
CHEFE DONSA
A.ABABA
REGION THREE
METEHARA
FENTALE
DUKME
AKAKI
DEBRE ZEIT
LUME
BOSET
WELENCHITI
WEST SHEWA
ADAA_
L.CHUKALA
MOJO
NAZARETH
ADAMA
Koka
ARSI
BORA_DUGDA
MEKI
8°00'
Ziway
ZIWAY
SOUTH ETHIOPIA
ADAMI
TULU_JIDO
ARSI
Abijata
Langano
Shala
ARSI
NEGELE
NEGELE
AJE
SHASHEMENE
SHASHEMENE
SIRARO
LEGEND
Regional Boundary
Zonal Boundary
Woreda Boundry
Un Decided Boundary
Zonal Capital
Woreda Capital
Lake
SCALE 1:1,250,000
12.5 0 12.5 25 37.5 50
Kms
39°00'

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተጠቀሰው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ተማሪ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የራሴ ሥራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኳቸውን ተዛማጅ ፅሁፎችና ሌሎች የመረጃ ምንጮች በአግባቡ የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም [illegible]

ፊርማ

ቦታ አ.አ

ቀን 17/8/87